# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፩ መጋቢት/ሚያዝያ ፲፱፻፺፮ ዓ.ም



ጌቴ ሴማኒ:- ጌታችን የጸለየበት የአትክልት ሥፍራ

(ዮሐ.፲፰፥፩)


እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ!

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመረ ጽድቅ - ልዩ የጋራ እትም

## መጽሔቷ በቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያትቱ የተለያዩ ጽሑፎችን ይዛ ቀርባለች፡፡

☞ ከክቡር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዘዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ



ክቡር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዘዳንት ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ

«ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን በሥነ ምግባር ለማነፅ ቀድሞም ቸል አላለችም፡፡ አሁንም ወጣቱን በማስተማር፤ ማስተማር ብቻም አይደለም የጠባይ ለውጥም እንዲ ያመጣ ጠንክራ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡»

« ቤተ ክርስቲያን ነባርና በኅብረተሰቡ ዘንድ እምነት የሚጣልባት ተቋም እንደ መሆኗ ለአረጋውያኑም ሆነ ለአሳዳጊ አልባ ልጆች መጠለያና መርጃ ብታቋቁም የምትጠይቀውን ርዳታ ከየትኛውም አካል ማግኘት የምትችልበትን ሁኔታ መንግሥት ያመቻቻል፡፡ »

« የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በሁሉም መልኩ ለአገሪቱ ያበረከተችው አስተዋፅዖ በቀላሉ ተነግሮ የሚታለፍ አይደለም፡፡ በታሪክም ቀደምትና የ ሠለጠነች ተቋም ስለሆነች ከሌላው በበለጠ የማኅበራዊ አገልግሎት ድርሻ አላት፡፡»

ከክቡር ፕሬዘዳንቱ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ጠቅላላ ይዘት ከሐመረ ጽድቅ ያገኙታል፡፡

☞ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የወጣቶች ሐዋርያ የነበረው የጋሽ ግርማ ከበደ ታሪክና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ለእኛ አብነት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፤

☞ «የመናፍቃን የጽሑፍ ቅሰጣ በኢትዮጵያና የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መልስ አጭር ዳሰሳ»

☞ «በድህነት ቅነሳ - የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚና ይኖራታልን?» በሚል ርእስ ቤተ ክርስቲያናችን በአገራችን ድህነት ቅነሳ የሚኖራትን ድርሻ እናያለን፡፡

☞ «አክብሮ በዓልና የሥራ ባሕል» በሚል ርእስ ስለ በዓላት የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት በዝርዝር ያገኙበታል፡፡

☞ «የቤተ ክርስቲያን የብራና መጻሕፍት በየት ይገኛሉ? ምንስ ይደረግ?» መልሱን ከሐመረ ጽድቅ ያገኙታል፡፡

☞ «ክርስቲያናዊ ጋብቻና መሰናክሎቹ» እንዲሁም «ጭንቀት - መንሥኤውና መፍትሔው» የሚሉና ሌሎችንም ትምህርቶች አካታለች፡፡

**በልዩ እትም በ56 ገጽ የተዘጋጀችው ይህች መጽሔት እነዚህንና ሌሎች ጉዳዮችን በማካተት በቅርብ ቀን በሥርጭት ላይ ትውላለች!!**

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስለዚህ ቫይረሱን በመዋጋት ወገኖቻቸውን ከእልቂት ለመታደግ የሚረባረቡት አካላት የቆሙለት ዓላማ ታላቅ መሆኑን ተገንዝበው በትጋትና በቁርጠኝነት ሊን ቀሳቀሱ ይገባል:: የወገኖቻቸውን ችግር አስተውለው መመዘንና መመልከት አለባቸው:: እነዚህ በሺዎች የሚቆጠሩ አካላት ይሠሩ ዘንድ ፈቃድና ዕውቅና የሚ ሰጠው መንግሥት በመሆኑ ማን ጥሩ ይሠራል? የት ኛውስ አይሠራም? በማለት የሚሠሩትን በማበረታ ታት፣ በታውንና ስሙን ብቻ ይዘው የግል ጥቅማቸ ውን ከሚያሳድዱት ደግሞ ሥራውን በመንጠቅ በእው ነትና በእምነት ለሚሠሩት መስጠት ይኖርበታል::

## የማኅበሩ መልእክት

እንደ ሊቃውንቱ አገላለጽ ሌሊት ከቅዳሴ መልስ በየቤታችን ልንመገበው የሚገባ ከጥሉላት ምግቦች ርቀን ከመ ቆየታችን አንጻር ጤንነታችንን የማይጐዳ ማር ፣ ተልባ፣በወተት በእርጎ ተደርጐ ነው የሚበ ላው:: እርድ መፈጸም ያለበት ጠዋት ወይም ደግሞ «ወተንሥአ እሙታን» ከተባለበት ከሌሊቱ 6:00 በኋላ ነው:: ያኔ መስቀል ይዞራልና::

## ጥያቄዎቻችሁ

የልጆች ዕድገት ላይ የማኅበራዊ ሕይወት ገጽታው ወሳኝ ይመስለኛል:: ኪሩቤል ከተወለደ በኋላ ባለቤቴ ወደ ት/ቤት መሄድ ነበረባት:: ከልጃችን ጋር የምና ሳልፈው ጊዜ በጣም አጭር ነበር:: እርስዋ ከት/ቤት ስትመጣ ጥናት አለባት፤ የቤቱን ሥራ ሙሉ በሙሉ የምትሸፍነው ደግሞ እርሷው ናት:: አሜሪካ ውስጥ የኑሮ ገቢ በአንድ በኩል ሆኖ ስለሚከብድ እኔም በበኩሌ የበለጠ ሰዓትና ከበድ ያለ ሥራ መሥራት ነበረብኝ:: ደክሞኝ እመጣለሁ፥ለልጄም በቂ የአባትነት ፍቅሬን መስጠት አልቻልም ነበር:

## ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር - መ/ር ኀይለ ማርያም ላቀው
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail: Hamer@ EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org

«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

ሐመር
፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፩
መጋቢት/ሚያዝያ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

## ማውጫ

የማኅበሩ መልእክት
• በአገር የመጣን ችግር ለማስወገድ ........ ፪
ዳብዳቤዎች ........ ፬
ከሰሞኑ በረከት
• ስሙኑ ሐማማት ........ ፯
ትምህርተ ሃይማኖት
• የንስሐ አባትና ........ ፱
• የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ........ ፲፩
የጥያቄዎቻችሁ መልስ
• እርድ ........ ፲፬
ኪነ ጥበብ
• ከመጋረጃ ጀርባ ........ ፲፮
እናስተዋውቃችሁ
• የዛፍ ጉደፈቻ ........ ፲፰
• አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ........ ፳
ዓምደ ወራዙት
• ከመፋጠጥ መደማመጥ ........ ፳፬
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
• ልጆቻችን ኢትዮጵያዊ ሆነው እንዲያድጉ ........ ፳፯
• ተገናኝተን ስንጫወት እኔ እኮ በተክሊል ላገባ ላገባ ነው አሉኝ ........ ፴፩
ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
• ዝክረ ቴዎፍሎስ፣ጴጥሮስ ወሚካኤል ........ ፴፫
ስቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
• ስለ ቅጽልና የቅጽል ዓይነቶች ........ ፴፮
ወቅታዊ ጉዳዮች
• የእምነት ነፃነት በኢትዮጵያ ሕግ ........ ፴፱

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

... ቅዱሳን ቤተ ... KIDUSAN LIBRARY

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

# በአገር የመጣን ችግር ለማስወገድ አገራዊ ትብብርና እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል::

በተለያዩ ዘመናት ለዓለም ሥጋት የሆኑ፣ ዓለምን በእጅጉ የፈተኑና ጉዳት ያደረሱ ክስተቶች ተፈጥረዋል:: ዓለም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እልቂት ያተረፈባቸው ጦርነቶች፣ የሰው ዘሮችን በጋራ ያጠቁት እንደ ተስቦ፣ ፈንጣጣ፣ ኩፍኝ ያሉ በሽታዎች በአብነት ይጠቀሳሉ:: በዚህ ባለንበት ዘመን ደግሞ ምንም እንኳን ድኻ በሚባሉ አገራትና ሕዝቦች ዘንድ የከፋ ቢሆንም ዓለምን ከጫፍ እስከ ጫፍ ያስጨነቀ፥ ማስጨነቅም ብቻ ሳይሆን ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ የሰው ዘሮች እየጠፉበት ያለ አንድ ከባድ ፈተና በዓለም ላይ ተጋርጧል:: ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ::

ይህ ቫይረስ ተከሰተ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ይመለከተናል የሚሉ አካላት አዳራሽ ዘግተው ሲወያዩና ሲመክሩ፣ ምሁራን ሲመራመሩ፣ ባዕለ ጸጋ መንግሥታት በችግሩ ላይ ለሚደረጉ ጥረቶች ገንዘብ ሲቸሩ እንሰማለን:: ነገር ግን ይህ ትጋታቸው መፍትሔ ሊያመጣ አልቻለም:: ይልቁንም ዕለት ዕለት ሲለፋፍ እንደምንሰማው ቫይረሱ በመቆም ፈንታ እንደ ሰደድ እሳት ከአንዱ ወደ ሌላው በፍጥነት ይዛመታል:: ለምን?

የመጀመሪያው ምክንያት በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ልባዊ ቁርጠኝነት አናሳ ሆኖ መገኘት ይመስለናል:: ሁሉም እንደ ሚያውቀው ችግሩ የተኙት እንዲነቁ፣ የተቀመጡት እንዲቆሙ፣ የቆሙት እንዲሮጡ የሚያደርግ ቢሆንም ለችግሩ መቃለል እንረባረባለን የሚሉት አካላት ችግሩ ላይ ከማተኮር ይልቅ በማያስፈልጉ ቢሮክራሲዎች በተጨባጭ መፍትሔ ሊሆኑ በማይችሉ አካሄዶች ላይ እንደሚያተኩሩ ይሰማል:: ሁሉም በመሳቀቅ እንደሚናገረው በምናወራው ችግር ዙሪያ ከላይ እስከ ታች ሁሉም ፈጣን እንቅስቃሴ ካላደረገ በዚህች አገር ይህ ነው የማይባል እልቂት ሊከሰት ይችላል:: ከበሽታው ጋር ተያያዥ በኾኑ ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ በሺዎች የሚቆጠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዕውቅና ተሰጥቷቸው በሚንቀሳቀሱበት አገር ቫይረሱ በመዳከም ፈንታ እያደረ በመጉልመስ ኢትዮጵያውያንን ሲጥል ይታያል::

ስለዚህ ቫይረሱን በመዋጋት ወገኖቻቸውን ከእልቂት ለመታደግ የሚረባረቡት አካላት የቆሙለት ዓላማ ታላቅ መሆኑን ተገንዝበው በትጋትና በቁርጠኝነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል:: የወገኖቻቸውን ችግር አስተውለው መመዘንና መመልከት አለባቸው:: እነዚህ በሺዎች የሚቆጠሩ አካላት ይሠሩ ዘንድ ፈቃድና ዕውቅና የሚሰጠው መንግሥት በመሆኑ ማን ጥሩ ይሠራል? የትኛውስ አይሠራም? በማለት የሚሠሩትን በማበረታታት፣ በታውንና ስሙን ብቻ ይዘው የግል ጥቅማቸውን ከሚያሳድዱት ደግሞ ሥራውን በመንጠቅ በእውነትና በእምነት ለሚሠሩት መስጠት ይኖርበታል::

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጠውን ፈተና ለማቃለል የሚንቀሳቀሱት እነዚህ አካላት በአንድ ላይ ተቀምጠው በመምከር ሥራ መከፋፈል አለመቻላቸው ወይም እንዲከፋፈሉ አለመደረጋቸው ይመስለናል:: ሁሉም እንደሚገነዘበው ከቫይረሱና ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች ጋር በተያያዘ ሥራ ሊሠራባቸው የሚገቡ ሦስት አቅጣጫዎች አሉ:: የመጀመሪያው ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩትን ወገኖች መከባከብ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በቫይረሱ ምክንያት ወላጆቻቸውንና ጧሪዎቻቸውን ያጡ ሕፃናትንና አረጋውያንን መከባከብና ራሳቸውን ማስቻል፣ ሦስተኛውም በቫይረሱ ያልተያዙት እንዳይያዙ ማስተማርና መምከር ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስት ነጥቦች ተያያዥ ቢ መስሉም ሠራተኞቹ ቁጭ ብለው ተወያይተው ተግባራዊ ቢያደርጓቸው በየራሳቸው ሊስተናገዱ የሚችሉ ሰፊ የሥ ራ መስኮች ናቸው፡፡ ስለዚህ የቫይረሱ በፍጥነት መዛመት እንዲቆም የሚመለከታቸው አካላት በጥሞና አስበውበት ቁጭ ብለው ሥራ ሊከፋፈሉ ይገባል፡፡ ያኔ ማን ምን እንደ ሠራ፤ ማንስ እንዳልሠራ ለማወቅ ይቻላል፡፡

ሦስተኛው ምክንያት በጉዳዩ ላይ የሚንቀሳቀሱ አካላት ገንቢ በሆነ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ዐቢይ አጋር አለመያዛቸው ይመስለናል፡፡ ይኸውም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል ረገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕ ዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ መንሥኤ አድርጋ ለምትሰጠው ትምህርት በችግሩ ዙሪያ እንሠራለን የሚሉት አካላት ተገቢ ወይም ትክክል አረዳድ ያላቸው አይመስልም፡፡ የምትሰጠው ትምህርት በቫይረሱ የተያዙትን የሚጐዳና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው፤ ቫይረሱን ለመከላከል «አማራጭ ዘዴ የሆነውን» ኮንደምን ሰዎች እንዳይጠ ቀሙ ትምህርቷ እንቅፋት ሆኗልና» የመሳሰሉትን አስተያየቶች በየዐውደ ጥናቱ ሲሠነዝሩ ይሰማል፡፡

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች የተቸገሩትን በመርዳት፣ የታመሙትን በመጐብኘት ቅዱስ መጽሐፍ የሚያዝዘውን እንዲፈጽሙ ታስተምራለች፡፡ ትመክራለች፡፡ ነገር ግን ትምህርቷም ሆነ ስብከቷ በቅዱስ መጽሐፍ /በሕገ እግዚአብሔር/ የተመሠረተ በመሆኑ እውነቱን እውነት፣ ሐሰቱን ሐሰት የሚል ነው፡፡ «የኤድስ ቫይረስ በዝሙትም ይመጣልና አትዘሙቱ» የሚል ትምህርቷን መቃወም እውነትን መቃወም ነው፡፡ ስለ ኮንደም የምታስተምረው ትምህርት የተሳሳተ ነው ማለት «አታመዝንር» የሚለውን ሕገ እግዚአብሔር መጻረር ነው፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን በሚያስቅቅ ሁኔታ ከመጣባቸው ፈተና ራሳቸውን እንዲታደጉ በማድረጉ ረገድ ፍሬ ያለው ሥራ እንሠራለን ብለው ታጥቀው የተነሡ አካላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በመግፋት ፈንታ በአጋርነት አሰልፈው ሊሠሩ ይገባል፡፡ በአገራችን ቤተ ክርስቲያናችን ምን ያህል የለውጥ ኃይል እንደ ሆነች፤ ያንንም የተቀረው ዓለም እንደ ተረዳ የሚያረጋግጥ ዜና ሁላችንም በቅርቡ ሰምተናል፡፡ ይኸውም በኢትዮጵያ የኤድስ ቫይረስን መስፋፋት ለመግታት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ አካል እንደ ሆነች የተረዳው የአሜሪካ መንግሥት ቤተ ክርስቲያናችን በሽታውን በመከላከልና በበሽታው ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡ እጓለ ሙታን ሕ ፃናትን በመከባከብ ላይ አተኩራ የምታከናውነው የተቀናጀ እንቅስቃሴ በገንዘብ እጥረት እንዳይስተጓጐል በማሰብ ከተለመደው የርዳታ ቢሮክራሲ ወጣ ባለ ሁኔታ በፕሬዝዳንት ቡሽ አስቸኳይ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ኢኔሼቲቭ ከተመደበ 15 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር ውስጥ ለመጀመሪያ ዙር አምስት ሚልዮን ዶላር መስጠቱ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያችንም በገንዘቡ የነበራትን የአሠራር መዋቅር አሻሽላ፣ ካለፈው እንቅስቃሴ ጠንካራና ደካማ አካሄዶችን ገምግማ ከላይ እስከ ታች ያሉ ሠራተኞቿን አስተባብራ በትጋት ትሠራለች፡፡

ይህንንም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የርዳታ ስምምነቱን በፈረሙበት ወቅት ባሰሙት ንግግር አረጋግጠዋል፡፡ እንዲህ ሲሉ፡- «በሕዝባችን መጻኢ ሕልውናና በሀገራችን ዕድገት ላይ ጋሬጣ የሆነውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል በምናደርገው እንቅስቃሴ ዛሬ የተፈራረምነው የርዳታ ስምምነት በግዙፍነቱ የመጀመሪያው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአሁን በፊት የጀመርነውን ጥረት በስፋትና በጥረት እንድናካሂድ ከማገዝ አልፎ ተግባራችንን በልበ ሙሉነት፣ በተስፋና በቆራጥነት እንድናከናውን ይረዳናል፡፡ በበኩላችን እስከ ታች ድረስ ዘልቀን አስፈላጊውን መልእክት ሕዝቡ ዘንድ ቶሎ ለማድረስ ችሎታውና ብቃቱ ስለ አለን፤ አሁን በተደረገልን ድጋፍ በመታገዝ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕዝባችንን ጠባይ በመለወጥ ተግባራዊ የሆነ ለውጥ እናስመዘግባለን ብለን እናምናለን፡፡»

ስለዚህ መንግሥትም ሆነ በችግሩ ላይ የሚሠሩት አካላት ይህንን የቤተ ክርስቲያናችንን ዝግጁነትና ዐቅም ተረድተው ተገቢና አስፈላጊ በኾነው ነገር ሁሉ የተገደፈውን በማስተካከል፣ የተጣመመውን በማቃናትና የደከመውን በማበርታት ሊተባበሩ ይገባል፡፡ በአገር የመጣን ችግር ለማስወገድ አገራዊ ትብብርና እንቅስቃሴ ማድረግ ለኢትዮጵያውያን አዲስ ነገር አይደለምና፡፡ የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት፣የእመቤታችን አማ ላጅነት፣የቅዱሳን በረከትና ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ጥንቃቄ

በቅርቡ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የአማራ ክልል ፕሮግራም ላይ በሰሜን ሸዋ አገረ ስብከት ታላቁ የመልከ ጸዴቅ ዋሻ ስለሚገኙት ያልፈረሱ አ ስከሬኖች የተሰጠው «ሳይንሳዊ» ማብራሪያ የቦታ ውን ክብር እንደ ማንንኪሰስ መንፈሳዊ ኃይሉን እንደ መቀነስ አድርጌ ተመልክቸዋለሁ:: በፕሮግራሙ ላይ የገዳሙ አባቶች እንደ ተናገሩት በዚሁ የሐመር መጽሔ ት አንደኛ ዓመት ቁጥር አራት 1985 ዓ.ም እትምም እንደ ተገለጸው በገዳሙ የሚከ ማቹት አስከሬኖች የማይፈ ርሱት፣ የማይበሰብሱትና የማይ ረግፉት እግዚአብሔር ለጻድቁ አቡነ መልከ ጸዴቅ በገባላቸው ቃል ኪዳን ነው:: ይኸውም «እዚህ አንተ በጸለ ይክበት ቦታ መጥቶ የተሳለመውን፣ ያስቀደሰውን ፣በቦታው የተቀበረውን ለአንተ ሰጥቼአለሁ» አላቸው:: አባታ ችንም «የዚህ ዘመን ሰው ምልክት ይፈልጋልና የሚታየው ምልክቱ ምን ድን ነው?» አሉት:: ጌታችንም «በዚህ ቦታ የተቀበረውን ሰው ሁሉ ዐጽ ሙን አፈር አያበሰብሰውም፣ ምስጥ አይ በላውም» አላቸው:: በዚህም መሠ ረት አስከሬን ሲመጣ በመጀመሪያ ይቀበራል:: ከደረቀ በኋላ ይወጣና በየቤ ቱ በየወገኑ (በየዘመዱ) ይቀመጣል:: በእርሱ መቃብርም ሌላ ይቀበራል:: እንዲህም ስለሆነ በገዳሙ ከምዕተ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠሩ አስ ከሬኖች አሉ:: በአጠቃላይ በመገናኛ ብዙኃን የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲ ያናትን ገዳማትና አድባራት በማስተ ዋወቅ ረገድ ያሉት ጥረቶች የሚደነቁ ናቸው:: ይሁንና ከላይ እንደ ተገለጹት ባሉ ሁኔታዎች አኪያ የምናያቸውና የምንሰማቸው አቀራረቦች ጥንቃቄ ቢደ ረግባቸው መልካም ነው:: የቅዱሳንን ቃል ኪዳን በእምነት ከመቀበል ውጭ በራሳችን አመለካከት በመተንተን በረከታቸው እንዲርቀን አንሻምና::

*ኃይለ መስቀል (ባሕር ዳር)*
*ወለተ መድኅን (ደሴ)*
*ኃ.ፕ (አዲስ አበባ)*

## ቢጨመር

ከዚህ ቀደም በአንድ የሐመር መጽሔት እትም በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ላይ ከሁለት በላይ ጥንታ ውያንና ታሪካውያን አድባራትንና ገዳማትን ታቀርቡ ነበር:: አሁን አሁን ግን ለምን እንዳነሰ አላውቅም:: በቀጣዮቹ ዝግጅቶቻችሁ ብዙም የማ ይታወቁ ጥንታውያን ቅዱሳት መካ ናትን በዓምዱ በርከት አድርጋችሁ እንደምታስተዋውቁን ተስፋ አደር ጋለሁ:: በዚህ አጋጣሚ በሐመር 11ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም የጀርባ ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ የኢት ዮጵያንና የምዕራባውያንን የዘመን መለወጫ ልዩነት ምክንያት ያቀ ረባችሁበት አጭር ጽሑፍ ግንዛቤ ያችን ለተለያየው አንባብያን ጥሩ የሆነ ማብራሪያ የሰጠን መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ::

*ይርጋ ታደለ*
*ነቀምት*

## ጥያቄዬ ተመልሶልኛል

የመስከረም/ ጥቅምት የሐ መር መጽሔት እትም እጄ የገባችው በታኅሣሥ ወር መጨረሻ ነበር:: በእጄ መግባት ብቻ ሳይሆን ይዘቷ ንም ሳገላብጥ በትምህርተ ሃይማኖት ዓምድ በሰፈረው ሥርዓተ ጸሎት ወስግደት ጽሑፍ አእምሮዬን ሲረብሸኝ ለነበረው ጉዳይ ትልቅ መልስ አግ ኝቼበታለሁ:: በጠቅላላው በቤተ ክርስቲያናችን የሥርዓት አፈጻጸም ወቅት በግዴለሽነት የምንፈጽማቸው በርካታ ስሕተቶች መታረም እን ዳለባቸው ተረድቻለሁ:: ለምሳሌ በጊዜ ቅዳሴ «ስግዱ. . .» ሲባል ቁጭ የምንል ብዙዎች ነን:: በጸሎት ጊዜያት አቡነ ዘበሰማያትን ስንደግም ስግደት እንዳለ የማናውቅ ጥቂቶች አይ ደለንም::ስለሆነም ለእነዚህና ለመሰል ጥያቄዎቼ መልስ የሰጠችኝ በመሆኑ የሐመር መጽሔትን እወዳታለሁ:: ለእናንተም አምላከ ቅዱሳን ጥበቡን ይግለጽላችሁ::

*ግርማ በዛብህ*
*ደሴ*

## ቃልቻው. . .

ቦታው ከአስኮ ትንሽ አለፍ ብሎ ቡራዩ ሳይደርስ ወደ ውስጥ ይዘልቃል:: የቤቱ ውጫዊ ገጽ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን ቢመስልም እርሱ ግን የቃልቻ (የጠንቋይ) ቤት ነው:: በዚህም ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ሰው እየተታለለ እየተሳለመ ወዲያውም ደግሞ ወደ እነርሱ እየተሳበ ነውና ከወዲሁ የሚመለከተው አካል ተገቢ መፍትሔ ቢያበጅለት መልካም ነው:: ምእመኑም በጉዳዩ ላይ ንቃት እን ዲኖረው መደረግ ይገባዋል::

*ወለተ ገብርኤል*
*አዲስ አበባ*

## እጅግ አስፈላጊ ነው

በቅርቡ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል በገበያ ላይ የዋለው «Utubaa Amantaa -ዓምደ ሃይማኖት» መጽሐፍ በእ ጅጉ አስፈላጊ ሆኖ አ ግኝቼዋለሁ:: ይኸውም በክልላችን ብዙዎች አዳጊ ሕፃናት ቀድመው የሚማሩት በኦሮ ምኛ ቋንቋ በመሆኑ ነው:: መጽሐፉ እኒህ ሕፃናትና አዳጊ ዎች÷ ወጣቶቹም ጭምር ስለ እምነታቸውና ሥርዓታቸው እንዲያውቁ ምቹ ሁኔ ታን ይፈጥርላቸዋል:: በዚህ መን ገድ በርካታ መሰል ሥራዎችን እንደ ምታቀርቡልን ተስፋ አደርጋለሁ::

*መ/ር ብርሃኑ ድጋፌ*
*ባሌ ወረቃ*

## ቢታሰብበት

በሐመር መጽሔት 11ኛ ዓመት ቁጥር አምስት ላይ «የን ስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት» በሚል ርእስ በትምህርተ ሃይማኖት ዓምድ በዶ/ር መስፍን ተገኝ ከቀረበው ጽሑፍ በጣም የምፈልገውን ነገር አ ግኝቻለሁ:: ከዚህም ጋር ደግሞ በው ስጤ በእጅጉ የማዝንባቸው ነገ ሮች አሉ:: እኒህም የነፍስ አባቶች ወደ ልጆቻቸው ቤት ሄደው ያለ መጠየቃቸው እንዲሁም የንስሐ ልጆ ቻቸውን ቁጥር ያለ መወሰናቸው ናቸው:: በመሆኑም ቤተ ክርስ ቲያናችንም ሆነች የጽሑፉ አቅራቢ ለአበው ካህናት እኒህን ነገሮች በየጊዜ ው ከማ ሳወቅ አንጻር ቢያስቡበት መልካም ነው እላለሁ::

*ፍቅርተ ሚካኤል*
*አዲስ አበባ*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## የሚበረታታ ነው

በሚዛን ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አባቶቻችን ካህናት ለንስሐ ልጆቻቸው በየዓመቱ የሚገናኙበትን የጊዜ ሰሌዳ በዚህም ልጆቻቸው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፣ሥርዓትና ትውፊት ተኮትኩተው እንዲያድጉ እየተደረገ ያለው ጥረትና የእርስ በእርስ ምክክር የሚበረታታ ነው:: በከፋ ሸካና ቤንች ማጂ አገረ ስብከት ሥር በርካታ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ስለሚገኙበት የሚዛኗን ደብረ ገነት ቅድስት ማርያም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ ሌሎች አካባቢዎችም ቢያጤኑት በአባቶቻችን እግር ሥር ተገኝተን በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ጸንተን እንድንኖር ያደርገናል እላለሁ::

*ሰሎሞን አበበ*
*ሚዛን ደ/ገ/ቅድስት ማርያም ሰንበት ት/ቤት*
*መ/ር ኤልያስ ሰብስቤ*
*ሰሜን ምዕ.ሸዋ-ሰላሌ*

## አካሄዳችን ቢታገዝ

በክልል ስድስት ጠረፋማ አካባቢ ሆሞሻ ከምትባል ወረዳ ለእንጀራ ፍለጋ ከተለያዩ ክልሎች የተሰባሰብን ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች እየተወያየን በእግዚአብሔር ፈቃድ ጸሎታችንን የምናደርስባት አንዲት በሣር የተሠራ ጸሎት ቤት ነበረችን:: ከዚህች አነስተኛ ቤተ ጸሎት ተነሥተን የቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት በማሰብ ኮሚቴ አቋቁመናል:: የኮሚቴዎቹ አባላት ራሳችንን አስቀድመን የተለያዩ ጥረቶች እያደረግን ነው:: በመሆኑም በጥሩ ሁኔታ ላይ ለሚገኘው አካሄዳችን በጎ አድራጊ ወገኖች እገዛ እንዲያደርጉልን መልእክታችንን አስተላልፉልን::

*ሀብታሙ በላይ*
*ክልል ስድስት ሆሞሻ ወረዳ*

## መፍትሔ ሹ

በሰሜን ሸዋ አገረ ስብከት በሂጳቡ አቦቴ ወረዳ ውስጥ ልዩ ስሙ ቃሪቦ በሚባል ቦታ የሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ካበቃ በኋላ ጽሌው ሳይገባበት እስከ አሁን ድረስ አለ:: በአሁኑ ጊዜ ጽሌው በመንበረ ክብሩ መቀመጥ ሲገባው ያለው በግለሰብ ቤት ነው:: እባካችሁ የሚመለከተው አካል መፍትሔ ይፈልግለት ዘንድ ይህን ማሳሰቢያዬን አስተላልፉልኝ::

*ወለተ ማርያም*
*ኩዩ*

## እኛ ያላከበርነውን

ቅዱሳት ሥዕላት ያለ አግባብ በየሜዳውና በየሱቁ ዕቃ እየተጠቀለለባቸው፥ አልባሌ ቦታ እየወደቁ ስለ መሆኑ በዚህ መጽሔት በተደጋጋሚ ተጠቅሷል:: በተለይ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተያዘው ፈሊጥ ለሙታን የ40 ቀን መታሰቢያ በሚታተም ካርድ ላይ ከፊት ለፊት የሟች ፎቶ፥ ከጀርባ ደግሞ «ምስለ ፍቁር ወልዳ» የእመቤታችን ሥዕል ተደርጐ ይዘጋጃል:: የመታሰቢያው ቀን ካለፈ በኋላ እንደ አልባሌ የትም ይጣላል:: ለመሆኑ እኛ ያላ ከበርነውን ማን ሊያከብርልን ይሆን? በእውነቱ ሁላችንም ልናስብበት ይገባል::

*ውብ ዓለም ውብሸት*
*አዲስ አበባ*

## የራቁትንም እናቅርባቸው

በተለያዩ ማኅበራት ተሰብስቦ ቅዱሳንን ማዘከር ክርስቲናያዊ ሥርዓትና ትውፊት ነው:: ወርኃዊና ዓመታዊ በዓላትንም እናከብራለን:: በተ ለይም በዓመታዊ በዓላችን የትም ሀርትና የመዝሙር ዝግጅቶችን በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ቅርበት ያላቸውን ሰዎች ብቻ እንጋብዛለን:: ይህ መልካም ሆኖ ሳለ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንዳች ወይም እምብዛም የማያውቁትን፥ በተለያየ ምክንያት የራቁትንም ወንድሞችና እኅቶች በአጋጣሚው ተጠቅሞ የማቅረብ ጥረት ሊኖረን ይገባል እላለሁ::

*አዜብ አሰፋ*
*ደቡብ ወሎ ፥ውጫሌ*

ከዚህ በታች የተዘረዘራችሁ አንባብያን ገንቢ አስተያየቶችሁንና ጥቆማችሁን የያዙ ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: ለተሳትፎአችሁ እያመሰገን ወደፊትም በተመሳሳይ ሁኔታ አትለዩን እንላለን::

ደነቀው ነጋ /ባሕር ዳር/፣ ትዕግሥት ደሳለኝ፣/ካይሮ/፣ዲያቆን ፋንቱ ድንቁ /እምድብር/፣ ዶ/ር ወልደ ጊዮርጊስ /ምሥ.ጎጃም/ ፣መ/ር ብርሃኑ ታደሰ /ጂንካ/፣ሰይፈ ገብርኤል፣ ኃይለ ገብርኤልና ኃይለ ሚካኤል /ክብረ መንግሥት/፣ዲያቆን አያና ሙሉጌታ /ምዕ. ወለጋ/፣እንግዳ መሰለ /ጌድኦ ዞን/፣ በላይነህ መሰለ /አሰበ ተፈሪ/፣ ግርማ ፋንታ /ባሌ ዞን/፣ይድነቃቸው መኮንን፣ እስክንድር አበበ፣ዐቢይ ማራኬ፣ወልደ ኢየሱስ /አዲስ አበባ/፤ ሰሎሞን ዓባይ ፥ አዜብ አበጁ ፣ድይትሮት-አሜሪካ/፣አሰገደች እሸቱ /ዱባይ/፤ዲያቆን ክንፈ ሚካኤል ሞገስ /አርሲ-ሣጉሬ/፣ታሪኩ መኮንን/ብቸና/፣ ኃይለ ኢየሱስ/ወንጂ-ገፈርሳ/፣ አስታጥቃቸው ወልደ ጊዮርጊስ /ወልቂጤ/፣ ሜላት መዘምር/ገርበ ጉራቻ/፣ አንተነህ ጌታቸው/ደቡብ ወሎ-ደብረ ሲና/፣ የሺጥላ ኃይሉ/አዴት/፣አምኃ ደስታ/ዩ. ኤስ. ኤ/፣ስንታየሁ ጋሹ /አ.አ/፣መስተዋት ተክለ ወልድ /አ.አ/፣መሰለ ዓለሙ/አ.አ/፣ ሰሎሞን ጌታቸው/ነቀምት/፣ተገኝ ቀጸላ/ መካኒሳ/፣አምሳሉ ለሜሣ/አ.አ. ዩ/፣ አንዱ ዓለም መንገሻ /በበቃ/፣ዲ.ተወልደ ዱባለ/አ.አ/፣ዋሲሁን በላይ /ነቀምት/፣ ዲ.ወንድማገኝ ታደሰ/ ከፋ/፣በቀለ ከተማ/ሰሜን ሸዋ/፣ዳንኤል እጥፍ ወርቅ/ጎንደር/፣መ/ር አሸናፊ ስለሺ/ባሌ-ጊንር/፣ዲ.መላኩ ተመስገን/አረካ/፣አስቻለው ዓምዱ/አርሲ-በቆጂ/፣ ቢንያም ግርማይ/መቐለ/፣መርዓዊ/አጋሮ/፣ይትባረክ ደርቤ /ዱብቲ/፣ታፈረ ታደሰ /አርባ ምንጭ/፣ይታየው ታገለ፣ መለሰ መልኩ/ውቅሮ እርሻ ኮሌጅ/፣ደስታው ባየ/ወረታ እርሻ ኮሌጅ/፣ ግርማ ጌትነት፣ተማሪ ገብረ ሚካኤል/ ጎፋ ወረዳ/፣ደረጀ ዓሊ/ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ/ምትኩ ተስፋዬ /አ.አ./ ኃይለ ጊዮርጊስ/ናይሮቢ/፣ወታደር ምስጋናን አጠና/መቐለ፤/ጌትነት መኳንንት/ትክል ደንጊያ/፣ዲያቆን ቡሩክ ሸዋ ታጠቅ / ሚዛን ተፈሪ/ ፣ጎሩይ ውቤ/አ.አ/ ፣አስካለ ማርያም የሻው/ጎንደር/፣ግርማ ጌትነት/ደብረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን/፣ ገብረ ሚካኤል/ ሣውላ/፣ኃይለ ኢየሱስ መርሻ/ ደብረ ሲና/፣ሙሉጌታ አበበ/በደሌሣ/ ፣ ዘበናይ አሰፋ፣ መሠረት /ቤሩት/፣ እንዳልካቸው ገላዬ/ነቀምት/፣ አዲሱ አር ጋውና ድንበሩ ደሳለኝ /ምዕ.ሐረርጌ/፣ኃይለ ሚካኤል/አ.አ/፣ሣራ ተሥሃለ/ኢጣልያ/፣ ወልደ ትንሣኤ ጥላሁን (ፓዌ)፣ እንዳልካቸው ገላዬ/5ኛ ክፍለ ጦር-ነቀምት/:: ብሥራተ ገብርኤል /ሀገረ ሰላም/፤ ሣህሌ ተስፋዬ /አ.አ/ ካሣው ዋለልኝ /ደቡብ ወሎ ወግዲ/፤ ሲስተር ፀሐይ ዐይተነው /ባሌ-ሮቤ/፤ ሙሉ ጌታ ዓለማየሁ /ሰቆጣ/፤ገነት ብርሃኑ /እ.መ.ብ.ቅ.ማ.መ.ድ ሰ/ት/ቤት፣ ዘላለም ታምራት /አላባ/::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሰሙነ ሕማማት

/መምህር ኃይለ ማርያም ላቀው

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከትንሣኤ በፊት ያለውን አንድ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት /የሕማማት ሳምንት/ በማለት ትዘክረዋለች:: ሕማማት የሚለው ቃል «ሐመ፤ ታመመ» ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማሙና ሞቱ የሚዘከርበት ሳምንት ነው:: በሌላም በኩል ይህ ሳምንት ከአዳም እስከ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነበሩ ነፍሳት በሲኦል የቆዩበት የአምስት ሺህ አምስት መቶ የመከራ፣ የፍዳና የኩነኔ ዘመን መታሰቢያ ስለሆነ የሕማማት ሳምንት የሚለውን ስያሜ አግኝቷል:: እንደዚሁም ይህ ሳምንት «ቅዱስ ሳምንት» ይባላል:: ከሌሎች ሳምንቶች ሁሉ የተለየ የከበረ ነውና:: ምክንያቱም በዚህ ሳምንት በእያንዳንዱ ዕለት ስለ ፍጹም ፍቅር የተከፈለ የመሥዋዕትነት ሥራ ስለ ተሠራበት፣ የሰው ልጆች ደኅንነት ስለ ተፈጸመበት፣ መድኃኔ ዓለም ስለ እኛ ቤዛ ሆኖ ለመስቀል ሞት ታዛዥ ሆኖ ነፍሱን ስለ ካሠልን «ቅዱስ ሳምንት» ተብሏል:: በተጨማሪም «የመጨረሻ ሳምንት» ተብሎ ይጠራል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሙዓለ ሥጋዌው ለፈጸማቸው የቤዛነትና የአርአያነት ተግባራት ፍጻሜ በመሆኑ ነው::

በዚህ ልዩ በሆነ ሳምንት ካህናትና ምእመናን በነግህ፣ በሠልስት፣ በቀትር በተሰዓትና በሠርክ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመጓዝ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል የሚያዘክረውን ምዕራፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት በማንበብና በመጸለይ ሕማሙንና ሞቱን ያዘክራሉ፤ ቅዱስ ያሬድ በመጨረሻው ሳምንት በየዕለቱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተፈጸመውን ነገረ መስቀል በተመለከተ ያዘጋጀውን መዝሙር ይዘምራሉ፤ አብዝተው ስግደትን ይሰግዳሉ::

ሰሙነ ሕማማትን ከሌሎች የዐቢይ ጾም ሳምንታት ልዩ የሚያደርገው ሥርዓት አለ:: በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓትና ደንብ መሠረት በሰሙነ ሕማማት ከጸሎተ ሐሙስ በስተቀር ቅዳሴ አይቀደስም፣ ስብሐተ ነግህ አይደረስም፣ ጸሎተ ፍትሐት አይጸለይም፣ ጸሎተ አስተስርዮም አይደረግም:: እንዲሁም ጥምቀተ ክርስትናም አይፈጸምም:: ከላይ የተዘረዘሩት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አስቀድሞ በዕለተ ሆሳዕና ይከናወናሉ::

በተጨማሪም ማንኛውም ክብረ በዓል በዚህ ሳምንት ቢውል ከትንሣኤ በኋላ እንዲከበር ይተላለፋል:: ይህ ብያኔ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የጸና ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓት ነው::

ሕማምና ሞት የማይገባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሕማምና ሞት ለራሱ በማድረግ በዚህ ሳምንት ለእኛ ቤዛ ሆኗል:: «ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ፤ ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጠረ:: እርሱ ግን ግፍን አላደረገም ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም::» /ኢሳ.53÷4-12/ ተብሎ እንደ ተጻፈ:: ምእመናን ክርስቶስ የተቀበለው የእኛን ሕማም መሆኑን በማዘከር በሰሙነ ሕማማት ከማንኛውም የሥጋ ሥራ መታቀብ በዋዛ በፈዛዛ ባለመነጋገር በኀዘን ልናከብረው ይገባል፤ ብድራትን የማያስቀረው አምላክም መተላለፋችንና በደላችንን በመደምሰስ የመንግሥቱ ወራሽ ያደርገናልና::

ሰሙነ ሕማማት እስከ አራተኛው ምዕተ ዓመት ድረስ ከጾሙ ተለይቶ ለብቻው ይከበር ነበር:: በኋላ ግን በባሕረ ሐሳብ ቀመር መሠረት ጾሙም ሕማማቱም ትንሣኤውም ተያይዘው እንዲከበሩ ተደረገ:: ምዕራባውያን ከአርባ ጾም ውስጥ የመጨረሻውን ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ያደርጉታል:: የምሥራቃውያን /ኦሪየንታል/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ግን አርባውን ጾም ጨርሰን ከኒቆዲሞስ በኋላ ያለውን ተከታዩን አንድ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት አድርገን እናከብራለን::

በእነዚህ የሕማማት ሳምንት ውስጥ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየዕለቱ ያከናወናቸውን የድኅነት ሥራዎች እንደሚከተሉት ናቸው::

**እሑድ - ሆሳዕና፡-** ሆሳዕና የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «ሆሼዕናህ» የሚል ሲሆን ትርጉሙም «እባክህ አሁን አድን» ማለት ነው:: ይህ ቃል በዘመነ ብሉይ በቀደምት ነቢያት ዘንድ የተለመደ ቃል ነው:: «አቤቱ እባክህ አሁን አድን፤ አቤቱ እባክህ አሁን አቅና፤ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው::» መዝ.117፥25-26:: የሆሳዕና በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ጀርባ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የሚቀድሙትና የሚከተሉት ሕዝብ በተለይም አእሩግና ሕፃናት «ሆሳዕና ለዳዊት ልጅ÷ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሳዕና በአርያም» በማለት ጌታችንን በክብር መቀበላቸው የሚታወስበት በዓል ነው:: በዓሉም ሆሳዕና የሚለውን ስያሜ ያገኘው በዕለቱ ከተዘመረው መዝሙር ነው::

በሌላ አነጋገር ይህ ዕለት «የጸበርት እሑድ» /Palm Sunday/ ይባላል:: ታሪካዊ አመጣጡ የመልካም ምኞት እና የድል አድራጊነት መገለጫ ሁኖ ከደገኛው አባታችን ይስሐቅ ልደት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው:: ይኸውም መካኒቱ ሣራ የወላድነት ዕድሜዋን ጨርሳ ልማደ አንስት ከተቋረጠባት በኋላ ሁሉን ቻይ የሆነ አምላክ ይስሐቅን በሰጣት ጊዜ፣ ዘመዶቿ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ የዘንባባ ዝንጣፊ በመያዝ የኀበኛ ትን አምላክ አመስግነዋል:: እስራኤል ከአስከፊው የግብፃውያን አገዛዝ ተላቀው ባሕረ ኤርትራን በደረቅ ሲሻገሩ የተሰማቸውን እጥፍ ድርብ ደስታ በገለጡ ጊዜ እንዲሁም ዮዲት የተባለች ንግሥተ እስራኤል ሆሎፎርኒስ የተባለ አላዊ ንጉሥን ድል ባደረገች ጊዜ ቤተ እስራኤል እንደ ሰንደቅ ዓላማ የዘንባባ ዝንጣፊ በመያዝ አደባባይ ወጥተው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል::

በዘመነ ሐዲስም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር ከዲያብሎስ ቁራኝነት ከሲኦል ባርነት ነጻ ለማውጣት ወደ ዙፋን መስቀሉ /ሉቃ. 22÷18/ በተጓዘ ጊዜ ሕፃናት እና አእሩግ ነጻ የሚወጡበት ቀን መድረሱን እነርሱ ሳያውቁ እግዚአብሔር ባወቀ ዘንባባ በመያዝ ዘምረዋል:: እስራኤል ዘንባባ በመያዝ እንዳመሰገኑት እኛም እስራኤል ዘነፍስ ዕለቱን ዘንባባ /ጸበርት/ በግንባራችን በማሰር በዓሉን በየዓመቱ እያስታወስን እናከብራለን:: በዚህ ዕለት ዘንባባ እየተባረከ ለሕዝቡ ይታደላል::

ሕፃናትና አእሩግ «ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መባል ይገባዋል» እያሉ ዘምረዋል:: ይህ ሁሉ በአንድ ወገን የነበረው የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ሲሆን በሌላ በኩል የነበረው አቀባበል ደግሞ እጅግ የሚያሳዝን ነበር:: ሥርዓተ ኦሪትን ትንቢተ ነቢያትን በሚገባ እንከታተላለን ይሉ የነበሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን «መምህር ሆይ÷ ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው» አሉት:: ጌታችንም መልሶ «እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ» ሲል መልሶላቸዋል:: ቅናት አቅላቸውን ያሳጣቸው ፈሪሳውያንም የዋህ የኾነውን ሕዝብ ምስጋና ወደ ጥላቻ እንዲለወጥ አድርገዋል:: ከሁሉ የሚያሳዝነው በዕለተ ሆሳዕና እሑድ ዘንባባ ይዘው የዘመሩለትን ጌታ ዓርብ «ይሰቀል ዘንድ ይገባል» ብለዋል::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ጀርባ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ:: በዚህም በነቢዩ ዘካርያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ:: «እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፤ በአህያዪቱ ግልገል በውርጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል::» ዘካ.9፥9፤ ማቴ.21፥4፤ማር.11፥1-10፤ሉቃ. 19፥28-40፤ ዮሐ.12፥15:: ጌታችን በአህያ ጀርባ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ የሰላም ንጉሥ መሆኑን ያመለክታል:: እስራኤል ዘመነ ምሕረት ሲሆንላቸው አባቶቻቸው በአህያ ጀርባ ተቀምጠው ይታዩ ነበር:: ጌታም እውነተኛ የኀሊና ሰላም ይገኝላችሁ መጣሁ ሲለን በአህያ ጀርባ ወደ ቤተ መቅደስ ሕይወታችን ተጉዟል::

መላእክት በዕለተ ልደቱ «በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል በምድር ሰላም ለሰው ሁሉ ይሁን» /ሉቃ. 2፥13/ እያሉ የዘመሩለት የሰላም ባለቤት ነው:: በመዋዕለ ትምህርቱም «ሰላሜን እሰጣችኋለሁ» /ዮሐ.14፥27/ ብሎ እንዳስተማረ ያን ሰላም የሚሰጥበት ዕለት መቅረቡን ለማመልከት ነው:: በሌላ በኩልም በአህያ ጀርባ መቀመጡ ኀቡዕ ምሥጢር አለው:: በአህያ ጀርባ የተቀመጠ ሰው ሌላውን አሳድዶ አይዝም፤ እርሱም ሮጦ አያመልጥም:: በዚህም ጌታችን በእምነት ለሚፈልጉት የሚገኝ ቅርብ ሲሆን በእምነት ለማይፈልጉት ግን የማይገኝ መሆኑን አስተምሯል:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ፀሐይ ዕድሜያችን ሳትጠልቅ በእምነት እንፈልገው:: አሞጽ 4፥4:: የአህያን ጀርባ ያልናቀ ጌታችን ትሑት ሰብእና እና የተሰበረ ልቡና ወዳለው ሰው ዘወትር ይጓዛል እንጂ የተዋረደውንና የተሰበረውን ልብ አይንቅም:: ኢሳ. 66፥2፤መዝ.50÷17::

ለታሰሩት መፈታትን ሊሰብክ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሰው የሆነ ጌታችን ከማሰሪያዋ በተፈታች አህያ እንደ ተቀመጠ ሁሉ ከኃጢአት እስራት በተፈታ ሕይወት ዛሬም ያድራል፤ የኅሊና ሰላምን ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ንስሐ ገብተን ጌታችንን ሆሳዕና በአርያም እያልን ልናመሰግነው ይገባል፡፡

## ሰኞ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ዓለም ሲመላለስ በሆሳዕና ማግሥት ጌታችን ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሁለት ነገሮችን አድርጓል፡፡ አንደኛ ከቅጠል በስተቀር ፍሬ ያልተገኘባትን ዕፀ በለስ ረግሟል፡፡ ሁለተኛ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን አስወጥቷል፡፡ ማቴ.21÷12-17፤ማር.11÷17፤ሉቃ.19÷45-46፡፡ በቅዱስ ማቴዎስ አገላለጥ «በማግሥቱ ተራበ» የሚል ቃል እንመለከታለን፡፡

«ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ለዘላለም አይራብም፤ አይጠማም፤ አይደክምም» /ኢሳ.46፥25/ ይላል፡፡ በቅዱስ ወንጌልም «በመጀመሪያ ቃል ነበር፡፡» ብሏል፡፡ ያ ቃል ቀዳማዊ እንደ ሆነ፣ ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ነበር፣ ያም ቃል እግዚአብሔር ነው ተብሎ ተጽፏል፡፡ ዮሐ.1፥1-2፡፡ ጌታችንም በመዋዕለ ትምህርቱም ሲያስተምር «የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው» /ዮሐ.4÷35/ ሲል ተናግሯል፡፡ ነቢዩ እግዚአብሔር እንደሚይራብ ተናግሯል፡፡ ታድያ ጌታችን ለምን ተራበ?

ሰማያውያን መላእክት እንዳይራቡ አድርጎ የፈጠረ፣ እስራኤልን ገበሬ በማያርስበት፣ ዘር በሌለበት ዝናብ በማይጥልበት ምድረ በዳ የመገበ ድኅረ ሥጋዌ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ ከ5000 የሚበልጡ ሰዎችን የመገበ ተራበ! ተብሎ ሲነገር እጅግ ይደንቃል፡፡ በእርግጥ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው በመሆኑ አልተራበም አንልም፡፡ የጌታችን ረሃብ ንዴት ያለበትና የአንዲት የበለስ ዘለላ ረሃብ አይደለም፡፡ ረሃቡ የበለስ ፍሬ ሳይሆን «በለስ ብሂል ቤተ እስራኤል እሙንቱ» እንዲል የበለስ ውክልና ከተሰጣቸው ቤተ እስራኤል የሃይማኖትና የመልካም ሥነ ምግባርን ፍሬ የሻ መሆኑን ለማጠየቅ ነው፡፡ ጌታችን የፈለገውን ባለማግኘቱ ጉባኤ አይሁድን ረግሟል፡፡ በአይሁድ ጉባኤ የነገሠውን ኃጢአት፤ በበለስ አንጻር መርገሙን ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «በአንጻረ በለስ ረገማ ለኃጢአት፤ በበለስ አንጻር ኃጢአትን ረገማት» ብሏል፡፡

እስራኤልም በአንድ ወገን የተጠበቀባቸውን ፍሬ ባለማፍራታቸው ተረግመዋል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ እስራኤል ከፍቅር ይልቅ እርግማን እንዳገኛቸው አሕዛብ ደግሞ የቃሉን ትምህርት ሰምተው የእጁን ተአምራት ዐይተው የአመኑበትን የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ ለመሆን መብቃታቸውን ሲመሰክር እንዲህ ይላል፡- «አሕዛብ አስተጋብኡ ጽጌሬዳ በሒሩቱ ወሶኩስ ተርፈ ኀበ አይሁድ ዘውእቱ ሕፀተ ሃይማኖት፤ አሕዛብ በእግዚአብሔር ቸርነት አበባ ሰበሰቡ፤ በአይሁድ ዘንድ ግን እሾኹ ተረፈ፡፡ ይኸውም የሃይማኖት ጉድለት ነው፡፡» ብሎ ተርጉሞታል፡፡ እሾኽ የእርግማን ምሳሌ ነው፤ አበባ የእግዚአብሔር ጸጋ ልጅነት ምሳሌ ነው፡፡ ዛሬ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ጌታችን ወደ መቅደስ ሕይወታችን ቢመጣ ምን ያገኝ ይሆን? ፍሬ ወይስ ቅጠል? የእግዚአብሔር ቃል ግን ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ ይለናል፡፡ ማቴ.3፥8፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ እናፍራ፡፡ ገላ.5፥22፡፡ ጌታችን በዳግም ልደት ሲመጣ ከሰው ልጅ ሃይማኖት መገኘቱ አጠ ራጣሪ እንደ ሆነ ተናግሯል፡፡ «የሰው ልጅ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ሃይማኖት ያገኝ ይሆንን?» ቀጣይ ሕይወታችንን በአምላካዊ ሥልጣኑ የቃኘ አምላክ በመጣ ጊዜ የእምነት ፍሬ አፍርተን ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለ ማዊ ፍቅሩን ለማትረፍ እንትጋ፡፡

## ማክሰኞ

በዚህ ዕለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሥልጣኑ ተጠይቋል፡፡ ጠያቂዎቹ የካህናት አለቆችና የሕዝብ አለቆች ናቸው፡፡ ጥያቄውም «በማን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን የሰጠህ ማነው?» የሚል ነበር፡፡ የካህናት አለቆች ያቀረቡት ጥያቄ ረቡዕ ዕለት ለሚወስኑት ይሙት በቃ ፍርድ መንደርደሪያ የሚሆን የፈተና ጥያቄ ነበር፡፡ ጌታችን ሰኞ ዕለት ሁለት ነገሮችን ማድረጉን ተያይዞ የተነሣ ጥያቄ ነው፡፡ ሰኞ ከቅጠል ብቻ በቀር ፍሬ ያላገኘባትን ዕፀ በለስ ረግሟል፤ በማስከተል ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ የሚሸጡትንና የሚለውጡትን አስወጥቷል፡፡ ማቴ.21፥23-25፤ ማር.11፥27፣ ሉቃ.20፥1-8፡፡ ከላይ እንደ ተገለጸው ጌታችን ሲያደርጋቸው የነበሩት ተአምራትና የኃይል ሥራዎች የካህናት አለቆችን ስላስቀናቸው ጌታችንን ከሮማ መንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር ለማጋጨት የቀየሱት ስልት ነው፡፡

ጌታችን በቤተ መቅደስ የነበሩትን ነጋዴዎችን አባሯል፤ መደባቸውን ገለባብጧል፡፡ ነጋዴን ማባረርና መደብን ማስለቀቅ መንግሥታዊ ሥራ ነው፡፡ በአንድ አገር የንግድ ቦታን የሚያጸድቅ መንግሥት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ጌታችን ፈሪሳውያን ላቀረቡት ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ አልመለሰም፡፡ ምክንያቱም ጥያቄው ለከሳሾቹ አመቺ ሁኔታን ስለ ሚፈጥር ጥያቄውን በጥያቄ መልሷል፡፡ «በምባሕተ መኑ ትገብር ዘንተ፤ በማን ሥልጣን ነው ይህን የምታደርገው?» ነበር ያሉት፡፡ በራሴ ሥልጣን ቢላቸው ፀረ መንግሥት አቋም አለው በማለት ከሮማ መንግሥት ዘንድ ለማሳጣት ነበር ዕቅዳቸው፡፡

ጌታችን እኩይ የሆነውን የፈሪሳውያንን አሳብ በመረዳት «የዮሐንስ ጥምቀት ከየት ነው ከሰማይ ነው ወይስ ከምድር ሲል» ጠይቋቸዋል፡፡ ከሰማይ ያልነው እንደ ሆነ ለምን አላመናችሁበትም ይለናል፥ ከሰው ያልነው ከሆነ ሕዝቡ ይጣላናል፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ ዮሐንስን እንደ አባት ይፈሩት እንደ መምህር ያከብሩት ነበርና ከዚህ የተነሣ ያቀረቡት የፈተና ጥያቄ ግቡን ሳይመታ ከሽፎባቸዋል፡፡ ማቴ.21÷25፤ማር.11÷27-30፤ሉቃ.20÷1-8፡፡

ዛሬም ቢሆን መልካም ሥራን በሠራን ጊዜ ከልዩ ልዩ ወገኖች የሚመጡ ፈተናዎች ለመልካም ሥራችን እንቅፋት ሊሆን እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን፡፡ ብዙ ወገኖች ለቅን አሳባችን ለምን ሰዎች ክፉ ነገር ይመልሱልናል በማለት ሲጠይቁ ይሰማል፡፡ ለቅን አሳባችን ከዓለም ዘንድ የተገላቢጦሽ ነገር እንደ ሚጠብቀን «ዓለም የሚወደው የገዛ ወገኑን ነው» የሚለውን የጌታችንን ትምህርት ልብ ይሏል፡፡ ይህ በመሆኑ በዘመናችን አሳልፈው ሊሰጡን የሚፈልጉ ሰዎች ተፈታታኝ ጥያቄ እንደሚያቀርቡልን ከወዲሁ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

## ረቡዕ

በቅዱስ ማቴዎስና በቅዱስ ማርቆስ አዘጋገብ መሠረት ሦስት ነገሮች ተደርገዋል፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1/ የካህናት አለቆች÷ የሕዝብ ሽማግሌዎችና ጸሐፍት ፈሪሳውያን በጌታችን ላይ ተማክረዋል፤
2/ ጌታችን በስምዖን ዘለምጽ ቤት ሳለ አንዲት የተጸጸተች ሴት ሽቱ ቀብታዋለች፡፡
3/ ከዳተኛው ይሁዳ ጌታችንን አሳልፎ ለመስጠት ከጸሐፍት ፈሪሳውያንና ከካህናት አለቆች ዘንድ 30 ብር ተመዝኖለታል፡፡

የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሹማምንት በጌታችን ላይ ይሙት በቃ ለመወሰን የሰበሰቡት ሸንጎ «ሲኒሃ ድርየም» ይባላል፡፡ በዚህ ሸንጐ ላይ በአብዛኛው የተሰየሙት ሰዱቃውያን ሲሆኑ የተቀሩቱ ደግሞ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ነበሩ፡፡ ሸንጐው በአጠቃላይ 72 አባላት የነበሩት ሲሆን የሚመራው በሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ነበር፡፡

በዕለቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት ይዘው እንደ ሚገድሉት መክረዋል፡፡ ከዳተኛው ይሁዳ በጸሐፍት ፈሪሳውያንና በካህናት አለቆች ዘንድ ይጉላላ የነበረውን ጥላቻ ያውቁ ስለነበር «ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ» በማለት ጌታችንን አሳልፎ ሊሰጣቸው እንደሚችል ተዋውሏል፡፡ የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታችን ያስተምር በነበረበት ወቅት ከተለያዩ ሰዎች የሚገባውን ገንዘብ ሰብሳቢ /ዐቃቤ ንዋይ/ ነበር፡፡ ከሚሰበሰው ሙዳየ ምጽዋት ለግል ጥቅሙ እየቀረጠ የማስቀረት የእጅ አመል ነበረበት፡፡ ይሁዳ ፍቅረ ንዋይ እንደ ሚያጠቃው ድብቅ አመሉ ጉልቶ የወጣው ጌታችን በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው ውድ የሆነ ሽቱ በቀባችው ወቅት ነበር፡፡ ሴቲቱ ሽቱውን በቀባችው ጊዜ ይሁዳ የተቃውሞ ድምፅ ካሰሙት አንዱ ነበር፡፡ «ይህ ሽቱ ተሸጦ ለድሆች ቢሰጥ መልካም ነበር» በማለት ያቀረበው አሳብ «አዛኝ መሳይ ቅቤ አንጓች» እንደ ሚባለው ነበር፡፡ ሽቱ ቢሸጥ የሚያገኘው ጥቅም አለ፤ ሽቶ ከፈሰሰ የሚተርፈው የለም፡፡ ይህ በመሆኑ ተቆርቋሪ መስሎ ያቀረበው አሳብ ተቀባይነት ስላጣ ማኩረፊያ ያገኘ መስሎት በቀጥታ ከካህናት አለቆች ዘንድ ሄዶ ተዋዋለ፡፡ ብር 30 ተመዘነለት፡፡ ይህ አሳዛኝ ታሪክ በሦስቱ ወንጌላት ውስጥ በሚከተሉት ጥቅሶች ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ማቴ. 26÷3–16፤ ማር.14÷1–11፤ሉቃ 22÷1–6 ይመልከቱ፡፡

የአስቆሮቱ ይሁዳ እንደ ሌሎች ሐዋርያት ከጌታችን እግር ስር ተምሯል፡፡ በረከተ ኀብስቱን ተመግቧል፡፡ የተለያዩ ገቢረ ተአምራት በጌታችን እጅ ሲደ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ረጉ ሁሉ ተመልክቷል:: ጌታችንም ከሌሎቹ ሁሉ ሳይለየው እግሩን አጥቦታል፤ ከዳተኛው ይሁዳ ግን ለሐዋርያት የጠራውን ተንበርክኮ እግሩን ያጠበውን ጌታውን አሳልፎ ሰጥቷል:: «የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል÷ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት እንደ ተባለ::» ማቴ.26÷24:: ሌሎች ሐዋርያት ከጌታችን ዘንድ ፍቅሩን ገንዘብ ሲያደርጉ ይሁዳ ግን እርግማንን ነው ያተረፈው:: «ገንዘብ የኃጢአት ስር ነው» ተብሎ እንደ ተነገረ ይህ የኃጢአት ስር የክርስቲያኖችን ሕይወት ሊያደርቅ ስለሚችል ለገንዘብ ያለን ፍቅር በልኩ ሊሆን ይገባል:: ሰው ይህን ዓለም ቢያተርፍ ነፍሱን ከጐዳ ምን ይጠቅመዋል ተብሎ የተነገረውን ቃል ልብ ማለት ጠቃሚ ነው::

ክርስቲያን ነን በማለት የክርስትናውን ስም በመያዝ እምነታቸውን፣ የቆሙበትን ዓላማ በመገንዘብ የሚለውጡ ሰዎች ዛሬም እንደ ይሁዳ ጌታችንን እየሸጡት እንደ ሆነ ሊገነዘቡ ይገባል:: ለድሆች መመጽወት ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው:: ዳሩ ግን በድሆች ስም የሰውን ገንዘብ ለግል ጥቅም ማዋል እጅግ የከፋ ኃጢአት ነው:: እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ለገንዘብ ብለው ድሆችን ለረሃብ ለችግር ባልንጀራቸውን ለመከራ እና ለሞት አሳልፈው ሲሰጡ ምንም አይጸጽታቸውም:: እውነተኛ ክርስቲያኖች ግን ሕይወታችንን ለገንዘብ ፍቅር ሳይሆን ለእምነታችንና ለባልንጀራችን አሳልፈን መስጠት ይኖርብናል:: በፍቅረ ንዋይ ተጠምደን ሰዎችን አሳልፎ በመስጠት ለአይሁዳዊ ሽንገላ ምቹ ሆነን መገኘት እንደሌለብን መገንዘብ አለብን::

## ኀሙስ

በዕለተ ኀሙስ «ለታወፅዖ ባሕር ዘቦ መንፈሰ ሕይወት፣ ውኃ ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾችን ታስገኝ» /ዘፍ.1÷20/ ባለ ጊዜ ለሥጋውያን ምግብ የሚሆኑ እንስሳትና አዕዋፍ ተፈጥረዋል:: ድኅረ ሥጋዌ የመንፈሳውያን ምግብ የሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለበረከት የመጣለትን ኅብስት ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት አድርጐ ለዘላለም የማያስርብና የማያስጠማ ምግበ ሕይወት ሥርዓተ ቁርባንን ሠርቶልናል::

በሕማማት ሳምንት ውስጥ ያለው ይህ ኀሙስ በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል::

1.ጸሎተ ኀሙስ ይባላል፤ ምክንያቱም:-
ሀ/ ጌታ ኅብስቱን በባረከ ጊዜ ስለ ጸለየ
ለ/ በዮሐ. 17 ላይ ያለውን ጸሎት ስለ ጸለየ
ሐ/ በጌቴ ሴማኒ ስለ ጸለየ ነው::

2.ትእዛዝ ኀሙስ ይባላል፤ ምክንያቱም:-
ሀ/ ከኅጽበተ እግር በኋላ ጌታ "እናንተም እንዲሁ አድርጉ " ብሎ ስለ አዘዘ
ለ/ በጌቴሴማኒ ጌታ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ ብሎ ስለ አዘዘ
ሐ/ ሥርዓተ ቁርባንን ከሠራ በኋላ "ከመዝ ግበሩ ተዝካርየ" ብሎ ስለ አዘዘ እንዲሁም በዚህ ዕለት የተሰጡትን ሌሎ ችንም ትእዛዝት ለማስታወስ ነው::

3. የነጻነት ኀሙስ ይባላል፤ ምክንያቱም "ከእንግዲህ ወዲህ ባሪያዎች አልላችሁም፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ" ያለውን የነጻነት ቃል ለማስታወስ ነው:: ዮሐ.15፥15፤ 1ጴጥ.2፥10::

4. ኅፅበተ ኀሙስ ይባላል፤ ምክንያቱም በዚህ ቀን ጌታ የደቀ መዛሙርቱን እግር ስለ አጠበ በአዘዘን መሠረት ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን መታሰቢያው ስለሚደረግ::

5. አረንጓዴው ኀሙስ ይባላል፤ ምክንያቱም በዚህ ቀን ጌታ በአትክልት ቦታ መጸለዩን የሚያስታውስ ስለሆነ::

6. የሐዲስ ኪዳን ኀሙስ ይባላል፤ በዚህ ቀን ምሽት ጌታ «ይህ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው» በማለት የሰጠንን ዘለዓለማዊ ኪዳን የሚያስታውስ ውሳኔ ነው:: ከዚህም ባሻገር መሥዋዕተ ብሉይን ሽሮ መሥዋዕተ ሐዲስንም ሠርቷል:: የተፈጸሙት ድርጊቶች በወንጌላት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል::
ሀ/ የፋሲካ ዝግጅት ተደረገ፤
ለ/ ጌታ ከቁርባን በኋላ ሥርዓተ ቁርባንን ሠራ፤
ሐ/ በዮሐንስ 17 ላይ ያለውን ረጅም ጸሎት ጸለየ፣ በጌቴሴማኒም ጸለየ፤
መ/ በዚህ ሌሊት ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ሰጠው፤ ወታደሮችም ያዙት:: እነዚህን የሚያስረዱ ጥቅሶች /ማቴ.26፥11-46፤ ማር.14፥12-52፤ ሉቃ.22፥1-53፤ ዮሐ. 18፥ 1-12/ ናቸው::
ሠ/ በዚህ ቀን ጌታ ፍጹም ትሕትናውን ለመግለጽ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፤ ዮሐ.13፥4-17::
ረ/ በዚህ ቀን ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ረጅም የማጠቃለያ ትምህርት አስተምሯል፤ ዮሐ.14፥16::

ይህ ቀን ጌታ በመዋዕለ ሥጋዌው ከሐዋርያት ጋር የነበረበት የመጨረሻው ቀን ነበር:: ስለዚህ በዕለቱ ያደረጋቸው ነገሮች ትዝታን የሚጥሉ ጌታም ለእኛ ያለውን ፍቅሩን የሚገልጹ ድርጊቶች ነበሩ፤ ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ይህንን ሲገልጽ «በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው ወደዳቸው» ብሎ ጽፏል:: ዮሐ.13፥1:: በእውነትም በዚህ ቀን እግር ማጠቡን፣ አማናዊ ሥጋውን ደሙን መስጠቱን፣ ከሐዋርያት ጋር መጸለዩን፣ የማጠቃለያ ትምህርት መስጠቱንና ስለ ሁላችን ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ስንመለከት የጌታን ጽኑ ፍቅሩን እንረዳለን::

እንግዲህ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለሰጠን ፍቅር ታላቅ ግምት ልንሰጠው ይገባል:: የፈጠረን አምላክ አፍቃሪ አምላክ በመሆኑ ፍቅሩ በእያንዳንዳችን ሕይወት መኖር አለበት:: በዚህኛውም ሆነ በወዲያኛው ዓለም እውነተኛ ደስታ ለማግኘት ማረጋገጫው ፍቅር ነው:: በፍቅር ላይ ያልተመሠረተ ሰብዓዊ ግንኙነት ሁሉ ትርጉም ሊኖረው አይችልም:: እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ የሚለው ትእዛዝ መሠረታዊ የተፈጥሮ ሕግ ከመሆኑም ባሻገር እንደ ምንተነፍሰው አየር የሚያስፈልገን አምላካዊ ስጦታ ስለሆነ እርስ በእርሳችን አጥብቀን እንዋደድ::

## ዓርብ

በዕለተ ዓርብ «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» ባለ ጊዜ /ዘፍ. 20÷21/ የፍጥረት ሁሉ ጉልላት የሆነ አዳም ተፈጥሯል:: በድኅረ ሥጋዌም ብኵረ ፍጥረታት አዳም[...] ለማዳን ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ በመስቀ[...] ላይ ውሏል::

በቤተ ክርስቲያናችን በሕማማ[...] ሳምንት ውስጥ ያለው ይህ ዓርብ የስቅለ[...] ዓርብ በመባል ይታወቃል:: ጌታችን ኢ[...]ሱስ ክርስቶስ ለዓለም ድኅነት በመስቀ[...] ላይ መሰቀሉ በቤተ ክርስቲያ[...] የሚታወስበት፣ የሚታሰብበት ዕለት ነው[...] በሌላ በኩል ጌታችን ወደ መቃብር እስ[...] ወርድ ድረስ በዚህ ዕለት በጌታ ላይ የ[...] ፈጸሙት ድርጊቶች በአራቱም ወንጌላት [...] መዝግበው እናገኛለን:: እነርሱም:-

1. በሊቀ ካህናቱ ፊት በሃይማኖታዊ ክ[...] በሐሰት አስመሰከሩበት፣
2. ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡትና በፖ[...]ቲካዊ ክስ በሐሰት አስመሰከሩበት፣
3. ጲላጦስ ወደ ገሊላው ገዥ ወደ ሄሮድ[...] ላከውና በዚያ ተጠየቀ፣
4. ሄሮድስ ንቆ ወደ ጲላጦስ መለሰው፤ ጲላጦስም መረመረው፣
5. ጲላጦስ በርባንን ፈርቶ ኢየሱስን ግ[...]ገርፎ ይሰቅሉት ዘንድ አሳልፎ ሰጣቸው፣
6. ፕራይቶሪዮን በሚባለው ግቢ [...] ልብስ አልብሰው የእሾኽ አክሊል ደፍተ[...]ው ዘንግ አስይዘው ዘበቱበት፣
7. መስቀሉን አሸክመው ሊሰቅሉት ወሰዱት፣
8. በስድስት ሰዓት ጎልጎታ /ቀራንዮ/ በተባለው የራስ ቅል ሥፍራ ቸንክረው በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት::
9. ልብሱን ለአራት ተከፋፈሉት፤ በእጀ ጠባቡም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፣
10. በመስቀል ላይ ሣለ ሰደቡት፣ ተፋበት፤ ሆምጣጤም አጠጡት ጎኑንም በጦር ወጉት::
11. በመስቀል ላይም ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከቆየ በኋላ ተሰቃይቶ ነፍሱን ስለ ሁላችን አሳልፎ ሰጠ::
12. ዮሴፍ ዘአርማትያስ እና ኒቆዲሞስ በአዲስ መቃብር ቀበሩት:: የስቅለቱ ታሪክ በአራቱም ወንጌላት እንደ ሚከተለው ተጽፏል:: ማቴ.26፥ 37፤ 27፥ 61፤ ማር.14፥53፤ 15፥45፤ ሉቃ.22፥ 54-56፤ ዮሐ.18፥12-42:: በቤተ ክርስቲያናችን የሚታወቁትና 13ቱ ሕማማተ መስቀል የሚባሉት:-

1ኛ. ተኰርአተ ርዕስ /ራሱን መመታቱ/
2ኛ. አክሊለ ሶክ/ የእሾኽ አክሊል ደፋበት/
3ኛ. ተአስሮ ድኅሪት/ የኋሊት መታሰር/
4ኛ. ስትየ ሐሞት/ሐሞት መጠጣት/
5ኛ. ቅንዋተ መስቀል/ዳናት፣አዴራ፣ሳዶር አላዶር፣ሮዳስ/
6ኛ. ተቀሥፎ ዘባን /ጀርባውን መመታቱ/
7ኛ. ርግዘተ ገቦ/ጎኑን መወጋቱ/
8ኛ. ተጸፍኦ መልታህት/ ፊቱን መመታቱ/ ማቴ.26.26::

ይህ ሁሉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የደረሰውን መከራና ሥቃይ ያስታወሰናል:: በፊታችን እንደ ተሰቀለ ሆኖ ጌታ እንዲሣል የሚያደርጉ ሕማማት ናቸው::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዕለት በመስቀል ላይ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በነበረበት ጊዜ ሰባት ተአምራት ተደርገዋል::

እነርሱም:-
1. ፀሐይ ጨለመች፤
2. ጨረቃ ደም ሆነች /መሰለች/፤
3. የቤተ መቅደስ

/ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

/ካለፈው የቀጠለ/

# የንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት

/ዶ/ር መስፍን ተገኝ/

ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች ተቋማት ልዩ የሚያደርጋት ያላት መዋቅራዊ አደረጃጀት ነው:: በተለይም እያንዳንዱን ሰው ለመጠበቅ፣ ለመከታተልና ለውጥ ለማምጣት በንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት ደረጃ:-

1. ያላት መንፈሳዊ ግንኙነት አስተማማኝ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችልና ከሌሎችም ተቋማት በአደረጃጀትና ከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ለመድረስ የተሻለች የሚያደርጋት ነው::

2. አንድን ሰው ለበጎ ሥራ የሚያነቃቃ፣ በመልካም ጠባይ ሕይወቱን የሚመራ ሲሆን ለመጥፎ ሥነ ምግባር አስተማሪ ካገኘም አውቆትም ይሁን ሳያውቅ የሚታለል ነው:: ስለዚህ የንስሓ አባት ሚና የንስሓ ልጅ ከግል እስከ ማኅበራዊ ሕይወት ሊያጋጥመው የሚችለውን ውጣ ውረድ ግምት ውስጥ በማስገባት መልካም ጠባዩ በክፉ ባልንጀሮች እንዳይለወጥ የሚያስችለውን ውስጣዊ መንፈሳዊ ጥንካሬ እንዲኖረው መርዳትን ሁሉ ያጠቃልላል:: ሰው ያየኛል ብሎ ሳይሆን እግዚአብሔር ያየኛል በማለት ሕይወቱን የሚመራ ምእመንን ማፍራትን ይጠይቃል:: ይህም የንስሓ አባት ጥንካሬና መልካም እረኛነት የሚታይበት ይሆናል::

በንስሐ አባትና ልጅ ግንኙነት ላይ መስተካከል የሚገባቸው ችግሮች ቢኖሩም ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን ማየቱ መፍትሔ ሊሆን ይችላል::

1ኛ. የአቀራረብ ችግር:- በንስሓ አባትና ልጅ መካከል ጎልቶ ከሚታዩ ችግሮች አንዱ የአቀራረብ ሁኔታ ነው:: አንድ የንስሓ አባት የንስሓ ልጁን እንዴት ነው የሚቀርበው? አንድ የንስሓ ልጅ የንስሓ አባቱን እንዴት ነው የሚቀርበው? በሁለቱም አቅጣጫ ያልተሟሉ ነገሮች መኖራቸው የድካም ፍሬውን ውጤታማነት አጠያያቂ ያደርገዋል:: ሰዎችን ወደ ንስሓ አባት እንዲመጡ የሚያደርጓቸው ሦስት ምክንያቶች ሲኖሩ ÷እነርሱም:-

ሀ/ ለበደልኩትና ለፈጸምኩት ኃጢአት ንስሓ ልግባ፤

ለ/ የተጨነቅሁበትን ጉዳይ በማካፈል ዕረፍት ባገኝ በማለትና

ሐ/ መንፈሳዊ ሕይወቴን በቀጣይነት እንዴት ላጠናክር ከሚል የተነሣ ሲሆን እነዚህን ነገሮች አስቦ የሚመጣ የንስሓ ልጅ ኃጢአቱንም እንዲናዘዝ የተጨነቀውን እንዲያካፍል ስለ መንፈሳዊ ዕድገቱ እንዲያስብ የንስሓ አባቱ አቀራረብ ወሳኝነት አለው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ እንደ ነገረን "መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል" ዮሐ. 10÷11፤ "በጎቹም ድምፁን ያውቃ ሉና ይከተሉታል፤ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም የሌላውን ድምፅ አያውቁምና::" ዮሐ.10÷4:: ይህ የሚያስረዳን በጎች የተባሉ ምእመናን የእረኞች ካህናትን ድምፅ የሚፈልጉትና የሚከተሉትም እንደ ሆነ ነው::

የእረኛው ድምፅ ለእነርሱ ተስፋና መጽናኛ ነው:: ሁል ጊዜም ራሱን አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ እነርሱን እንደ ሚወዳቸውና በፍቅር እንደ ሚቀርባቸው ስለ ሚያውቁ የእርሱን ቃል ከመስማት ወደ ኋላ አይሉም:: በዮሐ. 4÷1 ያለው ታሪክ የሚያስረዳንም በካህናት መንፈሳዊ አቀራረብ ምእመናን ከተደሰቱ እና ካመኑ የውስጣቸውን ሳይደብቁ እንደ ሚናገሩ የሚናገሯቸውን እንደ ሚሰሙ ከልባቸውም ቅርብ እንደሚሆኑ ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳምራዊቷን ሴት ሲቀርባት ምንም እንኳን አምላክነቱን ባታውቅ አክብሯት በትሕትና በመልካም አነጋገር አጽናኝ በሆነ ቃል ስለ ቀረባት በዚህ አቀራረብም ልቧ ስለ ተነካ ኃጢአቷን ሳትደብቅ ተናግራለች:: በትምህርቱም ተማርካ ሕይወቷን አስተካክላ ተከትላዋለች::

ይህንን ስንመለከት ከካህናት በኩል መስተካከል የሚገባው በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጠው የተጠሩበት ዓላማ ታላቅ መሆኑን መረዳት ነው:: ስለዚህም የብዙ ሰዎችን ሕይወት ለማዳን እንደ ሚችሉ ያስገነዝባል:: በንስሓ ልጅም በኩል የሚታዩ የአቀራረብ ችግሮች አሉ:: ለንስሓ አባታቸው የሚሰጡት ክብር፣ በራሳቸው ሊፈቱት የሚችሉት የመሰላቸውን ደብቀው በማስቀረት ደኅንነትን ከመጠያየቅ ባላለፈ መንገድ ተገናኝቶ መለያየት ከጥቅሙ ጉዳቱ እያመዘነ ይታያል:: አንድ የንስሓ ልጅ አባቱን ለማግኘት መቼ እንዴት ብሎ መለየት አለበት:: አለብኝ የሚሉትን ድክመት ለቅርብ ጓደኛቸው እየተናገሩ ለንስሓ አባታቸው ሌላ ነገርን የሚገልጡ አሉ:: እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የንስሓ አባት መያዛቸው መልካም ቢሆንም በአግባቡ ካልተጠቀሙበት እንደ ያዙ አይቆጠርም::

ምን የከፋ ነው የምንለውን ኃጢአት ብንሠራ መድኃኒቱ የሚገኘው ለንስሓ አባት ሲነገር ብቻ ነው:: ሌላ ጓደኛ ችግራችንን ሰምቶ ሊያጽናናን ይችል ይሆናል:: የበደልና የኃጢአት ስርየት ተገኝቶ ነጻ የሚሆነው ግን ለንስሓ አባት ሲገለጽ ብቻ ነው:: «አን ዳንድ ሰዎች በደላችንን ኃጢአታችንን ለንስሓ አባት መናገር ጨንቀን» የሚሉ አሉ:: በእርግጥ ይህ ሊከሰት ይችላል:: እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ግን መጨነቃችን ኃጢአት መፈጸም ምን ያህል ከባድ መሆኑን እንድናውቅና 'ከዚህ ስሕተት ተምረን እንድንተወው እንጂ ከዚህ አልፈን ተጨንቀን ተስፋ ቆርጠን ወይም ከመጠን በላይ በፍርሃት ተይዘን ከንስሓ አባት ጋር መነጋገርን እንድ ናቆም አይደለም:: ለንስሓ የሚያበቃውን ፍርሃት የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው:: ከንስሓ አባት መራቅን እንድንመርጥና ድብቅ እንድንሆን የሚያበረታታን ግን መጥፎ ታችንን የሚመኘው የሚ ፈልገውም ሰይጣን ደካማ ሰውነታችንን በመጠቀም ነው:: የዳዊት ልጅ አምኖን ትእማር የተባለችውን እኅቱን ለሥጋዊ ፈቃድ ሲፈልጋት ያጋጠመውን ችግር ለአባቱ ለዳዊት ቢነግረው መልካም መፍትሔ ያገኝ የነበረውን ትቶ በማታለያ ቃል አባቱን ተናግሮ ትልቅ በደል ፈጽሟል:: (2ኛሳሙ.13÷1-19):: ይህን እንዲያደርግ የመከረው ግን ራሱን መምራት የማይችል ባልንጀራው ነበር:: በእኛም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር አቀራረቡን እንወቅበት::

2ኛ/ ያለ ንስሓ አባት መኖር:- ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎች (ምእመናን) ንስሓ አባት የላቸውም:: ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን ልጆች መሆናቸውን ቢናገሩም የንስሓ አባት በመያዝ ሊያገኙት የሚገባቸው መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቅም የቀረባቸው ናቸው:: ብዙዎች ካህን የሚታሰባቸው ድንገተኛ ችግር ሲፈጥርባቸው ብቻ ነው:: ያለ ንስሓ አባት መኖር ትልቅ ስሕተት ከመሆኑም በተጨማሪ ሽክም እንደ ከበደኝ ልኑር÷ ከእግዚአብሔር ተለይቼ ልኑር ብሎ እንደ መምረጥ ነው:: «ብዙዎች ለምን ንስሓ አባት የላቸውም?» የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ብዙ ውይይትን የሚጠይቅ ነው:: ብዙ ችግሮች ሊዘረዘሩ ይችላሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ የትምህርት (ግንዛቤ) ማነስ፣ ያለ ንስሓ አባት መኖርን መለማመድ ሊጠቀሱ ይችላሉ::

በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያን በቀላሉ የማትመለከተውና ወደ ፊትም መፍትሔ ልታስቀምጥለት የሚገባው በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች ከአገር ወጥተው በባሕር ማዶ የሚኖሩ ሰዎች ጉዳይ ነው፤ ባሕልና ሃይማኖት በሚለያይበት ቦታ ያለ ንስሓ አባት ሕይወታቸውን የሚመሩ ምእመናን በርካታ ናቸውና:: በአካል የንስሓ አባት በማይገኝበት ቦታስ ምእመናን ምን እንዲያደርጉ ነው ቤተ ክርስቲያን የምትመክረው? በእርግጠኝነት የተነገሩ መረጃዎች ባይኖሩም የንስሓ አባት ይዞ ከሚኖረው የማይኖረው ይበልጣል:: አንዳንዶች አላቸው የሚባሉም ቢሆን በዓመት አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ቤተሰባዊ በሆነ መልክ በዝምድና ከመጠያየቅ ያለፈ ግንኙነት አለመኖሩ በእርግጥ እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት የንስሓ አባት አላቸው ለማለት ያስቸግራል:: በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያናችን ተቋማዊ ዐቅሟን በተለያየ ክፍል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ዓለም ያሉ ምእመናንን በማዕከላዊነት ለመድረስ የሚያስችላትን ከማጠናከር በመለስ ያሉትን ቴክኖሎጂያዊ የመገናኛ ዘዴዎች መጠቀም የሚቻልባቸውን መንገዶች አተኩራ ልታስብበት የሚገባ ይመስለናል።

**3ኛ/ ንስሓ ላይ ሳይሆን ዝምድና ላይ ያተኮረ ግንኙነት መኖሩ :-**

የንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት መሠረት የንስሓ ሕይወት ነው። በእርግጥ እንደ አንድ ቤተሰብ ተቀራርቦ ክፉና ደጉን መካፈሉ መልካም ቢሆንም የንስሓው ጉዳይ ጨርሶ ተረስቶ ዝምድና ላይ ብቻ ካተኮረ ግን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ መምጣቱ አይቀርም። ንስሓ ላይ ያተኮረ ግንኙነት አለመኖሩ አንዱ ችግር ነው። በእርግጥ በንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነት ዋነኛው የንስሓ ጉዳይ ሳይነሣ መቅረቱ የንስሓ አባትም ሆነ ልጅ ግንኙነታቸውን እንዴት እያዩት ነው የሚል ጥያቄ ያስነሣል።

**4ኛ/ብዙ ልጆች በአንድ ንስሓ አባት መያዝ:-** አንድ ንስሓ አባት ሊከታተላቸው የሚችላቸው የንስሓ ልጆች ለዚህ ተግባር በሚመድበው ጊዜ የሚወሰን ቢሆንም መጠኑን ለመወሰን ግን መመዘኛ ተደርገው መታየት የሚገባቸው ሁኔታዎች አሉ። በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዙሪያ ትምህርት መስጠት ቢገባትም እያንዳንዱ የንስሓ አባትም ዐቅሙን አውቆ መመጠን ይገባዋል። ልጆቼ በዝተዋል ማለት ባለበት ኃላፊነት መሠረት በጥራትና በብቃት አይከታተላቸውም ማለት ያመጣል። ይህ ደግሞ የኋላ ኋላ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የሚያናጋ አካሔድን ይፈጥ ል። በተለይ በአንዳንድ ቦታ አንድ ካህን እስከ 1,000 የንስሓ ልጆች አሉኝ ሲል ይደመጣል። መቼ ሊከታተሏቸው ይሆን? በርግጥ በአንዳንድ የአገራችን ክፍሎችና በባሕር ማዶም ጭምር የም እመናን አጠቃላይ ብዛትና የአገልጋይ ቀሳውስቱ ቁጥር ስለማይመጣጠን የንስሐ አባቶች አብዝተው የሚይዟቸ ውን ልጆች እንዴት መምራት እንደ አለባቸው ሊተኮርበት ይገባል።

**5ኛ/ የአመለካከትና የዕውቀት ልዩነት መፈጠር:-** በአሁኑ ጊዜ ካሉት ችግሮች መካከል አንዱ ይህ ነው። የዘመኑ ትውልድ በዘመናዊ ትምህርት አመለካከቱና አስተሳሰቡ እየተለወጠ ሲሄድ የሚያነሣቸው ጥያቄዎች የሚሰነዝራቸው አስተያየቶች የሚያጋጥሙት ችግሮች በዓይነትም በመጠንም ይለያያሉ። ከዚህ የተነሣ የአመለካከትና የዕውቀት ልዩነት ይፈጠራል። የንስሓ ልጅ ለሚፈጠሩብኝ ችግሮች መፍትሔ አላገኘሁም ይላል። የንስሓ አባት ደግሞ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው አያውቅም።

በአጠቃላይ በክፍል አንድ የገለጥናቸውን የንስሓ አባት ኃላፊነቶችን የንስሓ ልጅነት ሃይማኖታዊ ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት በዚህ በክፍል ሁለት የቀረቡትንም ችግሮች መፍታት የንስሓ አባትና ልጅ ግንኙነትን ፍሬያማ ያደርገዋል። በመሆኑም በሦስት ወገን ልዩ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

## 1. በቤተ ክርስቲያን በኩል

የቤተ ክርስቲያኒቱን ተልእኮ ተግባራዊ ከሚያደርጉ አካላት መካከል የመጀመርያዎቹ ቀሳውስት ናቸው። ስለዚህ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከዚህን በፊት በቅስና መዓረግ እንዲያገለግሉ የሠየመቻቸው ቀሳውስት ተልእኳቸውን ለመፈጸም፣ ምእመናንን ለመያዝና ለመምራት የሚያስችላቸውና ጊዜውንና ትውልዱን ያገናዘበ መመሪያ ብታወጣ ሥልጠናም ብትሰጥ መልካም ነው። ይህም ቀሳውስቱ አንድ ዓይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ በየጊዜው ኅብረተሰቡ ለሚያነሣቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት፣ በሕዝቡ መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታትና ብቃት ያላቸውን ቀሳውስት ለማሠራት ያስችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ እስከ አሁን ሲደረግ እንደ ነበረው በአንድ ክብረ በዓል በተጣበበ ጊዜ ለበርካታ ሰዎች ሥልጣነ ክህነት ከመስጠት ይልቅ ሰዎች አስቀድመው የክህነት ዓላማው፣ ኃላፊነቱ፣ አተገባበሩ ምን እንደ ሆነ የሚማሩበትን ሁኔታ ብታመቻች። ይህንንም በሥራ ለመተግበር እንዲቻል በአህጉረ ስብከት ደረጃ የካህናት ማሠልጠኛዎችን ማቋቋምና ማጠናከር ይገባል። በየአብነት ት/ቤቶችና በግል ከአብነት መምህራን መሠረታዊውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የተማሩ ሰዎች የመግቢያ ፈተና እየተሰጣቸው ወደ ማሠልጠኛው ገብተው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ትምህርተ ኖሎትን ተምረው ያን ሲያውቁ ሥልጣነ ክህነት ቢቀበሉ ጥሩ ውጤት ያለው ሥራ መሥራት ይቻላል። ይህም በአጠቃላይ በካህናትና በምእመናን መካከል ከንስሐ አባትነትና ልጅነት አኳያ ሊፈጠሩ የሚችሉ በርካታ አለመግባባቶችን ለማስወገድ ያስችለናል።

## 2. በካህናት በኩል

ሥልጣነ ክህነት ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበሏት አምላካዊ ገንዘብ መሆኗ ይታወቃል። በመሆኑም በእግዚአብሔር ገንዘብ እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ የመሥራት መሥራት ሕዝቡን በሃይማኖት በምግባር የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ዘወትር በልቡናቸው ሊያስቡትና ሊሠሩት ይገባል። ይህንንም ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት አስቀድሞ አገልግሎቱን እንደ ሥራ ሳይሆን እንደ የሕይወት አካል አድርጎ መቀበል ያስፈልጋል። የሚያስገድደው ሳይኖር ወድዶ ፈቅዶ ሥልጣነ ክህነትን የተቀበለ ሰው በቅዱስ ጴጥሮስ በኩል የተቀበለው ክህነቱን ብቻ ሳይሆን አደራውን ጭምር ነው። በመሆኑም ያለበትን ጊዜ፣ ኅብረተሰብ፣ በአገር ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ክስተቶችን ከግምት ውስጥ አስገብቶ ሕዝቡን ለመጠበቅ እንዲችል በየጊዜው በዕውቀት ምሉዕ ሆኖ መገኘት አለበት። በመንፈሳዊ ዕውቀቱ ከሚሠራቸው ምእመናን ካልተሻለ፣ በቀለም ዕውቀት ቢያንስ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን የማያውቅ ከሆነ ከፈረሱ ጋሪው በመቅደሙ ተልእኮውን ለመፈጸም ያዳግተዋል። በተጨማሪም እርሱም የበታችነት እየተሰማው አገልግሎቱን ይጠላል፤ የሚያናገረውና የሚያስተምረውም ትምህርት ምእመናንን የማይስብ ይሆናል። ስለዚህ ካህኑ «ዘመኑን እየወጃችሁ በውጭ ባሉቱ ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ። ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁል ጊዜ በጨው እንደ ተቀመመ በጸጋ ይሁን» ያለውን ቃለ ሐዋርያ መመሪያው እንዲያደርገው ይጠበቅበታል። ቆላ.4÷5-6።

## 3. በምእመናን በኩል

ምእመናን በሃይማኖት መንገድ ተጉዘን ከእግዚአብሔር ለመድረስ የእርሱ የሆነውን በጎ ነገር ሁሉ ለማግኘት የንስሐ አባት ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን መረዳት ይገባናል። በግብፅ ለነበረው ሕዝበ እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን፣ ለእስራኤል ሌዋውያንን የሰጠ እግዚአብሔር በየጊዜው ሕዝቡን በሃይማኖት መንገድ የሚመሩ ካህናትን ይሰጣል። በመሆኑም እያንዳንዱ ምእመን በብቃት ሊያስተምሩት፣ ሊመክሩት ሊመሩት የሚችሉትን የንስሐ አባት የመያዝ መንፈሳዊ ግዴታ ስላለበት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የንስሐ አባት መያዝ ብቻ ሳይሆን ከንስሐ አባቱ ጋር በመነጋገር ሊማር ሊወያይ የሚችልበትን ጊዜ መስጠት ይጠበቅበታል። በዚህም ጊዜ የንስሐ አባቱ ከሚሰጡት ትምህርት በተጨማሪ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ በኑሮው ውስጥ ያጋጠሙትን ችግሮች በግልጥ በማንሣት የንስሐ አባቱ መፍትሔውን እንዲሰጠው ተቀዳሚና የዘወትር ተግባሩ ሊያደርገው ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ ካህናት ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ሊፈጽሙበት የሚገባውን ጊዜ ኑሯቸውን ለመደጎም ሲል በሚያደርጉት መሯሯጥ እንዳይጨርሱት ምእመናን ከደብራቸው የሰበካ ጉባኤ ጋር በመነጋገር አስተዋፅዖዋቸውን በጊዜ መክፈል፣ አዳዲስ የልማት ሥራዎችን ማስፋፋትና ማጠናከር እጅጉን ይጠበቅባቸዋል። ይህ ካህናቱ በአንድ አሳብ አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙ፣ ባላቸው ጊዜ ዕውቀታቸውን እንዲያስፋፉ ያደርቸዋል።

በዚህ መልኩ ሁሉም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሲወጣ ቤተ ክርስቲያኒቷ ባላት ልዩ መዋቅራዊ አደረጃጀት ከከተማ እስከ ገጠር ለመድረስና በኅብረተሰቡ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መፈታትና የሕዝቡን ሕይወት መታደግ ትችላለች። አገልጋዮቹም ጸድቀው የሚያጸድቁ ይሆናሉ። <u>የተወደዳችሁ አንባቢያን:-</u> ባነሣነው ርእስ ጉዳይ ላይ ያላችሁን አስተያየት እንድትልኩልን በዚህ አጋጣሚ እንጠይቃለን። ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት

*መምህር ቸሬ አበበ*

ካለፈው የቀጠለ

## መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

«መጽሐፈ ኪዳን ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሐፍወ ለዝ ኪዳን ዮሐንስ ወጴጥሮስ ወማቴዎስ እንዘ ያጽሕፎሙ እግዚእነ ወፈነወ በአርዓያዝ ግጽው እም ኢየሩሳሌም፤ ይህን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የኪዳን መጽሐፍ ዮሐንስ ጴጥሮስና ማቴዎስ ጌታችን እያጻፋቸው ጻፉት:: በዚህ ዓይነት መግለጫም ወደ ኢየሩሳሌም ላከው፤ እንዲህ ብሎ በመጀመር የሚያትተው ይህ ጌታ ያስተማረው መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ከ81 መጻሕፍት አንዱ ሲሆን የሚመደበውም ከሐዲስ ኪዳን ስምንት የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍት ክፍሎች ነው::

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 29 አንቀጾች ያሉት መጽሐፍ ነው:: ይህም ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን፣ የዘወትር ኪዳናት፣ ትምህርተ ኅቡአት፣ እግዚአብሔር ዘብርሃናት፣ ቅዳሴ እግዚእ፣ በእንተ ቅድሳት ወዘተ የሚናገር መጽሐፍ ነው:: ይህ መጽሐፍ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት ለ11 ቅዱሳን ሐዋርያት በገሊላ ለ40 ቀናት እየተገለጠ ያስተማራቸው እየጠየቀት የመለሰላቸው ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አንዱ ነው::

«ኪዳን ዘነገሮሙ እግዚእነ ለዐሠርቱ ወአሐዱ አርዳኢሁ በገሊላ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት በገሊላ ጌታችን ያስተማራቸው /የነገራቸው/ የኪዳን መጽሐፍ ይህ ነው::» እንዲል:: /መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ክፍል 1፣ ግብረ ሐዋ.1÷2-3/::

የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ይዘት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቅዳሴ ነው:: ይህም ጸሎተ ኪዳን እንዲጸልዩባቸው በተመደቡ ሦስት የኪዳን ጊዜያት /ጸሎተ ኪዳን ዘሠለስቱ ጊዜያት/ ተከፍለው የሚገኙ ዘጠኝ ሥርዓታተ ጸሎታትን /ዘጠኙ ኪዳናት የሚባሉትን/ ይዟል:: እነርሱም:-

1. ኪዳን ዘመንፈቀ ሌሊት
   - ሀ. ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኩሉ
   - ለ. አምላከ ብርሃን ወላዴ ሕይወት
   - ሐ. ንሤልስ ለከ ዘንተ ስብሐት
2. ኪዳን ዘነግህ
   - ሀ. እግዚአብሔር አብ ወሃቤ ብርሃን
   - ለ. እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዓነ ቅዱስ
   - ሐ. ንሤልስ ለከ ቅዱስ ስብሐተ
3. ኪዳን ዘሠርክ
   - ሀ. ለከ ለአብ ዘኢይማስን መድኃኔ ነፍስነ
   - ለ. ንዌድስከ እግዚኦ
   - ሐ. ለከ ዘእምልብነ ናቸው::

### የመጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ አንቀጾች ዝርዝር ይዘት:-

- አንቀጽ 1 ስለ መንፈስ ቅዱስ
- አንቀጽ 2 ስለ ኋለኛው ዘመን ትምህርት
- አንቀጽ 3 በስማያት ስላለው ነገር
- አንቀጽ 4 ስለ ተመረጡ ሰዎች
- አንቀጽ 5 ሀገሮች ላይ ስለ ተነገረ ትንቢት
- አንቀጽ 6 ስለ ሐሳዊ መሲህ ትምህርት
- አንቀጽ 7 ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ስላስተማራቸው ትምህርት
- አንቀጽ 8 ኢየሱስ ክርስቶስ ለማርያም፣ለማርታና ለሰሎሜ ስለ መለሰላቸው
- አንቀጽ 9 በሃይማኖትና በምግባር ስለ ጸኑ ሰዎች
- አንቀጽ 10 ስለ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና
- አንቀጽ 11 ስለ ጳጳሳት ሹመት
- አንቀጽ 12 ስለ ጳጳሳት ሹመት የሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
- አንቀጽ 13 ኤጲስ ቆጶሳት ለጸሎትና ለመሥዋዕት ስለሚያደርጉት ዝግጅት
- አንቀጽ 14 በቤተ ክርስቲያን ስለ ሚያስተምሩ ሰዎች
- አንቀጽ 15 በቤተ ክርስቲያን የተለያየ መቋሚያ ቦታ ስለ መኖሩ
- አንቀጽ 16 ስለ ሥርዓተ ቁርባን
- አንቀጽ 17 ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ
- አንቀጽ 18 በሽተኞች ላይ ስለሚደረግ ቅብዕ
- አንቀጽ 19 ስለ ማኅበር ምስጋና
- አንቀጽ 20 ስለ ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን
- አንቀጽ 21-22 ስለ ቀሳውስት ሹመትና ሥርዓተ ጸሎት
- አንቀጽ 25 የካህናትን ቃል ስለሚሰሙ ሰዎች
- አንቀጽ 26 ስለ ድኅነትና ስለ ጥፋት
- አንቀጽ 27 በሽተኞችን ስለሚጐበኙ ካህናት
- አንቀጽ 28 ስለ ዲያቆናት ሹመት
- አንቀጽ 29 ስለ ዲያቆናት መላክና እንግዳ መቀበል
- አንቀጽ 30 ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መቆም እንዲገባቸው
- አንቀጽ 31 ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት
- አንቀጽ 32 ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ስለ ሚቆሙ ሰዎች
- አንቀጽ 33 ስለ ዲያቆናት አገልግሎት
- አንቀጽ 34-36 ስለ ምእመናን ሹመትና ሊደረግላቸው ስለሚገባ ጸሎት
- አንቀጽ 37 ስለ ቧት አገልግሎት
- አንቀጽ 38 ስለ ንፍቅ ዲያቆን ሹመት
- አንቀጽ 40 መሾም ስለ ሚገባው ሰው
- አንቀጽ 41 ስለ ሕዝባውያን
- አንቀጽ 42 አገልጋዮችን ስለ መቀበል
- አንቀጽ 43 ስለ ዘማውያን ሥርዓተ ጥምቀት
- አንቀጽ 44 ሰላምን ስለ መቀበል
- አንቀጽ 45 ሴቶች ራሳቸውን ስለ መከናነባቸው
- አንቀጽ 46 ንዑስ ክርስቲያንን ስለ መባረክ
- አንቀጽ 47-48 ንዑስ ክርስቲያንን በመከራቸው ጊዜ ስለ መቀበል
- አንቀጽ 49 ስለ ሥርዓተ ጥምቀት
- አንቀጽ 50 ስለ ሜሮን አቀባብ
- አንቀጽ 51 ስለ ምሥጢረ ቁርባን
- አንቀጽ 52 በበዓለ ኀምሳ ጾምና ስግደት እንደማይገባ
- አንቀጽ 53 ከኤጲስ ቆጶሳት ጋር ስለ ሚጠሩ ሰዎች
- አንቀጽ 54 ለቤተ ክርስቲያን መብዓ ስለ ሚያገቡ ሰዎች
- አንቀጽ 55 ስለ ሙሽሮች ሥርዓት
- አንቀጽ 56 ለበሽተኞች ስለሚፈጸም ተግባር
- አንቀጽ 57 ስለ ሞተ ደኻ ሰው የሚደረግ ሥርዓተ ጸሎት
- አንቀጽ 58 ሁል ጊዜ ስለሚጸልዩ ሰዎች
- አንቀጽ 59 ስለ ሥርዓተ ቁርባን

## መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

ይህ ሁለተኛው የኪዳን መጽሐፍ ከስምንቱ የቅዱሳን ሐዋርያት የትምህርትና የሥርዓት መጻሕፍት አንዱ ሲሆን እንደ መጀመሪያው የኪዳን መጽሐፍ በአንቀጽ የተከፋፈለ አይደለም:: በሥርዓተ ቅዳሴው መጽሐፍ የቅዳሴ እግዚእ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ ባለ 59 አንቀጽ ሲሆን መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ ደግሞ ወጥ ሆኖ ስለ ካህናት ሹመትና አገልግሎት፣ ስለ ንዑስ ክርስቲያን ጥምቀትና ምሥጢረ ቁርባን እንዲሁም የጥጦስን የሐሳዊ መሲህን ነገር በመግለጽ ስለ ክርስቶስና ስለ ዳግም ምጽአት የሚናገር መጽሐፍ ነው::

ሐሳዊ መሲሕ «እኔ ክርስቶስ ነኝ» ብሎ የሚመጣው አባቱ ከነገደ ዔሳው እናቱ ከነገደ ዳን እንደ ሆነ የሚነገርለት የዓመፅና የክፋት ሰው ነው::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት እንደሚነሡ ተናግሯል:: /ማቴ.11÷23-35፣ 24÷25/:: ሐሰተኞች ከራሳቸው አንቅተው ትንቢት እንናገራለን /ኤር.14÷14/ እያሉ በክፉ መንፈስ የሚመሩ /1ነገ.22÷19-24/ ራሳቸውንም ሌላውንም ወደ ጥፋት የሚወስዱ ናቸው::

ቅዱስ ዮሐንስም በደሴተ ፍጥሞ በግዞት ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የወደፊቱን የዓለም ጉዞ ምን እንደሚመስል በራእይ ሲመለከት ስለ ሐሳዊ መሲሕም በስፋት ተናግሯል:: /ራእይ 13÷1-18/::

በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ስለ ሐሳዊ መሲሕና ተከታዮቹ በይበልጥ፣ በስፋት ይናገራል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## መጽሐፈ ዲድስቅልያ

ዲድስቅልያ የመጽሐፉ ስም ሲሆን ትርጉሙም ትምህርት ማለት ነው። ይህም ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 35 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ አንዱና ጥንታዊው ነው። ዲድስቅልያ ዘቅዱሳን ሐዋርያት /Apostolical Constitutions/ ይባላል። መጽሐፉ ቀደም ሲል ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉሞና ተጠብቆ ኖሯል። እንዲያውም ከፍተኛ ዋጋው ቀደም ብሎ ስለ ታወቀ ከእንግሊዝኛ ትርጓሜው ጋር በአውሮፓ ታትሟል። ይህ መጽሐፍ የቅዱሳን ሐዋርያት አስተምህሮ የሥርዓት ክፍል ሲሆን 43 አንቀጾችን የያዘ መድበለ ትምህርት ወተግሣጽ ነው። እነዚህም ስለ ሰው ልጅ ሕይወትና ሞት ስለ ፍቅረ ሰብእና ፍቅረ እግዚአብሔር፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ጾምና ጸሎት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ካህናት ክብርና አገልግሎት፣ ስለ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚፈጸሙ የተለያዩ ምሥጢራት ይናገራል ።

መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዐበይትና ንዑሳን አንቀጾች አሉት። በእያንዳንዱ ዐቢይ አንቀጽ ብዙ የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች ይገኛሉ።

### የመጽሐፈ ዲድስቅልያ ዐበይት አንቀጾች ዝርዝር

አንቀጽ 1 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት
አንቀጽ 2 ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብና መረዳት እንዲገባ
አንቀጽ 3 የትዳር ጓደኞች መከባበር እንዲገባቸው
አንቀጽ 4 የካህናት ክብርና አገልግሎት
አንቀጽ 5 ኤጲስ ቆጶሳት ነገረ ሠሪን መስማቱ እንደማይገባቸው
አንቀጽ 6 ካህናት በፍቅር በየወሃት ሆነው ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመለሱትን ሰዎች ንስሐቸውን መቀበል እንደሚገባቸው።
አንቀጽ 7 አንድ ሰው መበደሉን ሳያረጋግጡ መቅጣት እንደማይገባ
አንቀጽ 8 ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን መብዓ ማቅረብ እንዲገባቸው
አንቀጽ 9 ዲያቆናት ለካህናትና ለኤጲስ ቆጶሳት መታዘዝ እንዲገባቸው
አንቀጽ 10 ኤጲስ ቆጶሳት መንፈሳዊ ዕውቀትና ጥበብ ሊኖራቸው እንዲገባ
አንቀጽ 11 ቂም በቀል መያዝ እንደማይገባ
አንቀጽ 12 ክርስቲያኖች መዝፈንና ወደ ዘፈን ቦታ መሄድ እንደማይገባቸው
አንቀጽ 13 ባል የሌላቸው ባልቴቶች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማበርከት እንዲገባቸው
አንቀጽ 14 ሴቶች ማጥመቅ እንደማይገባቸው
አንቀጽ 15 ሥልጣነ ክህነት የሌለው የክህነትን ሥራ እንደማይሠራ
አንቀጽ 16 ባል ሚስትን ወይም ሚስት ባልን ያለ ምክያንት መፍታት እንደማይገባ
አንቀጽ 17 አባትና እናት ስለ ሞቱባቸው ልጆች
አንቀጽ 18 ኤጲስ ቆጶሳት አባትና እናት ስለ ሞቱባቸው ልጆች ማዘንና መርዳት እንዲገባቸው
አንቀጽ 19 ባል የሞተባት ሴት በሃይማኖትና በትዕግሥት መቀበል እንዲገባ
አንቀጽ 20 ኤጲስ ቆጶስ መብዓ ከማን መቀበል እንዲገባው ስለ መረዳቱ
አንቀጽ 21 ወላጆች ልጆቻቸውን መምከርና መገሠጽ እንዲገባቸው
አንቀጽ 24 ስለ ፋሲካ በዓል አከባበርና ስለ ዓበይት በዓላት ክብር እንዲገባ
አንቀጽ 25 ለቅዱሳን ሰማዕታት ክብር እንዲገባቸው
አንቀጽ 26 ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ዘፈን ሳይሆን መዝሙር ማቅረብ እንዲገባቸው
አንቀጽ 27 ክርስቲያኖች በጣዖትና በአጋንንት ስማቸውን ይጠሩና ይምሉ ዘንድ እንዳይገባ
አንቀጽ 28 የበዓላትን ቀን በመንፈሳዊ ደስታ ማክበርና መጠበቅ እንደሚገባ
አንቀጽ 29 ሰሙነ ሕማማትንና የፋሲካ በዓላትን ማክበር እንደሚገባ
አንቀጽ 30 ወንጀለኞችና መናፍቃን ካልተመለሱ መለየት እንዲገባ
አንቀጽ 31 ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በቤተ ክርስቲያን ክርክርንና መለያየትን እንደሚፈጥር
አንቀጽ 32 ሐዋርያት ያስተማሩትን የአንድነት የሦስትነት ትምህርተ ሃይማኖት መማር እንዲገባ
አንቀጽ 33 ለሞቱ ሰዎች መጸለይ እንዲገባ
አንቀጽ 34 የሞትና የሕይወትን ጎዳና መለየት እንዲገባ
አንቀጽ 35 ስለ ሜሮን አስፈላጊነት
አንቀጽ 36 ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሠራዊተ መላእክት አገልግሎት
አንቀጽ 37 ሰንበትን ሲያከብሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ እንዲገባ
አንቀጽ 38 ይጠመቁ ዘንድ ስለሚወዱ ንዑስ ክርስቲያን
አንቀጽ 39 በውኃ ላይ ስለሚደገመው ጸሎት
አንቀጽ 41 አዲስ አማንያን ሲጠመቁ ጸሎት እንዲገባ
አንቀጽ 42 በሐዋርያት ሥልጣን ስለ ተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት

## መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

ይህ መጽሐፍ ከቅዱሳን ሐዋርያት ስምንት የሥርዓትና የትምህርት መጻሕፍት አንዱ ነው።

መጽሐፉም ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውና ቅዱስ ቀሌምንጦስ ከእርሱ አግኝቶ የጻፈው ነው። የቀሌምንጦስ መጽሐፍ በአኅጽሮተ ቃል ልዩ መጠሪያው ጴጥ. ሲሆን ትርጉሙም ጴጥሮስ ማለት ነው። ይዘቱም ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጽ ያለው ነው። ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቅርጹን አስመልክቶ ስለ ጽላተ ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጶስ አዲስ ቤተ መቅደስ የሚባረክበትን ሥርዓት፣ ሥርዓተ ጥምቀትንና በእጅ መንሻና መተያያ ጥምቀት እንደማይፈቀድ ስለ ሥርዓተ ቁርባን ወዘተ ይናገራል። በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ስለ ክብረ በዓላት፤ ስለ ሰንበተ ክርስቲያን የዕረፍት ቀን መሆን በሰሙነ ሕማማት የምእመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለ መሆኑ ያትታል። /ቀና. 1-11/።

ቅዱስ ጳውሎስ ቀሌምንጦስ በፊልጵስዩስ ይኖር እንደ ነበርና «አንተም ደግሞ በሥራዬ አብረህ የተጠመድህ እውነተኛ ሆይ ...» (ፊልጵ.4÷3) በማለት ቀሌምንጦስ በሕይወት መጽሐፍ የተጻፈ እውነተኛ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድእና ደቀ መዝሙር እንደ ሆነ ገልጿል።

በዚህ መጽሐፍ የአበው ሐዋርያት ትምህርቶች ከሆኑት ሁለት ጽሑፎች መልእክትና ድርሳን (letter and homily) ተጠቅሰዋል፤ በትውፊትም ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ቀሌምንጦስ የሮማ 3ኛ ጳጳስ እንደነበረ ይናገራል።

ድኅረ ልደተ ክርስቶስ የተጻፈው ቀዳማዊ ቀሌምንጦስ የቤተ ክርስቲያን አበው መምህራን በመገደላቸው ምክንያት አለመግባባት ወደ ተፈጠረባት የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በሮማው ጳጳስ የተላከ መልእክት ነው።

መልእክት ከሰባው ሊቃናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸውና እንዲሁም ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በተለይ ከዕብራውያን መልእክት የተወሰደ መሆኑ ተገልጿል።

ታሪክም «ሐዋርያው ማትያስ ለ40 ቀናት በእስር ቤት ተቀምጦ እግዚአብሔር ጽናቱን ስለ ሰጠው ያቀረቡለትን ሣር ሳይበላ በጾም አሳለፈው። በ40ኛው ቀን ማትያስ ሣሩን ከፊቱ ከምሮ ሲዘምር እንድርያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ በተዘጋው በር ገባ፤ በደስታና በናፍቆት ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ «እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ የሚለው ቃል ዛሬ በአንተ ተፈጸመ» ሲል የእግዚአብሔርን ቃል አስታወሰው፤ ከእስር ቤትም ይዞት ወጣ፤ አብረውት በዚያው ታስረው የነበሩ 183 ሰዎችም ወጡ። ይህንን ተአምር ያዩት የአገሪቱ ሰዎች በትምህርቱ አምነው ተጠመቁ» በማለት ያስረዳል። ለእነዚህ ሰዎችም መጽሐፍ ጽፎ እንደ ሰጣቸው ቀሌምንጦስ በመጽሐፉ መስክሯል።

### የመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ክፍሎች

መጽሐፈ ቀሌምንጦስ በስምንት ዓበይት ክፍሎች የሚከፈል ሲሆን የእያንዳንዱን ክፍል ሙሉ አሳብ ማቅረብ ባይቻልም በከፊል እንደሚከተለው ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ክፍል 1

- ❖ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐረገ በኋላ ሐዋርያትን በሁሉም አቅጣጫ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ እንዲያስተምሩ እንደ ላካቸው፤
- ❖ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርት ላይ እንደ ተመሠረተች፤
- ❖ ከአዳም ጀምሮ ስላለው አጠቃላይ የዘር ሐረግ፤
- ❖ ስለ ገነትና ስለ ታላላቅ አባቶች የቀረበ ሰላምታ (ምስጋና)፤
- ❖ ከገነት ወጥተው ወደ ደብር ቅዱስ ስለ ገቡ ሰዎች ሁኔታ

## ክፍል 2

- ❖ ቀሌምንጦስ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ሆኖ ስለ መመረጡ
- ❖ ስለ ቀሌምንጦስ ሕይወትና አጠቃላይ ኑሮው
- ❖ የቀሌምንጦስ መንፈሳዊ አገልግሎት

## ክፍል 3.

- ❖ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ለቅዱሳን ሐዋርያት ያደረገውንና ያስተማረውን ሁሉ ለቀሌምንጦስ እንደ ነገረው፤
- ❖ በአገልግሎቱ እንዲጸና እንደ መከረው ይናገራል።

## ክፍል 4.

- ❖ እግዚአብሔር ለቅዱስ ጴጥሮስ ስላሳየው ራእይና ተአምራት፤
- ❖ ስለ ሥልጣነ ክህነት ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት አጀማመርና አሰጣጥ፤
- ❖ ስለ ዓለም አፈጣጠርና ሁኔታ፤
- ❖ ስለ ዳግም ምጽአት እንዲሁም ስለ ጻድቃንና ኃጥአን ሁኔታ፤
- ❖ ስለ መንፈስ ቅዱስ መውረድና ሁሉን እንደ ሚገልጥላቸው ይናገራል።

## ክፍል 5

- ❖ በሰው ልጆች ላይ በሰማይና በምድር ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ እንደ ነገረው
- ❖ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ስለ መወለዱ፤
- ❖ ኢየሱስ ክርርስቶ ወደ ግብፅ ስለ መሰደዱ፤
- ❖ ኢየሱስ ክርስቶስ ግብፅንና በዙሪያዋ ያሉ አውራጃዎችን ከአምልኮ ጣዖታት ነጻ ስለ ማድረጉ፤
- ❖ ወደ ገሊላ ስለ መግባቱ ይናገራል።

## ክፍል 6

- ❖ እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው ሥርዓተ ደብተራ ኦሪት ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደ ነገረው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ለቀሌምንጦስ ይህን ሰማያዊ ሥርዓት እንዳስተማረው፤
- ❖ ሙሴ እንደ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ አሮንና ልጆቹን ስለ መሾሙ፤
- ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዳስተማረው፤
- ❖ ስለ ሙሴና ስለ ጴጥሮስ ንጽጽራዊ ትምህርት፤
- ❖ በክርስቶስ የሚያምን የክርስቶስን ሥራ እንደሚሠራ፤
- ❖ ቅዱሳን ሐዋርያት ድውያንን ስለ መፈወሳቸው፤
- ❖ ንጽሕና በረከት ለመቀበልም ለመስጠትም አስፈላጊ እንደ ሆነ፤
- ❖ ክርስቶስ ራሱን ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሠዋ ይናገራል።

## ክፍል 7

- ❖ ስለ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት፤
- ❖ ስለ ዲያብሎስ ክፋትና ሽንፈቱ፤
- ❖ ስለ ሙሴ በትርና ስለ ክርስቶስ መስቀል ምሳሌነት፤
- ❖ ስለ ቅዱሳን ሐዋርያት አስ ተምህሮ፤
- ❖ ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ስለ መታዘዙ ይናገራል።

## ክፍል 8

- ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ንስሐ አስፈላጊነት ያየውና ያስተማረው
- ❖ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ብፁዕ ስለ መባሉ
- ❖ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጴጥሮስ የቃል መሠረትነት እንደምትሠራ
- ❖ ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ ስለመቀበሉ ወዘተ ይናገራል።

### ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት በይዘታቸው በትምህርትና በትንቢት በይበልጥም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያተኩራሉ።

እነዚህ የሥርዓት መጻሕፍት በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ቋንቋዎች ተጽፈው የሚገኙ ቢሆንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ ተጽፈው የሚገኙት በግእዝ ቋንቋ ነው። የሚገኙትም በታላላቅ ገዳማትና ጥንታውያን አድባራት ነው። በጽሑፉ እንደ ተገለጠው የሁሉም የሥርዓት መጻሕፍት አጠቃላይ ዝርዝር ይዘታቸው አልተሟላም። ይህም የሆነበት ምክንያት መጻሕፍቱ የሚገኙባቸው ቦታዎች ውስንነትና የቦታ ርቀት መኖር ነው።

ከመጻሕፍቱ ብዙዎቹ በአንቀጾች የተከፋፈሉና ለእያንዳንዳቸው መሪ ምልክት ወይም ልዩ መጠሪያ እንዳላቸው ሊቃውንት ይናገራሉ። መጻሕፍትም ያረጋግጣሉ።

**ረስጠአ:-** የመጀመሪያዎቹ ሁለት ፊደላት «ረስ» - ረሱል /Rusul/ ከሚለው ዐረብኛ ቃል የመጡ ሲሆን ትርጉሙም ሐዋርያት ማለት ነው።

ሦስተኛው ፊደል «ጠ» ቀኖናቱ ወደ ምእመናን ሁሉ ከተላኩበት ረድእ ቀለምንጦስ ከሚለው ስም በማሳጠር የመጣ ነው፤ አንድም ተጥላሳት ከሚለው የዐረብኛ ቃል በማሳጠር የተወሰደ ሲሆን ቀኖናት፥ ትእዛዛት ማለት መሆኑ ተመልክቷል።

«አ» በግብፃውያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት አንደኛ ቀዳማዊ ማለት ነው። ረስጠአ ማለትም «ሐዋር ያት ቀኖናት ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ» ሲሆን ቅዱሳን ሐዋርያት በረድእ ቀሌምንጦስ አማካይነት የላኩት የመጀመሪያው የሥርዓት መጽሐፍ ማለት ነው።

**ረስጠብ:-** የ«ረስ» ና «ጠ» ትርጉም አስቀድሞ ከላይ እንደ ተገለጠው ነው። የመጨረሻው ፊደል «ብ» በግብፃውያን አኀዝ አቆጣጠር ሥርዓት የቀናቱን ቅደም ተከተል የሚጠቁም ሲሆን ሁለተኛው፥ ዳግማዊ ማለት ነው።

**ዓይን:-** ቃሉ የመጣው የመጀመሪያው ፊደል «ዓ» ከጽርዕ ፥ዓይን ደግሞ ከጽዮን ወስዶ ከጽርሐ ጽዮን (ዓይን) እንደ ተገኘ ይናገራል። በሌላም በኩል ዓይን ሐዋርያት ከተሰበሰቡት ቦታ የጽርሐ ጽዮን በገነት የመጀመሪያው ፊደል ነው ይባላል ።

**ድስቅ:-** ድስቅ ማለት የዲድስቅልያን መጽሐፍ የማያስረዳ መሪ ምልክት /አኅጽሮተ ቃል/ ነው።

**ቀሌ/ጴጥ:-** ቀሌ. ማለት ቀሌምንጦስ ማለት ሲሆን ጴጥ. ማለትም የቀሌምንጦስ መጽሐፍ አኅጽሮተ ቃል ሆኖ ጴጥሮስ ማለት ነው። ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ እየነገረው የጻፈው መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# በትንሣኤ በዓል እርድ መከናወን ያለበት መቼ ነው?

አብዛኛውን ጊዜ በተለይም በትንሣኤ በዓል ብዙ ምእመናን ቅዳሜ ለእሑድ ምሽት 12 ሰዓት ጀምሮ እርድ ያከናውናሉ:: ለመሆኑ የትንሣኤው ሌሊት ቅዳሴ ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የጾሙ ክፍል በኾነው ሰዓት የታረደ እንስሳ ሥጋ ይበላልን? በአጠቃላይ የትንሣኤ በዓል እርድ መከናወን ያለበት መቼ ነው ? ብታብራሩልኝ?

ኤልያስ አይፎክሩ
/መሐል ሜዳ/
በለጠ ጥላሁን

መልስ :- የተወደዳችሁ አንባቢያን:- የላካችሁልን ጥያቄ ወቅታዊና መሠረታዊ በመሆኑ ምላሹንም ምእመናን ሁሉ ሊያውቁት የሚገባ ነው:: ለዚህ ጥያቄ መልስ በመስጠት የተባበሩንን የሐዲስ ኪዳን መምህር የሆኑትን አባ ወ/ጊዮርጊስ ፀጋውን እያመሰገንን የጥያቄውን መልስ እንዲህ አቀናብረነዋል:: መልካም ንባብ ::

በዐቢይ ጾም ውስጥ ካሉት ስምንት ሳምንታት ውስጥ አንዱ ሰሙነ ሕማማት ነው:: ሰሙነ ሕማማት ማለት የሕማማት ሳምንት ማለት ነው:: እነዚህ ዕለታትም ከሠርክ ሆሣዕና ጀምሮ ያሉት ቀናት ናቸው:: ሰሙነ ሕማማት የተባለው ለ5500 ዘመን የነበረው የዓመተ ፍዳ የዓመተ ኩነኔ ምሳሌ በመሆኑ፤ አንድም ዕለታቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር ኃጢአት ለመደምሰስ፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ለማላቀቅ፣ከሲኦል ባርነት ነጻ ለማውጣት፣ ከሞተ ሥጋና ከሞተ ነፍስ ለማዳን በዕለተ ዓርብ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራዎች የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው:: «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ» እንዲል:: ኢሳ. 53÷2::

በሰሙነ ሕማማት የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መከራና ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍት ተውጣጥተው ይነበባሉ፤ አዳም ከፈጣሪው ተጣልቶ ለ5500 ዘመን መኖሩን ለማስታወስ መንበረ ታቦቱ ሳይቀር በጥቁር ልብስ ይሸፍናል:: ልብሰ ተክህኖውም ጥቋቁር ነው::

ቅዱሳን ሐዋርያትም ጌታችን ከተያዘበት ከሐሙስ ማታ ጀምሮ እስኪነሣ ድረስ ትንሣኤውን ሳናይ ምግብ አንቀምስም ብለው ለሦስት ቀናት የጾሙት «ጾመ አክፍሎት» ይባላል:: «ሙሽራው ከእነርሱ በተለየ ጊዜ ይጾማሉ::» እንዳለ ጌታ:: ማቴ.9÷15:: ከእነዚህ ዕለታት አንዱ ቀዳም ስዑር ናት:: ቀዳም ስዑር ጾም መሆኑን ሠለስቱ ምእት :- «ጾመ አርብዓ /ዐቢይ ጾም/ እና ከፋሲካ የሚቀድሙ ሰባቱን ዕለታት /ሰሙነ ሕማማት/ ጾምነታቸውን በፍጹም ጥንቃቄ ጠብቅ:: በሰንበት ቀኖችም እንደ ሌሎች ቀኖች አትጹም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስኩብ በመቃብር ሆኖ ከነበረባትና ድኅነት በተደረገባት ከፋሲካ ዋዜማ ካለች ከአንዲት ቅዳሜ ቀን /ቀዳም ስዑር/ በቀር» በማለት ገልጸዋል:: ሃይ .አበው ዘሠለስቱ ምእት ምዕራፍ 21÷27:: ይህች ዕለት ግን በጾም ስለ ተሻረች «ቀዳም ስዑር፤ የተሻረች ሰንበት» ትባላለች:: በዚህች ዕለት ካህናት «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሃደ» እያሉ ቄጤማ እያደሉ የምሥራቹን ይናገራሉ:: ምሳሌነቱም ኖኅ የላካት ርግብ የለመለመ ቅጠል ይዛ የጥፋት ውኃ መጉደሉን ለኖኅ እንዳበሠረች ካህናትም «ነትገ ማየ ኃጢአት÷ ሐጸ ማየ ኃጢአት» እያሉ በመስቀል ኃጢአተ ዓለም መደምሰሱን ቄጤማ ይዘው ያውጃሉ::

ብዙ ሰዎች የቀዳም ስዑር ምሽት ዶሮ፣በግ፣...ወዘተ ያርዳሉ:: በዚህ ዕለት ማረድ በልማድ ተያይዞ የመጣ እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ትውፊቱ አያዝም:: በቀዳም ስዑር ለምን እንደሚያርዱም ሲጠየቁ «ለበዓሉ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ፣ ሌሊት ከቤተ ክርስቲያን አስቀድሰው ሲመለሱ ለመግደፍና ነዳያንን ለማስፈሰክ ነው» በማለት ይመልሳሉ:: ሊቃውንቱ ሲያትቱ ግን ዝግጅት የሚያስፈልጋቸው የሚባሉት በባሕርያቸው የሞቱ ለምን ላቸው ምግቦች ነው:: ማለትም እንጀራ፣ ዳቦ...ወዘተ:: ምክንያቱም እነዚህን ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ የሚፈልግ ነውና:: እንስሳት ግን ደመ ነፍስ ናቸው:: እንስሳን ለማረድ ዝግጅት አይጠይቅም፤ ወዲያው የሚታረዱ ናቸው:: ነዳያንን ማስፈሰክ ለተባለውም ተንሥአ እሙታን ከሚባልበት ከመንፈቀ ሌሊት በኋላ ተሠርቶ የሚደርስ ነው::

በዓሉን በማስመልከት ባለን ዐቅም እርድ የምናርደው የደስታ፣የምሥራች መግለጫ ነው:: ደስታችንን የምንገልጸው ደግሞ ጌታችን ከተነሣ በኋላ ነው:: የትንሣኤያችን የምሥራች የተሰበከልን በጌታችን ትንሣኤ ምክንያት ነውና:: ስለዚህ «ወተንሥአ እሙታን፤ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤» ተብሎ ዐዋጅ ሳይታወጅ መታረድ የለበትም:: በቀዳም ስዑር ማረድ ዐዋጅ ሳይታወጅ ከማረዳችንም በላይ የትንሣኤን በዓል አላከበርንም እንደ ማለት ነው::

የጌታችን ትንሣኤ የምሥራች እስከሚነገርበት ሰዓት ድረስ ስመ ሥላሴ አይጠራም:: ታድያ በቅዳሜ ምሽት በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሳይባል፣ በመስቀል ሳይባረክ ማረድ በዘመነ አሪት እንደ ታረደ ፣/እንደተሠዋ/ ነው የሚቆጠረው:: ምክንያቱም «ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን» አልተባለምና::

እንደ ሊቃውንቱ አገላለጽ ሌሊት ከቅዳሴ መልስ በየቤታችን ልንመገበው የሚገባ ከጥሉላት ምግቦች ርቀን ከመቆየታችን አንጻር ጤንነታችንን የማይጐዳ ማር ፣ ተልባ፣በወተት በእርጎ ተደርጐ ነው የሚበላው:: እርድ መፈጸም ያለበት ጠዋት ወይም ደግሞ «ወተንሥአ እሙታን» ከተባለበት ከሌሊቱ 6:00 በኋላ ነው:: ያኔ መስቀል ይዞራልና::

አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ ቀዳም ስዑር ጾም መሆኑን አምናለሁ:: ነገር ግን ከምሽቱ 11:00 /ከዋዜማው/ ጀምሮ ወደ ሚቀጥለው ቀን /እሑድ/ ስለሚቆጠር ማረድ ይቻላል ይላሉ:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ሲመልሱ :- ፍትሐ ነገሥቱ .በአንቀጸ ጾም ላይ «ክብርት በምትሆን በ፵ ጾም በመጀመሪያው ሱባኤ እስከ 12 ሰዓት፣ከቅድስት ጀምሮ እስከ ኒቆዲሞስ ዓርብ እስከ 11 ሰዓት፣በሰሙነ ሕማማት እስከ 13 ሰዓት /ከሌሊቱ አንድ ሰዓት ጨምሮ ወይም እስከ ፀአተ ኮከብ –ኮከብ በሰማይ መልቶ እስኪታይ/ ጹሙ» ይላል:: ቅዱሳት መጻሕፍትም ለጾም ማድላት እንዳለብን ይመክሩናል::

ከምሽቱ 11:00 ጀምሮ ወደ ሚቀጥለው ቀን /ወደ ማግሥቱ/ ነው የሚቆጠረው የሚባለው ለምስጋና ሲሆን ነው:: ለምሳሌ:- በዋዜማ ምስጋና ለነገ የበዓሉ መዳረሻ /መግለጫ/ እንዲሆን ማለት ነው:: ጾም ግን ወዲያውኑ በተግባር /በድርጊት/ የሚፈጸም ነው:: ወደ ማግሥቱ ይቆጠራል አንልም፤ ምክንያቱም ጾም ተግባር ነውና::

በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍትም የሚያዙን «የሚቻላችሁ ከሆነ ከዚህ አብልጣችሁ ጹሙ» ነው የሚሉን:: ይልቁንም የጾማችንን ጊዜ ከዕለት ወደ ዕለት ከፍ እያደረግን ልንሄድ ይገባናል እንጂ በየምክንያቱ ከነበርንበት ልንቀንስ አይገባም:: የሰው ልጅ – በረከት፣ ስርየተ ኃጢአት፣ ድኅነት፣የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ራሱን ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መገዛት ማስገዛት ካልቻለ ከፈጣሪው ጋር አንድነት አይኖረውም:: ፈቃደ ነፍስን ለመፈጸም የምታበረታታ ደገኛ ሕግ ደግሞ ጾም ናት::»

በአጠቃላይ በቀዳም ስዑር ማረድ የጾም ክፍል በኾነው ሰዓት ከማረዳችን በተጨማሪ የትንሣኤን ምሥራች አይሰብከም:: ምክንያቱም ጌታችን እስኪነሣ ድረስ በኀዘን ነው ያለነው፤ እንደ ሥርዓቱ ከሆነ ሲታረድ ካህኑ ቢላዋውን ይባርክለታል÷ አራጁ ያርዳል÷ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብር አጥፍቶ ተነሥቷልና፤ «ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን» ተብሎ ዐዋጅ ተነግሯልና:: ስለሆነም በቀዳም ስዑር ምሽት ማረድ በልማድ የመጣ እንጂ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አይደለም::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከመጋረጃው ጀርባ

*በ1994 ዓ.ም በተደረገው የአጭር ልብ ወለድ ውድድር ሦስተኛ የወጣ::*

*መ/ር ጌታሁን አማረ ጎሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት*

«እንዴት ቢንቀኝ! እንዴት ቢደፍረኝ! በተከበርኩበት÷ ሀብት ንብረት ባፈራሁበት÷ እርሳቸው ገንዘብና ዘር ይመርጣሉ ተብሎ በታማሁበት አገር ይህ ጎርፍ ያመጣው መደዴ መንገደኛ የኔን ልጅ ለጋብቻ መጠየቁ:: እንዲያውስ ማሰቡ:: ይገርማል÷ መቼም ዕድሜ ዘልዛላው የማያሳየኝ የለ:: ብዬ ብዬ በዚህ ሰሌዳ ጠራጊ ልደፈር! ብቻ ጥፋቱ ከእርሱም ላይሆን ይችላል:: ያንን ጠመኔውን ሲለቀልቅ የሆነ መድኃኒት ቀባብቷት ይሆናል እንጅ አይደፍረኝም ነበር:: ደግሞ ከነርሱ ብሶ እነዚህ ቄሶች አርፈው ዳቦና ጠላቸውን እየዞሩ አይበሉም:: ሽማግሌ ነን ብለው ወደኔ ቤት ተንተው የሚመጡት:: እግራቸው ይሰበርና እንደ ለመደው ችግር አውርቶ ብር ሊለምን የመጣ መሰለኝ እንጂ መቼ ከእጁ እሳለም ነበር:: ወይኔ! ወይኔ! ከዚህ ሌላ ምን ውርደት አለና ጎበዝ:: አቻን ማጣት፣ እኩያን አለመሻት:: ደግሞ ልጅ ዎን ለልጃችን ተባለልኛ ነው ወጉ::» አሉ አቶ ቢሻው ንዴት በተሞላበት ንግግር ከበራፋቸው ላይ ከግራ ወደ ቀኝ እየተንጎራደዱ::

ረጅም ቀሚስና ተደራቢ ፎጣ በነጠላቸው ላይ አዘውትረው መልበስ የሚወዱት ወ/ሮ አስቻለች በባለቤታቸው ከመጠን ያለፈ ንዴት ተገርመውና ተደንቀው በአንክሮ ይመለከቷቸዋል:: በምን ዓይነት የንግግር ስልት ሊያስረዷቸው እንደሚችሉ ግራ ቢገባቸውም «ለምን ዝም አልሽኝ» ከመባል ለመዳን ሲሉ ብቻ ጉሮሮአቸውን ጉንፋን እንደ ዘጋው ሰው በሳል መልኩ ጠረግ ጠረግ ለማድረግ ሲሞካክሩ አቶ ቢሻው ዘወር ብለው ተመለከቷቸው::

«አየሽልኝ ያንቺዋን ጉድ! ደግሞ በተከበርንበት አገር ታላቋ ሳያገባ ለእርሷ ሽማግሌ መላኩን» አሉ ዐይናቸውን እያጉረጠረጡ::

«ምን ጉድ አለውና ነው÷ ሽማግሌዎቹ የጠየቁት ሁለታችንንም አይደለም እንዴ? የእርስዎ እንዲህ ደርሶ ብግን ማለት ከየት የመጣ ጠባይ ነው እቴ!!»

«አሃ. . . አንቺም ሽማግሌዎቹን ደጋፊ ነሻ! መች ገባኝ::»

«ታላላቅ አዛውንት ያውም የቤተ ክርስቲያን ካህናት ክብር ናቸው፤ ለኛ ደግሞ የአብርሃም እንግዶቻችን ናቸው፤ በሥርዓቱና በደንቡ ተቀብለን፣ አይሆንም፤ እኛ አንፈቅድም ነበር መባል ያለበት ወይስ እነኝህን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ማሳዘኑ ነበር የሚበልጠው::»

«ተይኝ! ተይኝ! እነርሱስ የሚሔዱበትን አጣርተው አይመጡም:: ወይኔ እጄና ገንዘቤ ነው ያስደፈረኝ::»

«ለምኑ? ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን መስጠትዎ? ቢያውቁበት ጽድቅ ነው:: ለካንስ እርስዎን ካህናቱ እንዲያመሰግንዎት፣ በየክብረ በዓሉ ቀን ስምዎት በየዐውደ ምሕረቱ እንዲጠራ ብቻ ነው ፍላጎትዎ:: ባይገርሞት የዛሬው ንግግርዎ እንኳን የውጮቹን እንግዶች እኔንም አሳዝኖኛል:: እርስዎን የመሰለ የተከበረ÷ አጥንቴ ሳይቀር የኮራ ነው ብለው የሚናገሩ ትልቅ መካሪ÷ ጥቁር ይሁን ቀይ የማያውቁትን ልጅ አክብሮ ሽማግሌ ቢልክ «ጎርፍ ያመጣው» ይላሉ:: እኔንና እርስዎንስ ምን አመጣን? ስንት አገር አቋርጠን ባዳውን ዘመድ አድርገን አይደለም ወይ የምንረኖው:: አጥፍተዋል÷ የተጣሉት ከሰው ሳይሆን ከፈጣሪዎ ጋር ነው:: ምክንያቱም እንግዳ አቃለዋልና ነው:: አሁን ሁሉም አልፏል÷ ይረጋጉና ሰንበትን ያክብሩ፤ ድሮም ሴትን የወለደ ይጠየቃል እንጂ አይጠይቅም:: የእርስዎ አኳኋን እኮ ለልጅዎ ባል የሚሆናት ጋር ሽማግሌ እንደሚልክ እንጂ እንደ ተጠያቂ አይደለም፤ አልነካም ባይ ነዎት» አሉ::

«አንቺ ጠበቃነትሽ ለማንኛው ነው? ለልጅሽ? ለቄሶችሽ? ለአምላክሽ ወይስ ለራስሽ?»

«ኡኡቴ ደግሞ ስለ ራሴ ለምኔ÷ ልጅቱም የጋራ፣ ቄሶችም የሁላችን፣ አምላኬ ሳይሆን አምላካችን ነው:: የምድራዊ ንግግርዎ ሰው ሳያስደስት÷ ወደ ሰማይ መዝለቅዎ ለቅስፈት ነው::»

«እኔ ልቀሰፍ÷ አንቺም ዳሪያትና ሰርግ ብሉ÷ ያማረሽ ይኸው ነው እንጂ ማንይሙት አንድ ልጅ ለአባቱና ለቤተሰቡ ክብር ሳይሰጥ ደርሶ ሽማግሌ ጠያቂ ያስመጣል እንዴ? እርሱን አልወቀው፣ ካህናቱም ሽምግልናው ይክበዳቸው:: ይህች ዘላን ምንም የማታውቅ መስላ እዚያው ቤተ ክርስቲያን የተቀረቀረችው ብትንቀኝ አይደል:: በእርሷ ቤት ሽማግሌዎቹ እኔን እሺ አሰኝተው ልታገባ:: መስሎአታል:: ለጸሎትና ለትምህርት የምትሔድ መስሎኝ÷ ለካስ የሷ ማታና ጠዋት መንዘላዘል ባል ፍለጋ፣ ምህላዋ ባል ስጠኝ ነበርና እንዴት ሠመረላት!! ይህ ነው ጸሎትና ምህላ:: እንደው ፍርጥ ብላ ትሞታለች እንጂ ዓይኔ እያየ አስተማሪ አታገባም::»

«አስተማሪነቱን ማን ነገረዎ? ዐሥሬ አስተማሪ፣ አስተማሪ የሚሉት?»

«ሽማግሌ ተብየዎቹ ናቸው:: እርሱም ቢሆን ወንጌል ያስተምራል፣ ጥሩ ልጅ እንደ ሆነ የነገሩኝ÷ ለፍላፊ ነው አይሉኝም፤ ስሙን ማሣመራቸው:: እርሱ አስተማሪ ሳይሆን አደንቋሪ ነው::»

«አለመታደልዎ÷ ወንጌል ያስተምራል ማለት ጠመኔ ለቅላቂ ማለት ነው? አይደለም እንጂ ቢሆንስ:: ቢገባዎት ሰውን ወይም መንግሥትን ሳይሆን የሚያገለግለው እግዚአብሔርን ነው:: ይህማ የተመረጠ እውነትን ያወቀ ቅዱስ ነው እንጂ::»

«አ-ሃ-ሃ-ሃ-ሃ ትገርሚያለሽ÷ የኛ መነኩሲት ነሽ እማሆይ÷ ተማክረሽ ነዋ ሽማግሌ የተላከው፤ እንዲህ ነው ወጉ:: ወንድና ሴቱ ይለያል፤ ያንቺን ቅዱስ አማች እናያለን:: ክንዴን ሣልንተራስ ልጄ ለፍላፊ አታገባም!!»

«አሁን የኔና የርስዎ ባዶ ሜዳ ላይ መነታረክ ምንም አይፈይድም÷ ትንሽ ረጋ ይበሉ÷ ንዴቱ ለጤንነትዎ ጥሩም እንዳ ልሆነ ያውቃሉ:: ለማንኛውም ባለ ጉዳይዋ ትምጣና አሳቧን እንጠይቃለን፤ እኔና እርስዎ ተጋጭተን ኋላ ሁለታችንም ጭራ እንዳንሆን:: የዛሬ ልጅ እንደው ሁሉንም ዐዋቂ ነው::»

«ኧረ ዕውቀት ይንሳት፤ አንዲት ቃል ትንፍሽ ትልና አንገቷን ጠምዝዤ ጥዬ ነው እጄን ለፖሊስ የምሰጠው፤ ደግሞ የምን ከሷ ጋር መነጋገር ነው፤ ኧረ ወዲያ» በማለት ከበረንዳው ወደ ቤት ውስጥ ገብተው ከሶፋው ላይ ዘጭ ብለው ተቀመጡ::

አብነት ወንድ አፍራሽ ዕድገቱ አዲስ አበባ ልዩ ሰፈሩ ደግሞ ሾላ በግ ተራ አካባቢ ነው:: ከልጅነቱ ጀምሮ በየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግል የኖረ ዲያቆን ነው:: አባቱ የቀድሞው ሻምበል ባሻ ሲሆኑ መተዳደሪያቸው የጡረታ ደሞዛቸው ነው:: ዛሬ አብነት ከሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በዲፕሎማ ተመርቆ በራሱ ጥያቄና ፍላጎት ከአዲስ አበባ ውጭ መመደቡን ወዶ በኢሉባቦር ዞን መቱ ከተማ በዞኑ አገረ ስብከት የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊና በመቱ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቋሚ ሰባኬ ወንጌል የሆነ የሃያ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ጠይም ዘለግ ያለ መልከ መልካም ልጅ ነው:: ከራሔል ቢሻው ጋር የተዋወቀው ድንገተኛ ሕመም አጋጥሞት በመቱ ካርል ሆስፒታል ተኝቶ እርሷ ደግሞ የኩላሊት ቀዶ ጥገና የተደረገለትን ወንድሟን እያስታመመች ሣለ የሁለቱ በሽተኞች አልጋ ጎን ለጎን በመሆኑ ነበር::

«አይዞህ:: ይኸው አጠገብህ ቀዶ ጥገና የተደረገለት ወንድሜን አታይም፤ አንተን እንኳ እንደሱ የሚያደርግህ አይመ ስለኝም፤ ቅድም ሐኪሙ "ተረጋጋ፤ ያንተ እምብዛም አስቸጋሪ አይደለም " ሲልህ የሰማሁት መሰለኝ:: ነዋሪነትህ በዚሁ በመቱ ከተማ ነው? በዐይን የማውቅህ መስሎኝ» አለችው ደስ በሚያሰኝና ቃና ባለው ንግግር ከራስጌው ቁማ ቁልቁል እያየችው::

አስተያየትና አነጋገርዋ ከጠበቀው በላይ የሆነበት አብነት «አመሰግናለሁ:: ልክ ነሽ ሕመሜ አስቸጋሪ አይደለም÷ ታይፎይድ ነው፤ መድኃኒቱን ስጨርስ የምወጣ ይመስለኛል፤ የመጣሁት ደግሞ ከአዲስ አበባ ነው::» አላት ሸቅብ ዐይኗ ላይ ዐይኑን ተክሎ ከውስጧ ጹሑፍ የሚያነብ መስሎ::

«ወይኔ ወንድሜን:: የሰው አገር ሰው ሁነህ ነዋ የምትጨነቀው::»

«እኔ? ጭንቀት እንኳ የለብኝም፤





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

በርካታ ወንድሞች፣እኅቶች አባቶችና እናቶች አሉኝ፤ የመቱ ሕዝብ በሙሉ ቤተ ሰቤ ነው፡፡»

«እውነቱን ተናገርክ፥ በራፍ ላይኮ በርካታ ሰዎች «መምህሩ እንዴት ነው?» ይላሉ፤ አንተ ነህ እንዴ?»

«አታውቂኝም ማለት ነው? እንዲያውም አንቺ ነሽ የሰው አገር ሰው»

«አልቀረብህም፥ እትብቴ ከተቀበረበት ከተማ ደግሞ ወደ የት ልትወስደኝ ነው፡፡ ቅድም በዐይን አውቅሃለሁ አላልኩህም»

«በቃ ከዛሬ ጀምረሽ በደንብ ከነስሜ ዕወቂኝ አብነት ሽፈራው (ሣህለ ሚካኤል) እባላለሁ፡፡ የምትገኝበትና በአገልግሎት የምትሳተፍበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የት ነው?»

«ስሜ ራሔል ቢሻው እባላለሁ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንኳ አዘውትሬ አልሄድም፡፡ ለቅዳሴ ግን ልደታ ለማርያም ቢሻሬ ነው የምሔደው»

«እግዚአብሔር ፈቅዶ ወንድምሽም እኔም ከሆስፒታል በደኅና ከወጣን መልካም ፈቃድሽ ቢሆን በሠርክ ሰዓት በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ብትከታተይ እኅትና ወንድም እንሆናለን፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትም እንዴት ከሁሉ በልጦ እንደሚሻል ትረጂዋለሽ፡፡ ደግሞ ይህ አጋጣሚ ለበጎ ነውና አደራሽን፡፡»

«ጉባኤ የሚሉትን ነገር እንኳ አታንሣብኝ፤ ግን አንተ ድነኅ ስታስተምር ለማየት እመጣለሁ» «እኔን ለማየት ሳይሆን የአምላካችንን ቃል ለመስማት ብትመጪ በጣም ደስ ይለኛል፡፡»

«ለማንኛውም አንተ ደነኅ ተነሥ፡፡ አይዞህ እጠይቅሃለሁ፥ በል ዶክተሮቹ ስለ መጡ ልውጣ፡፡»

■ ■ ■

«ስሚ የኛ እመቤት፥ ያንቺ ቤተ ክርስቲያን እስከ አምስት ሰዓት ነው ወይ? ወይስ ምን ያህል ነው አንቺን በመጠበቅ በርሃብ የምንቀጣው፡፡ ሰው ሁሉ ወደ ቤቱ ከተመለሰ ጊዜ የለውም፡፡ አንቺ እንደ ዋልሽ እዛው አታድሪም፥ ይሻላል ተጠቃሎ መግባት» አሉ አቶ ቢሻው ነጠላዋን አጣፍታ ለብሳ የጸሎት መጽሐፍዋን እንደ ያዘች ከቅዳሴ በኋላ በሰንበት ት/ቤት መርሐ ግብር ቆይታ ስትገባ፡፡

«አባባ ለምን ትቆጣለህ፡፡ ዛሬ ነው እንዴ ልዩ የሆነብህ? እኔ ሰንበት ት/ቤት መከታተል ከጀመርኩኝ ይኸው ሁለተኛ ዓመቴ፡፡ የምመጣውም በዚህ ሰዓት ነው፡፡ ደግሞ ልጄ ቁም ነገር ጀምራለች፤ እንዳላልከኝ ዛሬ የሚያበሳጭህ በተቀደሰ ሥፍራ መዋሌ ሆነ» አለችና ወደ መኝታ ክፍልዋ ገባች፡፡

የአባቷንና የእርሷን ንግግር የሰሙ እናቷ ከማዕድ ቤት ፈጠን ብለው በመምጣት ወደ ሳሎን ለመሔድ ራመድ ስትል ከኋላ ቀሚሷን ጎተት አድርገው ወደ ኋላ መለሷት

«ምነው? እማዬ» አለች ሥራቸው ግራ አጋብቷት፤

«ነይ አባትሽ ዛሬ በጣም ተናደዋል» አሉ ድምፃቸውን ቀንሰው በሹክሹክታ

«ለምን ተናደደ፥ በሽማግሌዎች መምጣት ነው እንዴ?»

«ኧረ በፈጠረሽ እንዳይሰማሽ» ብለው አፋቸውን በእጃቸው ተመተሙ፡፡

«እና ይህ ምኑ ያናድዳል? እኔና አንቺ ጉዳዩን ተማምነንበታል አይደል እንዴ» አለች፡፡ ድሮም ቢሆን የሰውን አሳብ አይቀበልም ደግሞ ይህ ለሁለታችሁም ወግና መዓረግ ነበረው፡፡ አገር አስለቸች የተባልኩት ልጃችሁ እግዚአብሔር ወደ ቤቱ ጠርቶኝ ለዚህ ቁም ነገር መታደሌ ሁለተኛ መወለድ ነው፡፡»

«አባትሽ መች ይኸን አሰበ፤ ቄሶቹንም አቅልሎአቸው ነው የተመለሱት'ኮ!»

«ለምን? እነርሱ ምን አጠፉ? አክብረውት መጡ እንጂ እኔ የማልሻው ብር አምላኪ ወዳጅ እንዲላክለት ፈለገ እንዴ? ስሚ እማማ እኔኮ የሚጠቅመኝን መምረጥ እችላለሁ፡፡ ልጅ አይደለሁም፤ የሃያ አራት ዓመት ወጣት ነኝ፤ እናንተን ለማክበርና የሃይማኖት ፍሬነቴን ልመሰክር ነው እንጂማ ሱቅ እየጠበቅሁ አላፊ አግዳሚውን ልቆጥር አይደለም፡፡ ስለዚህ እንደ ድሮው መዝለሌ ነበር ክብራችሁ? ብታውቁበት ይህ ነው ክብርና ሞገሳችሁ፡፡ እናንተ በተለይ አባዬ ይህን የማይቀበል ከሆነ ቤተ ክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ናት በወግ በማዕረጉ አጊጣ ትድረኛለች፤ ኋላ ግን የሚቆጨው እሱኑ ነው፡፡» በማለት በቀጥታ ሳሎን ሶፋ ላይ ቁጭ ወዳሉት አባቷ ሔደች፡፡

አባቷ ከጓዳ ውስጥ የነበረውን የሁለቱን ንግግር ልቅም አድርገው ስለ ሰሙት ገና ብቅ ከማለቷ «የኛ ክርስቲያን የለፈለፍሽውን ሁሉ ሰምቻለሁ፤ አዛኘና ናዛዥ ያደረገሽ ከቶ ማን ነው? ደግሞ ሕይወትሽ የተቀየረው ለባል ነው እንዴ ይህን ያህል የምትፈነጭው፥ አታገቢም! አታገቢም! ነው ቃሌ፤ የኛ ባለሀብታም ቤተ ክርስቲያን ከኛ የለቃቀሙትን ለልጅ ማጋቢያ ሊያደርጉ ነው፤ ተማክረሽ ነዋ ቄሶቹን ያስላካችሁት እስቲ ድጋሚ እዚህች በራፍ ድርሽ ይበሉ፥ እኔ ቢሻው አይደለሁም» አሉ በንዴት ጦፈው በፊታቸው ያለውን ጠረጴዛ በጡጫ እየደበደቡ፡፡

«አባባ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም» ይላል የእግዚአብሔር ቃል፡፡ መልካም የሆነውን ነገር ማደናቀፍ ጥሩ አይመስለኝም፡፡ ደግሞ በሌላ ምዕራፍ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል አንድ አካልም ይሆናሉ» ይላል፡፡ እኛም ከዚህ ቃል ውጭ አይደለንም፤ ግን ያንተን ትእዛዝ ማክበር የግድ ይለኛል እንጅ ንቀት አይደለም፡፡» አለች በረጋና በሚያባብል አቀራረብ፡፡

«እስቲ ንትርኩን አቁሙና ቁርስ ቀማምሱ፥ ሰዓቱ ወደ ምሳው ቢጠጋም» በማለት እናትዬው ጥሩ የሥጋ ፍርፍር ከዳቦ ጋር የምግብ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጡ፡፡

■ ■ ■

አብነት ከሆስፒታል በሰላም ወጣ፡፡ የራሔልንም ወንድም ድኖ ወደ ቤቱ እስከ ተመለሰ ድረስ በመጠየቅ ጥሩ ዝምድና አፈራ፡፡ ራሔልንም ጠንካራ ምእመንና የሰንበት ት/ቤት አባል እንድትሆን በማድረግ ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት መምራት ከጀመረች ሁለት ዓመት አለፋት፡፡ በዕለት ተዕለት ግንኙነታቸው እሱ ፍላጎቱና ዕቅዱ ባይሆንም ከእርሱ መለየት ከመንፈሳዊ ሕይወት መዛል እንደ ሆነ አጥብቃ እየነገረችው ነበር ለዛሬው ትልቁ ቁም ነገር ለመድረስ የወሰኑት፡፡

«ራሔል እኔ'ኮ ለትዳር ብመኝሽም ሁኔታዎች አይፈቅዱልኝም፤ ጠንካራ መንፈሳዊ እኅት መሆንሽ ቢያኮራኝም ቤተ ሰቦችሽ ከኔ ጋር ያለውን ጋብቻ የሚቀበሉት አይመስለኝም፡፡» አላት በአንድ የሰንበት ቀን በቤተ ክርስቲያን ታዛ ስር ቁጭ ብለው፡፡

«አቢ፥ እኔ ዛሬ ሰው መሆኔ ያንተ ያልተቋረጠ ጥረት ውጤት ነው፤ ይህ ደግሞ ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ነው፡፡ እኔ ብር አምላኪ አይደለሁም፥ እውነትን ዐውቄአለሁ፤ ፍጹም የከበደ ችግር ቢኖርም መሠናክሉን አልፈን ለቁም ነገር መብቃት አለብን፡፡ ንስሐ አባቴን አማክሬአቸው «ይህማ በእውነት የሚገባ ነው፤ ሽማግልናውን እኛ እንጨርሳለን ነው ያሉኝ፡፡»

«እኔ ግን ይከብደኛል፤ ገንዘብም ቢሆን ያስፈልገኛል፤ ድግስ ጥሎሽ ወዘተ የሚባል ጣጣ የተለመደ ነው፡፡»

«አይደለም የኔና ያንተ ሰርግ ፍጹም አስተማሪ መሆን እንዳለበት ይሰማኛል»

«ይሁና፥ በጸሎት ይበልጥ ልንተጋ ይገባል፡፡ አባቶችንም ማማከር ፈተናዎችንም መቋቋም ይገባናል፡፡»

■ ■ ■

ካህናቱ በሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ተሰብስበዋል፡፡ ራሔልና አብነትም በመካከላቸው ተገኝተው ያዳምጣሉ፡፡

«እኛ ማድረግ የሚገባንን አድርገናል፤ ሁለተኛው ሽምግልናችን ይበልጥ የሚያበሳጭ ነው፡፡ ሆኖም እኛ ለራሔል ክብር ለአብነት ደስታ ስንል ሁሉንም ችለናል፡፡ አሁን ነገሩን ሁለቱም ባሉበት ወስነን ቀጣዩን ሥራችንን ብናቅድ ይሻላል» አሉ አባ መንግሥቱ ዘለቀ የሁለቱም ንስሐ አባት፡፡

«እኛም ከርስዎ የተለየ አሳብ የለንም፤ ይኸው በሽምግልና ብቻ ብዙ ጊዜ ፈጀን፡፡ የሚቀጥለውን ብናደግር ይሻላል» አባ ሀብተ ኢየሱስ ደግመው ተናገሩ፡፡

«ዕድሉን ለኔ ከሠጣችሁኝ በዚህ የአባቶች ውይይት ላይ ከአንዴም ሁለቴ በመሣተፌ በጣም ዕድለኛ ነኝ፡፡ የምትናገሩት ሁሉ ለኔና ለወንድሜ በማሰብ ነው፤ እኔም ከእናቴ ጋር ሁሉንም ነገር ተስማማተን ጨርሰናል፡፡ በጣም ደስተኛ ናት፤ ቀጣዩ አሳባችሁን ሰምተን ወደ ሥራችን እንሠማራ፡፡» አለች ራሔል ከተቀመጠችበት ተነሥታ፡፡

«እኔም ከእኅቴ የተለየ አሳብ የለኝም፤ ጽናቱ ከኔ ይልቅ ለእርሷ የተሰጣት ይመስለኛል፤ በጣም በጣም ደስተኞች ነን የናንተም የአባቶቻችን ትዕግሥት ከአንዴም ሁለቴ ለሽምግልና መመላለሳችሁ ትልቅ ውለታ ነው፡፡ እግዚአብሔር ያክብራችሁ፥ ምክራችሁም ወደ እውነትነት የሚቀየርበት ጊዜ ስለ ተቃረበ ይመስለኛል ከኔ በላይ ደስተኞች የሆናችሁት፡፡ እኔም ማድረግ የሚገባኝን ለመፈጸም እየተሯሯጥኩኝ ነው፡፡ የእናቷ ከፍተኛ ሃይማኖታዊ ፍቅ ርም ለልቤ የበለጠ ጥንካሬን ሰጥቶኛል፡፡ አመሰግናለሁ፡፡»

«መልካም ራሔል በጣም ተጠንቀቂ፥ ምስጢሩ መባከን የለበትም፡፡ ማወቅ የሚገባቸው ሰዎችን ማንነትሽን ሳንገልጽ ከሩቅ አገር የምትመጭ አስመስለን ዝግጅቱ በተለይ ለአብነት እንደ ሆነ የኛ ድርሻን እናዘገጃጃለን፤ ለአባትሽ ጤንነትም አ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስቢላቸው፤ ይህ የእናትሽ አደራ ነው፤ በሉ በርቱ አንተም ለዝግጅቱ ራስህን አበረታታ፤ ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን፡፡ አቡነ ዘበሰማያት፡፡» በማለት ልጆችን በማስናበት የየራሳቸውን የሥራ ድርሻ የሰንበት ት/ቤቱ አጠቃላይ ዝግጅት፣ የሰበካ ጉባኤ የገንዘብና የቁሳቁስ ርዳታ፣ የአዳራሹ ዝግጅት በየክፍሉ እንዴት መጠናቀቅ እንዳለበት ተወሰነ፡፡

■ ■ ■

ዕለቱ እሑድ ጥር አሥራ ሁለት፤ የቅዱስ ሚካኤል በዓል ከወትሮው በተለየ መልኩ ቤተ ክርስቲያኑ በሕዝበ ክርስቲያን ከጫፍ እስከ ጫፍ ተሞልቷል፡፡ ካህናት፣ መነኮሳትና የሦስቱ አድባራት አገልጋዮች የአገረ ስብከቱ ጳጳስ ቀደም ብለው በመቅደስ ተገኝተዋል፡፡ የሁለቱ ወጣቶች መምጫ ሰዓት በመድረሱ ከወዲሁ መቀመጫና ምንጣፍ እየተዘጋጀላቸው ነው፡፡ ራሔል ከቤቷ በቀጥታ ለቅዳሴ የሚሔድ ሰው መስላ ነው ቀደም ብላ በሌሊት የወጣችውና በሰንበት ት/ቤቱ ጽ/ቤት የአብነት ሚዜዎችና የእርሷ ሚዜዎች ተገናኝተው ልብሷን መቀያየር የጀመረችው፡፡ ...ብሩ የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ረጃጅም ...ፍ ለኩሰው፣ በሁለት ረድፍ ቆመው፡-

«ሶበ ሰማእነ ዜናከ፣ መጻእነ ሐቤከ. . .» የሚለውን ወረብ ይወርባሉ፡፡ ሁለቱ ወጣቶች ከሰንበት ት/ቤት በሚዜዎቻቸው ታጅበው ወደ ዘማሪዎቹ ሲቀርቡ እልልታው ደምቆ ተቀበላቸው፡፡ ሚዜዎችም ይዘው ጧፋቸውን ከዘማሪዎቹ ጋር ወረቡን ይበልጥ አደመቁት፡፡ ራሔል ፊቷን ቀላ ባለ ስስ ዐይነ ርግብ ሸፍና ማንነቷን ለመረዳት ያስቸግራል፡፡ በራሳ ቸው ፍላጎት የተዘጋጁት ሁለት የቪዲዮ ቀራጊዎችና የፎቶ አንሺዎች ይህን ትዕይንት ለትውልድ ቀርፆ ለማስቀረት ይሯሯጣሉ፡፡ ሙሽሮቹ በዘማሪዎች መሐል አልፈው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሲገቡ አጠቃላይ ምእመናኑ በደመቀ እልልታና ዝማሬ ተቀበሉዋቸው፡፡ በቀጥታ ወደ ጳጳሱ አጠገብ በመሔድ በመስቀል ተባርከው ከቦታቸው ላይ ቆሙ፡፡ የተክሊል ሥነ ሥርዓት በመልካም ሁኔታ ተከናወነ፡፡ ቃል ኪዳናቸውን ፈጸሙ፤ ቅዳሴው ተከናወነ፣ ጳጳሱ ረጋ ብለው በትረ ሙሴያቸውን እንደ ያዙ ወደ ድምፅ ማጉያው ተጠግተው ቆሙ፤

«የተወደዳችሁ ምእመናን÷ እንደ ምን ሰንብታችኋል?፡፡ ለዚህ ቀን ያደረሰን አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ ... ዛሬ ለሁላችንም ድርብ በዓል ነው፡፡ በዚህም ላይ ታላቅ ታሪካዊ ቀን፡፡ እኛ በልጆቻችን አስተማሪ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት በጣም ተደስተናል፡፡ አጠቃላይ ሁኔታውን የምናውቅበትና የምንማማርበት በማጠቃለያው በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ባለው አዳራሽ ትልቅ ዝግጅት ስላለን ሁላችሁም በዚህ ዝግጅት ላይ እንድትገኙ እጠይቃለሁ፡፡» በማለት ጥሪያቸውን አስተላለፉ ወዲያውም ዲያቆኑ «አድንኑ» ብለ ሠርሆተ ሕዝብ ሆነ፡፡ የሰንበት ት/ቤቱ መዘምራንም በውስጥ የድምፅ ማጉያው ታግዘው፡-

«ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ!» በማለት እየዘመሩ ወደ አዳራሽ አጅበው ይዘዋቸው ሔዱ፡፡

የአዳራሹ መድረክ በሚያብረቀርቅ መጋረጃ ተሸፍኖአል፤ የከተማው የቅዱስ ሚካኤል ማኅበር አባላት የሆኑ ነጋዴዎች ለወርኃዊ ዝክራቸው የአዳራሹን ጥግ በከፊል ይዘው ተቀምጠዋል፡፡ ምእመናን በተላለፈው መልእክት መሠረት ቦታ ቦታቸውን በመያዝ፣ ግማሾቹ ደግሞ ተጠጋግተው በስተመጨረሻው ማዕዘን ላይ ቆመዋል፡፡ ከዚህ የተረፉት ደግሞ በየመስኮቱ ሆነው ወደ ውስጥ ይመለከታሉ፡፡ በአዳራሹ የተከፈተው መዝሙር «ቃና ዘገሊላ» የሚለውን ዝማሬ እያስተጋባ ድምቀቱን ጨምሮታል፡፡ የሰበካ ጉባኤውና የሰንበት ት/ቤቱ ያዘጋጀው ምግብና መጠጥ ሲስተናገድ ደፋ ቀናው ተጧጡፏል፡፡ ለወርኃዊ ዝክር ዘግይተው የመጡት አቶ ቢሻውና ወ/ሮ አስቻለች በራፍ ላይ ቁሞ ይጠብቃቸው በነበረው ዲያቆን እየተመሩ ፊት ለፊት በተዘጋጀላቸው ክፍት ወንበር ላይ ሔደው ተቀመጡ፡፡ ምግብና መጠጡ መስተናገዱን ቀጥሎአል፡፡ መጋረጃው ግን አሁንም እንደ ተዘጋ ነው፡፡ ጳጳሱ ሞገስ በተሞላበት ሁኔታ ከመጋረጃው ውስጥ ብቅ ሲሉ ሕዝቡ ሁሉ ብድግ ብሎ ተቀበላቸው፡፡ ተቀመጡ በሚል ምልክት ሕዝቡን ቁጭ አደረጉትና ንግግራቸውን ጀመሩ፡፡

«ዛሬ ከዚህ መጋረጃ ጀርባ ያለውን ትልቅ ተአምር ቅዱስ ሚካኤል በተራዳኢነቱ ያከናወነው ድንቅ ሥራ ነው፡፡ ሰው ሁሉ ለአምላኩ ፍጹም ራሱን ሰጥቶ ቢተጋ ምንኛ ባማረበት ነበር፡፡ ወገኖቼ! እኔ የነዚህን ሁለት ወጣቶች ክርስቲያናዊ ጽናት የምናገርበት አንደበት የለኝም፡፡ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለቤተሰቦቻቸው ኩራቶች ናቸው፡፡ ይህንን ዝግጅት ስናቅደውና ስንጀምረው አጠፋችሁ፣ አበላሻችሁ ትሉናላችሁ ብለን ሰግተን ነበር፡፡ ብዙዎቻችሁ ግን ተደስታችሁ በፍጹም ክርስቲያናዊ ስሜት ረዳችሁን፤ ውጤቱም ሠመረ፡፡ አሁንም ወጣቶቹን እግዚአብሔር ይባርካቸው፤ እናንተንም ውለታችሁን ቅዱስ ሚካኤል ይመልስላችሁ፤ የኔን በዚሁ ላብቃና ቀጣዩን ሒደትና ሽልማት ታዩታላችሁ፡፡ ተባረኩ! ተቀደሱ!» በማለት ረጋ ብለው ወደ መጋረጃው ውስጥ ዘለቁ፡፡

የሽልማቱ ሥነ ሥርዓት በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በርካታ ስጦታዎች የሰፊውን ጠረጴዛ ገጽ ሞልተውታል፡፡ ሙሽሮቹ መጋረጃው እንደ ተከፈተ ባማረ የሰርግ ልብስ ተውበው የራሔል በቀዩ ዓይነ ርግብ እንደ ተሸፈነች ትታያለች፤ እልልታና ጭብጨባው ሊያቆም አልቻለም፡፡ ከሙሽራው ሚዜዎች አንዱ ነጠላውን ካስተካከለ በኋላ ከጳጳሱ ጉልበት ስር ጎንበስ በማለት ቡራኬ ተቀብሎ መናገር ጀመረ፡፡

«የተከበራችሁ ምእመናን፡- የቤተ ክርስቲያናችን ፍሬዎች የሆኑትን ሁለት ወጣቶች የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ለመታደም በመምጣታችሁ ደስታችን ከፍ ያለ ነው፡፡ በርካታዎቻችሁ ሙሽራውን ታውቁታላችሁ፤ ሙሽራዪቱን ለመመልከት እንደ ጓጓችሁ አስተውላለሁ» አለ ወደ እነ አቶ ቢሻው በጥንቃቄ እየተመለከተ፡፡ አቶ ቢሻው የልጅቷን ማንነት ማወቅ ካልቻሉት አንዱ ናቸው፤ ወደ ባለቤታቸው ጆሮ ጠጋ ብለው፡-

«አስቻለች÷ እነዚህ ምንኛ የተባረከ ቤተሰብ ያፈራቸው ናቸው፣ ጳጳሱ ሳይቀሩ ተገኝተው እንዲህ የሚያደንቋቸው? ልጁም የጥሩ አጥንት ዘር ይመስላል፤ እርሷን ለምን ፊቷን አይገልጧትም አቤት! አቤት! ድምቀታቸው» አሉ፡፡

«እኛማ ብንጠየቅ አሻፈረኝ አልን፤ ክብራችንን አናናቅነው፤ የታደሉትማ እንዲህ ይመረቃሉ እኛ ደሞ . . .»

«እኔ የእኛ እንዲህ የሚሆን መች መሰለኝ፤ አሁንማ ለኔም ጥሩ አይደለም፤ እሺ ብል ካህናቱ ይታዘቡኛል» አሉ፡፡

«በዚህም መሠረት» አለ ሚዜው ንግግሩን በመቀጠል «ሙሽራዪቱን የምናውቅበት ሰዓት ተቃርቧል፡፡ የሙሽራዋን ዐይነ ርግብ ገልጠው ያዘጋጁትን ሽልማት የሚሰጡልን እናታችን ወ/ሮ አስቻለች ደስታ! » በማለት ድምፁን አጉልቶ ተናገረ፡፡ ስማቸው እንደ ተጠራ ከጎናቸው ሲነሡ ግራ የተጋቡት አቶ እንደሻው ዐይናቸውን ከሚገለጠው ዐይነ ርግብ ላይ ተከሉ፡፡ ወ/ሮ አስቻለች በቀጥታ በመሔድ የሙሽራውን ግንባር በመሣም ዐሥራ አምስት ግራም ወርቅ ከአንገቱ ሲያጠልቁለት እልል ታው ተጀመረ፡፡ የሙሽሪትን ፊት የሸፈ ነውን ዐይነ ርግብ ገለጥ አድርገው ለሷም ተመሳሳይ ግራም የአንገት ሀብል አንገቷ ውስጥ አጥልቀው ጉንጯን ሲስሚት እልልታው የቤቱን ጣሪያ አነቃነቀው፡፡ ከውጭ የርችት ችቦ እንደ መትረየስ ተንጣጣ፤ ጳጳሱ በያዙት መስቀል ባረኳቸው፤ እናታቸውን ከመሐል አድርገው ከመድረኩ ወደ አቶ ቢሻው መጡ፡፡

አቶ ቢሻው ዐይነ ርግቡ ሲገለጥ ራሳቸውን ማመን አቅቷቸው ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ስሜትና ድንጋጤ ከተቀመጡበት ወንበር ተንሸራተው በጉልበታቸው ተንበረከኩ፡፡ እጃቸው ወደ ሰማይ ተሰቅሎ በማይሰማ ድምፅ፡- አጉተምትመው «አቤት ጉዴ፣ አቤት ጉዴ፣ ምነው እግሬን በሰበረው ኖሮ ጌታዬ፤ የዛሬውን ማረኝ፡፡ የዛሬውን ማረኝ፡፡ የንስሐ ዕድሜ ስጠኝ ንስሐ...»አሉ ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ፡፡

«ይነሡ! ይነሡ አቶ ቢሻው ይነሡና ይመርቋቸው» አሉ ጳጳሱ፡፡

«አጥፍቻለሁ ይማሩኝ አባቴ፣ ይማሩኝ! ይማሩኝ! አባቴ እኔ እንዲህ ያለ ክብር መሆኑን መች ተረድቼ÷ አጉል መካሪ ሰምቼ ነው፡፡ ይቅር በይኝ ራሔሌ! ማሪን! ይህን ሁሉ ክብር ያጣሁት ራሴ ነኝ፡፡ አንቺንማ እግዚአብሔር አክብሮ ቀደሰሽ፤ እባክዎን አባታችን ለዚህ ሕዝብ አንድ ቃል እንድተነፍስ ይፍቀዱልኝ፡፡» ብለው ከጳጳሱ እግር ስር ድፍት አሉ፡፡

«ይነሡና ይናገሩ፡፡ ይቅር ለእግዚአብሔር ብለናል ይነሡ፡፡»

አቶ ቢሻው እግራቸው እየተምታታ ከሙሽሮቹ ፊት ለፊት ከጳጳሱ ጎን መድረኩ ላይ ቆሙ፡፡

«ስሙኝ ወገኖቼ÷ ካህናቱንም ልጁንም አሳዝኛለሁ÷ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ፡፡ የዛሬውን የንስሐ ግዜ ስለ ሰጠኝ ካህናት አባቶቼን ይቅርታ እጠይቃለሁኝ፡፡ ከዚህ ሌላ ለነዚህ ልጆች በተለይ ለሙሽራው ልዩ ስጦታ ዐሥር ሺህ ብር የጎጆ መውጫና አዲስ ለጀመራችሁት የሰንበት ት/ቤት ማጠናቀቂያ ዐሥራ አምስት ሺህ ለመስጠት ቃል እየገባሁኝ ባለቤቴን እግዚአብሔር የሃይማኖት ፍሬ ያድርጋት፤ እንደኔ ብትጠም መች ይህን ታምር ዐይኔ ያይ ነበር፡፡ እንግዲህ ለይቅርታው ማጽኛ የዛሬ ዐሥራ አምስት ቀን አባታችን መልካም ፍቃድዎ ቢሆን እዚህ አዳራሽ መልስ ጠርቻለሁኝ»

«ይባርክዎት. . . ይቀድስዎት ዕድሜ ይስጥዎት ጳጳሱ መረቁ እልልል! . . . እልልል!. . . እልልል! የአዳራሹና ከአዳራሹ ውጭ የነበረው ምእመን በሙሉ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «የዛፍ ጉዲፈቻ» በወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም

ዲ.ፋሲል አሰረስ



የመልአከ አድኅኖ ወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ቤተ ክርስቲያን

መልአከ አድኅኖ ወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በ14ኛው ምዕተ ዓመት ከተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በደብረ ብርሃን ከተማ መግቢያ ወደ ጅሩ መስመር በሚወስደው መንገድ 22 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው::

ወደ ገዳሙ የሚወስደው መንገድ ወደ ጅሩ ከሚያመራው መንገድ ጋር መንትያ ሆኖ በቀኝ በኩል የተጉለት ከተማ ባሻጋሪው የበዞና እና የሞጆ አፋፍ ይታያል:: በግራ በኩል ከጫጫ ጅረት ማዶ ያለው የአብቹና የዋዩ ሜዳ የሚገኝ ሲሆን በሰሜን አቅጣጫ የጅሁር ቀበሌ ይታያል:: በዘመናቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንደታነፁና የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፉ በሚታመንባቸው በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ጊዜ እንደ ተመሠረተ የሚነገረው ይህ ገዳም በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ስም ታንፆ ለአካባቢው ምእመናን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ ነበር::

በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ግራኝ አሕመድ ደብረ ብርሃን ከተማን ማዕከል በማድረግ ተጉለትን፣ ወግዳ፣ መርሐ ቤቴን፣መንዝ ገዳምን፣ ይፋትን በመቆጣጠር አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቃጥል ንዋያተ ቅድሳትንና ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲመዘብርና ሲያወድም የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳምም የጥቃቱ ሰለባ በመሆን ጠፍቷል::

ጉር ማለት ብዙ ድንጋይ የተከመረባት ሥፍራ ሲሆን ወርቅ ጉር የተባለውም ብዙ ወርቅ የተከመረበት እንደ ማለት ነው:: /መልአከ አድኅኖ መጽሔት÷ ታኅሣሥ 1989 ዓ.ም/:: ይህ ማለት ለንጉሥ ከተማ ሁኖ እጅ መንሻ ወይም ግብር እና ገንዘብ የሚሰበሰብበት ቦታ እንደ ነበር ያመለክታል:: ይህ ገዳም በወቅቱ በታላላቅ የቤተ ክርስ ቲያን ምሁራን ትምህርት ሲሰጥበትና በጠበልም ብዙ ገቢረ ተአምራት ይፈጸምበት እንደ ነበር ይነገራል::

ጊዜው ደርሶ ገዳሙ እንደ ገና እስኪሠራ ድረስ የቅዱስ ገብርኤል ጽሌ በፈንጣጣ ዋሻ በሚገኘው በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በደባልነት ቆይቷል:: በዚህ ወቅት በየዓመቱ ታኅሣሥ 19 ቀን በጠበሉ ቦታ ድንኳን በመትከል ሥርዓተ ንግሥ በማድረግ ይከበር ነበር::

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ክብረ በዓል ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ በአካባቢው ሕመም እንደ ጠፋና በክረምት ወራት አልፎ አልፎ በማዕበል ይመቱ የነበሩ መሬቶች ከአደጋው መዳናቸውን እንዲሁም በጠበሉ ብዙ ፈውስ መገኘቱን የአካባቢው ምእመናን ይናገራሉ::

የቀደሙት አባቶች የቅዱስ ገብርኤልን ጽሌ ከግራኝ ወረራ ለማዳን ከቤተ ክርስቲያኑ ደቡብ ምዕራብ በኩል ባለው ወገብ ላይ በሚገኘው ዋሻ ከሌሎች የከበሩ ንዋያት ጋር እንዳስቀመጧቸው ይነገራል::

በቤተ ክርስቲያኑ ጠበል ዙሪያ በሚገኘው ዐጸድ ስር ጸሎት በማድረግ ላይ የሚገኙት መነኮሳት ጽሌው ይገኝበታል ተብሎ በሚነገርበት ቦታ የተለያዩ ምልክቶች እናያለን በማለት ይናገራሉ::

ይህ ገዳም በግራኝ ወረራ ምክንያት ጠፍቶ÷ ጠፍ ሆኖ ቢቆይም የበቁ አባቶች ይህ ቦታ ስብሐተ እግዚአብሔር ይደረግበታል:: መሥዋዕተ እግዚአብሔር ይሠዋበታል በማለት ትንቢት ሲናገሩ ቆይተዋል:: ምኞቴን ቢያስፈጽመኝ አሳቤን ቢያሟላልኝ የቅዱስ ገብርኤልን ጽሌ ከጥንት ሥፍራው እመልሳለሁ በማለት ያላቋረጠ ጸሎት ያደርጉ የነበሩ ብላታ ደምሴ ወርቅ አገኘሁ ከወንድማቸው ከአቶ መኮንን ወርቅ አገኘሁ ጋር በመመካከር በሐረርና በአዲስ አበባ የሚገኙ ወዳጆቻቸውን በማስተባበር ገዳሙን ለመሥራት ተነሣስተዋል::

እግዚአብሔር የፈቀደው ጊዜ ሲደርስ ቤተ ክርስቲያኑ እንደ ገና ተሠርቶ ሚያዝያ 19 ቀን 1955 ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል::

እግዚአብሔር ለጠቢቡ ሰሎሞን «ዐይኖቼም ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ» መ.ነ.ቀ.9÷3:: የተናገረበት፣ ስሙ የሚጠራበት፣ ሥጋውና ደሙ የሚታደልበት ቦታ የተቀደሰ ነውና የተለያዩ ገቢረ ተአምራት ይፈጸምበታል:: «ዜና ቤተ ክርስቲ ያን ዘኢትዮጵያ» የካቲት 18 ቀን 1959 ዓ.ም ባወጣው እትሙ ስለ ወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም እንዲህ ሲል ዘግቦ ነበር::

«ጥር 20 ቀን ቅዳሜት ለእሑድ አጥቢያ ከምሽቱ 5 ሰዓት ገደማ ላይ አንዳንድ ካህናት ንዋም አድርገው ጥቂቶቻችን ተቀምጠን ሳለን ከቤተ ክርስቲያኑ ጉልላት ላይ የሚያስደነግጥ ታላቅ ብርሃን ተገለጠ:: እኛም ቤተ ክርስቲያኑ በእሳት ተቃጠለ ብለን በድንጋጤ ተነሥተን ብናይ እግዚአብሔር የላከውና የገለጠው ብርሃን እንጅ ቃጠሎ አለመሆኑን አውቀን በተደረገው ተአምር እያደነቅን ተመለስን::» /አቶ ተክለ ጻድቅ፣ አቶ ነጋሽ ሀብተ ሚካኤል፣ አቶ የኋላ ወርቅ ማሞ በቦታው ተገኝተው እንደ ተናገሩት/::

ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ይቀጥላል፡- «በተለይ ነጋሽ ሀብተ ሚካኤል የተባለው እንደ ገለጠው ለመናገር ፈርቼ ዝም አልኩ እንጂ ይህ የአሁኑ ብርሃን ከመገለጡ በፊት መሰንበቻውንም በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተደጋገመ ብርሃን ሲወርድበት ተመልክቻለሁ» ብሏል::

የአካባቢው ገበሬዎችና ሽማግሌዎች እኛ ብርሃን ሲንቦገቦግ ዐይተናል:: ነገር ግን በወቅቱ ያረፉት የአለቃ ወርቅ አገኘሁ ሰዓተ ሌሊት ስለ ተያዘ ልጆቻቸው ኤሌክትሪክ እያበሩ መስሎን ነበር በማለት መግለጣቸውን ጋዜጣው ይናገራል::

ይህ ጥንታዊና ባለ ታሪክ ገዳም ሕንፃው ከዘመኑ ብዛት የተነሣ ለአገልግሎት ምቹ ባለመሆኑና በዘመናዊ መልክ ለመገንባት በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የአካባቢው ተወላጆችና የአካባቢው ምእመናን በመነሣሣት ይህን የሕንፃ ግንባታ ሥራ የሚያስተባብር ኮሚቴ አቋቁመው እንቅስቃሴ ጀምረዋል:: ታኅሣሥ 19 ቀን 1989 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የሰሜን ሸዋ አገረ ስብከት ሊቀ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባልና የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል፡፡

የተቋቋመው ኮሚቴ በአዲስ አበባ፣ በደብረ ብርሃንና በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ምእመናንን በማስተባበር ሕንፃውን በዘመናዊ መልክ በመሥራት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገው በ1993 ዓ.ም ሕንፃ ቤተ ግንባታው ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

የበጐ ነገር መሠረት የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የልማት እንቅፋትና የድህነት ምክንያት ተደርጋ ስትጠቀስ ይሰማል፡፡ ይህ ግን ታሪክን ካለማወቅና የቤተ ክርስቲያንን ዓላማና ተግባር ካለመረዳት የመነጨ እንጅ «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ» ሮሜ.12÷11 በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ለሥራ የምትፋጠን መሠረተ ልማት ያለባት ነች፡፡ በየገዳማቱ የሚገኙ መነኮሳት የሥራ ክፍፍል አድርገው የወንድ የሴት ባለ ማለት ወንዶች በማዕድ ቤት ሥራ፤ ሴቶች በግብርና ተግባር ተሠማርተው ማየት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነበረና ያለ ወደ ፊትም የሚኖር ነው፡፡

የወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሕንፃ አሠሪና የልማት ኮሚቴ ሕንፃውን በመሥራት ብቻ ሳይወሰን የዛፍ ተከላ መርሐ ግብር በማዘጋጀት «የዛፍ ጉዲፈቻ» በሚል ስያሜ ታላቅ ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡

«ጉዲፈቻ» ቃሉ ኦሮምኛ ነው፤ ለአንድ ሰው አሳዳጊው ሁኖ ሲረከቡት «ጉዲፈቻ» ይባላል፡፡

ጉደታ..........ያድጋል
ጉዲፈቴ.........አሳደገ
ጉዲሳ ............አሳዳጊ
ጉዲና ...........ዕድገት
ጉዲፈቹ.........ማሳደግ
ጉዲፈቻ......ማደጐ ማለት ነው፡፡

«የዛፍ ጉዲፈቻ» ማለት ደግሞ ዛፍን ለአንድ ሰው አሳዳጊው ሁኖ ሲረከቡት የሚቀጸል ስም ነው፡፡ አንድ ሰው በሥጋ ለማይወልደው አሳዳጊ ሲሰጥ «የማደጐ ልጅ» እንደሚባለው የዛፍ ችግኝ ለአሳዳጊ የማደጐ ዛፍ ወይም ደግሞ የዛፍ ጉዲፈቻ ይባላል፡፡ የመልአከ አድኅኖ ወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የልማትና ሕንፃ አሠሪ ዐቢይ ኮሚቴ የዛፍ ተከላ መርሐ ግብር አለው፡፡

በየዓመቱ ሐምሌ 18 ቀን ለወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አካባቢ ነዋሪዎች «የዛፍ ተከላ ቀን» ነው፡፡ ከተለያዩ ችግኝ ጣቢያዎችና በስጦታ ወይም በግዢ የሚገኙትን ችግኞች ወደ ወርቅ ጉር ቀበሌና አካባቢ ኮሚቴ በመውሰድ የአካባቢውን ሕዝብ ባሳተፈ ሁኔታ ይተከላል፡፡

የኮሚቴው አባል የሆኑት አቶ በየነ ሞገስ እንደ ገለጹልን የዛፍ ተከላው መርሐ ግብር የሚከናወነው በሚከተለው ሁኔታ ነው፡፡

ለዛፍ ተከላው የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ኮሚቴው የሚሸፍነው በዓሉን ለማክበር ከሚመጡ ምእመናንና በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚገኙ የዓላማው ደጋፊዎች ከሚሰጡት ርዳታ ነው፡፡

ርዳታ ሰጪዎቹ ለአንድ ዛፍ አንድ ብር በዓመት ድጋፍ እንዲያደርጉ ሁኖ እንደ ዐቅማቸውና ፍላጐታቸው ከ50-200 የዛፍ ችግኞችን ስፖንሰር ያደርጋሉ፡፡

አሠራሩም አንድ ገበሬ በዓመት 300 ዛፍ በጉዲፈቻ ወይም በማደጐ እወስዳለሁ እከባከባለሁ ቢል 300×0.80 = 240 ብር ያገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 10 ወይም 15 ገበሬዎችን የሚቆጣጠር በመመደብ የተጠቀሱት ዛፎች በትክክል በክብካቤ መያዛቸውን እንዲቆጣጠር ይደረግና በእያንዳንዱ ዛፍ 0.20 ይሰጠዋል /ይከፈለዋል/፡፡

የዛፍ ተከላውን ጥቅም አቶ በየነ ሞገስ ሲገልጡ፡-

- ❖ በደን መመናመን ምክንያት የተራቆተው መሬት ለምነቱ የሚመለስበት ሁኔታ ይኖራል፡፡
- ❖ ገበሬውና ቤተሰቡ ተጨማሪ ገቢ ያገኛሉ፡፡
- ❖ አዳጊ ሕፃናት ወላጆቻቸው ለዛፍ ክብካቤ ሲያደርጉና በዚህ ጥቅም ሲያገኙ ለደን ፍቅር ያድርባቸዋል በማለት ያብራራሉ፡፡

ኮሚቴው ሥራውን ሲጀምር በአካባቢው የሚገኘው ነዋሪ ለመርሐ ግብሩ የነበረው ተቀባይነት እስከዚህም እንደ ነበር አቶ በየነ ሞገስ ገልጠው ከዓመት ወደ ዓመት ግን ጥቅሙን በመረዳት የዛፍ ተከላውን ቀን በጉጉት የሚጠብቁ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ለዚህ ሥራ ቀጣይነት ድጋፍ ለማድረግ ርዳታ ለሚለግሡ ሁሉ «ለወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም÷ የተንቀሳቃሽ ሒሳብ ቁጥር 48÷ አቢሲኒያ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ» ብለው መላክ ይችላሉ፡፡

አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ከሚታወቁበት አንዱ ዙሪያቸው ጥቅጥቅ ባሉ አገር በቀል ዛፎች የተከበቡና የአእዋፍ መጠለያ መሆኑ ነው፡፡ ይህንን የሆነውን ደን ለተመለከተው እጅግ የሚያስደስት፣ መንፈስን የሚያድስ እና ለጸሎት ምቹ ነው፡፡

በወርቅ ጉር ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ልማት ኮሚቴ እየተከናወነ ያለው ተግባር ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ሌሎችም ደንን በዘፈቀደ ከመጨፍጨፍ በመቆጠብ በተለይም ዝርያቸው በመጥፋት ላይ ባሉትና በቤተ ክርስቲያን ቅጽርና ዙሪያ ተወስነው በሚገኙት አገር በቀል ዛፎች ላይ በማተኮር ፈለጋቸውን ቢከተሉ መልካም ነው እንላለን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ሰሙነ ሕማማት...

ከገጽ ፲ የዞረ

መጋረጃ ከሁለት ተቀደደ፤
4. ምድር ተናወጠች፤
5.ዓለቶች ተሰነጣጠቁ፤
6. መቃብራት ተከፈቱ፤
7. ሙታን ተነሡ /ማቴ.27፥45-64/፡፡

በዚህ ዕለት ጌታችን በመስቀል ላይ ሣለ ሰባት የፍቅር ቃላትን ተናግሯል፡፡ እነርሱም ሰባቱ አጽርሃ መስቀል ይባላሉ፡፡

1ኛ. ኤሎሄ ኤሎሄ ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ፤ ማቴ.27፥46፡፡
2. እውነት እውነት እልሃለሁ÷ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትራለህ፤ ሉቃ.23፥43፡፡
3. አባት ሆይ÷ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፤ ሉቃ.23፥46፡፡
4. አባት ሆይ÷ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው፡፡ ሉቃ.23፥34፡፡
5. እናትህ እነኋት÷ እነሆ ልጅሽ፤ ዮሐ.19፥26-27፡፡
6. ተጠማሁ /ዮሐ.19፥30/
7. ተፈጸመ /ዮሐ.19፥30/ ናቸው፡፡

እነዚህ የፍቅር ቃላት ጌታችን ጽኑዕ ፍቅሩን የገለጠባቸው ቃላት ናቸው፡፡ በዕለተ ዓርብ በአደረገው የማዳን ሥራ ጌታችን ዓለምን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከራሱ ጋር ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስታረቀ፡፡ ዕብ.7÷27፡፡ በዚህ ፍቅሩ ለሰቀሉትና ግፍ ለፈጸሙበት አምላካዊ ይቅርታውን አድርጓል፡፡ ጌታችን ወደር በማይገኝለት ፍቅሩ አስቀድሞ ስለ ወደደን እኛም የመጨረሻ ፍቅሩን የገለጸልንን አምላክ ልንወደው ይገባል፡፡ «እርሱ አስቀድሞ ወዶናል እኛ እንወደዋለን» /1ኛዮሐ.4÷19/ እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ፡፡

በመጨረሻም በዕለተ ዓርብ በአንድ ወገን ጥላቻ ቢያይልም በሌላ ወገን ደግሞ ለፍቅሩ የሚሳሱ ሰዎች አልታጡም፡፡ ፍቅሩ አገብሯቸው ከጲላጦስ ፊት ቀርበው ቅዱስ ሥጋውን ከመስቀል አውርደው ለመቅበር ፈቃድ የጠየቁ የጌታችን የመከራ ቀን ወዳጆች ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ ናቸው፡፡ የጌታችንን ሥጋ ከመስቀል አውርደው ደገኛው ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር አኑረውታል፡፡ ይህ ዮሴፍ ዘአርማትያስ የሠራው የጽድቅ ሥራ ዛሬ እኛም በዘመናችን ልንፈጽመው የሚገባ ደገኛ ሥራ ነው፡፡ ዮሴፍ የጌታችንን ሥጋ ከጠላት ዓይን ሰውሯል፡፡ ጌታችን በመስቀል ላይ ሳለ አላፊ አግዳሚው ይገላምጡት ራሳቸውን እየዘበቱ ይነቀንቁበት ነበር፡፡ ዮሴፍ ዘአርማትያስን ከእኒህ ዓይን እንደ ሰወረው ዛሬም ምእመናንና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በክፉ ዓይን ከሚመለከቷት መናፍቃን ልን ሰውራት ይገባል፡፡

## ቅዳሜ

በዕለተ ቅዳሚት ቅድመ ሥጋዌ «ወአዕረፈ እግዚእነ እምኵሉ ዘአኃዘ ይገበር፤ በሰባተኛው ቀን /ቅዳሜ/ እግዚአብሔር ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ» ይላል፡፡ ዘፍ.2÷3፡፡ ድኅረ ሥጋዌ ሁሉን ቻይ የሆነ አምላክ የድኅነት ሥራውን ፈጽሞ በከርሰ መቃብር ዐርፏል፡፡ ከስቅለት በኋላ ያለው ይህ ቅዳሜ በተለያየ ስያሜ ይጠራል፤ ይኸውም፡-

/ወደ ገጽ ፴፪ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዘደብረ በንኮል ገዳም

/ንቡረ እድ ገብረ ዋሕድ ግርማይ



በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነትና ረድኤት የአባታችን የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን ታሪክ መጻፍ እንጀምራለን:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የተወለዱት ቢሐት በምትባል መንደር አካለ ጉዛይ ነው:: አባታቸው ትልቁ ካህን ስንበት ተስፋነ እናታቸው ኂሩተ ማርያም ይባላሉ:: ሁለቱም ጻድቃንና ንጹሓን ሲሆኑ ከከበሩ ወገኖች /ዘሮች/ የተወለዱ ናቸው:: ሁለቱም በፈቃደ እግዚአብሔር የሚመሩና የሚኖሩ እምነተ ጽኑዎች ነበሩ:: ልጅ ግን አልነበራቸውም:: እግዚአብሔርም ልጅ እንዲሰጣቸው ይማፀኑ ነበር:: እግዚአብሔርም ልመናቸውን፣ ልቅሷቸውን ምጽዋታቸውን፣ ለነዳያን የሚሰጡትን የተቀደሰ ትሩፋታቸውን ዓይቶ ስእለታቸውን መሥዋዕታቸውንም ተቀበላቸው:: ይህ መልካም ፍሬ የሆነ፣ መዓዛው እንደ ገነት የሚሸት፣ ከበረሃ አበባ የበለጠ፣ በተለይም በሚያዝያ ወር እንደሚታይና እንደ ሚሸት አበባ የሚሸት ሕፃን ተወለደ፤ እርሱም ለመንግሥተ ሰማያት መሪ የሚሆን ነው::

ሕፃኑ በተወለደ ጊዜም ዘመዶቹ በሙሉ ደስ አላቸው፤ እግዚአብሔርን በመፍራት ተከባከቡት በጥበብም አሳደጉት፤ እንዳደገም የአባቱን በጐች ይጠብቅ ነበር:: አባቱ ደስ እንዲለው ጥሩ ልብስ መርጦ ገዝቶ አለበሰው፤ እርሱ ግን ልብሱን አውልቆ ለአንድ የድኻ ልጅ ሰጠው፤ ከዕለታት አንድ ቀን አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ሰውነቱ በቁስል የተመታ ሰው ዐዩ፣ ልባቸው ተሸበረ አዘኑ፤ የአባታቸውን አህያ አንሥተው ሰጡት፤ በአህያው እየተቀመጠ እንዲሄድ አስበው አባታቸውም የልጃቸውን ርኅራኄ ዐይተው በጣም ደስ አላቸው:: አባታቸው ለሞት በተቃረቡ ጊዜም ልጃቸውን አቡነ መድኃኒነ እግዚእን ጠሩ::

አባቶች ልጆቻቸውን እንደ ሚባርኩ እርሳቸውም ለልጃቸው ብዙ በረከት ሰጧቸው፤ ባረኳቸው፤ ብዙ ጥበብ ለወዲያኛው ዓለም የሚጠቅም ትምህርት በስፋትና በጥልቀት አስተምረዋቸዋል:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በተወለዱ ጊዜ በጀርባቸውና በሆዳቸው በትእምርተ መስቀል /የመስቀል ምልክት/ የነፍስ መድኃኒት የኾነ የመስቀል ቅርጽ ባዩበት ጊዜ አባታቸው ይህ ልጅ በምድርና በሰማይ የተመረጠና የተከበረ ይሆናል ብለው ትንቢት ተናግረውላቸዋል:: ከዚህ በኋላ አከበሯቸው:: በጥረታቸው ያቀዱትን ሁሉ እንዲያደርጉ ሥልጣን ሰጧቸው:: እነሆ ሰባ መጻሕፍት አሉ፤ ለፈቀድከው ለወደድከው ስጥ፤ እንደ ፈለግኸው አድርግ አሏቸው:: ልጃቸው መድኃኒነ እግዚእ ግን ለቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንስጥ አሏቸው:: አባታቸው ደስ እንዳሰኘህ አድርግ አሏቸው::

መድኃኒነ እግዚእም አባታቸውን «ለእኔ እንደ ሆነ በእጅህ የያዝከው በትረ መስቀል ብቻ ይበቃኛል» አሏቸው:: እርሳቸውም ወዲያውኑ የእጃቸውን መስቀል ሰጧቸው:: ከዚህ በኋላ ዐረፉ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የአባታቸውን መሞት ባዩ ጊዜ ገንዘባቸውን ሁሉ ለድኾችና ለችግረኞች ሰጡ፣መጸወቱ:: ወዲያውኑም መላ ዘመናቸውን በምናኔ ለመፈጸም ወስነው ከትውልድ አገራቸው ወጥተው ጉና በተባለው በረሃ በምናኔ ድምፀ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን፣ ፀብአ አጋንንትን ሳይፈሩ 100 ዓመት ከቆዩ በኋላ ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቆብና አስኬማ ተሰጣቸው:: መዓርገ ምንኵስና ከሰጡአቸው በኋላ በቅዱስ ገብርኤል አማካይነት በደመና /በክንፉ/ ወደ ደብረ በንኮል አደረሳቸው:: ገዳማቸው ከገቡ በኋላ አንድነት መሠረቱ:: ሲመሠርቱ በ1312 እስከ 1342 ዓ.ም. ያለው ዘመን በዐፄ ዓምደ ጽዮን በስምንተኛ ዓመተ መንግሥታቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን ቆረቆሩ::

ጻድቁ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ወደ ደብረ በንኮል ደብረ ሣህል ገብተው አዲስ ገዳም ከመሠረቱ በኋላ ምን ምን ዓበይት ተግባራት እንደ ፈጸሙ ገድለ መድኃኒነ እግዚእ ዘደብረ በንኮል በዝርዝር ሲገልጽ እንዲህ ይላል:-

«ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ልደቶሙ ለመነኮሳት፤ በእግዚአብሔር ቸርነት የመነኮሳትን ትውልድ እንዘረዝራለን:: እንጦንስ መቃርስን በቆብ ወለደ፤ መቃርስ ጳኵሚስን በቆብ ወለደ፤ ጳኵሚስ ዘሚካኤልን /አረጋዊን/ በቆብ ወለደ፤ አረጋዊ ማትያስን በቆብ ወለደ፤ ማትያስ ዮሴፍን በቆብ ወለደ፤ ዮሴፍ መስቀል ቤዛነን በቆብ ወለደ፤ መስቀል ቤዛነ ቀዳማዊ መድኃኒነ እግዚእን በቆብ ወለደ፤ ቀዳማዊ መድኃኒነ እግዚእ ዮሐኒን በቆብ ወለደ፤ ዮሐኒን ኢየሱስ ሞዓን በቆብ ወለደ፤ ኢየሱስ ሞዓ ተክለ ሃይማኖትን በቆብ ወለደ፤ ተክለ ሃይማኖት መድኃኒነ እግዚእን በቆብ ወለደ» በማለት ይዘረዝራል::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት መዓረገ ምንኩስናን ተቀብለው የደብረ በንኮልን ገዳም ሲመሠርቱ እንደ ደብረ ዳሞ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ደብረ ሊባኖስ የ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታዋቂ ገዳማት ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍለ ግዛቶች ሕይወታቸውን በሙሉ በምንኩስና በብሕትውና በጸሎትና በቅድስና ማሳለፍ የፈለጉ መናንያን ወደ ደብረ በንኮል ገዳም መጉረፍ ጀመሩ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ከተማሪዎቻቸው ብቃት ያላቸውን መርጠው አምስቱ /ኀምስቱ/ ከዋክብትና ዐሥርቱ ወሰብዓቱ ቅዱሳን ተብለው የተሰየሙትን መነኮሳት መርጠው በአንድ ቀን አመነኰሷቸው:: እነርሱም:-

አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ፣አባ ሳሙኤል ዘቈየጻ፣አባ ሳሙኤል ዘጣሬጣ፣ አባ ያሳይ ዘመንዳባ፣ ፣ አባ ዮሐንስ ዘዘግራናቋ፣ አባ አሮን ዘከቱር፣አባ ኢዮስያስ ዘማኅበረ ማርያም፣አባ ድምያኖስ ዘቤ[...] በኃይላ፣አባ ማማስ ዘጉድጉዳ አባ ገብረ ክርስቶስ ዘተዓሚና፣አባ ያፍቅረነ እግዚእ ዘጉጉቤን ፣አባ ገብር ሔር ዘጋዜን ምንጋጋ፣አባ ኂሩተ ክርስቶስ ዘማይ ሠካይም ፣አባ መርቆሬዎስ ዘሞግዕ፣አባ እንድርያስ ዘአማዐታ፣ አባ መርቆሬዎስ ዘማይሰካይም አባ ገብረ ክርስቶስ ዘማይቡር፣ አባ አብሳዲ ዘዘህ አምባ፣አባ ታዴዎስ ዘባርትርዋ፤

የተባሉ ዕውቅ መነኮሳት በደብረ በንኮል ተምረው በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ እጅ መንኵሰው በመላው ትግራይ፣ በሰሜንና በበጌምድር አውራጃዎች በመሠራጨት የየራሳቸው አዳዲስ ገዳማት በመመሥረት የኢትዮጵያ፣ ገዳማት ቁጥር ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገሩና በመሠረቱዋቸው ገዳማት ሁሉ የየራሳቸውን ትጉሃን መነኮሳትን አስተምረው በማመንኰስ በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ትምህርት እንዲጠናከር በየገዳማቱ የቁም ጽሑፍ፣ የሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ፣ የግብረ ሕንፃና ልዩ ልዩ ጥበበ እድ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ባሕል በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፉ ያደረጉ ናቸው::

አሁንም ወደ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገድል ትረካ እንመለስና ጻድቁ በዚህ ገዳም ሲገቡ ካደረጉዋቸው ዓበይት ተግባራት መካከል ሲጠቀስ፣ በስምንተኛ ዓመተ መንግሥቱ ለንጉሥ ዓምደ ጽዮን፣ «ወእምዝ አሠነዩ ኵሉ ዘይደሉ ለቤተ ክርስቲያን ወአስተናበረ ንዋያተ ቅዱሳት ወመጻሕፍተ አስተዳለወ ለንባበ ትምህርት ወቀደሰ ከመ ሕግ ሐዋርያት ወአሰርገ ቁርባነ ወጸሎተ ብዙህ ወስብሐት ወተቀደሰት ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ውኅረ,ያ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ እም ውስተ ደቂቁ እለ ወሀቦሙ አስኬማ ቅድስተ»፤ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ለንባብ ማስተማሪያ የሚውሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን አዘጋጁ:: እንደ ሐዋርያት ሕግ ሥጋ ወደሙን ፈትተው ብዙ ጸሎትና





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



የደብረ በንኮል አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ገዳም ቤተ ክርስቲያን

ምስጋና ከደረሰ በኋላ ያች ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰች ኾነች:: ቤተ ክርስቲያም ይህን ትመስላለች::

ንጉሥ ዓምደ ጽዮን በነገሠ በስምንተኛው ዓመቱ ከመነኮሱት መነኮሳት መካከል አባ አኖሬዎስ፣ አባ ኢሳይያስ፣ አባ ወረደ ቃል፣ አባ ገብረ ክርስቶስ፣ አባ ገብረ አምላክ የተባሉትን መርጠው ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ጋር በመሆን ሥርዓተ ቅዳሴ ፈጸሙ» በማ ገድሉ ያስረዳል::

ከዚህ ሌላ ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ተምረው መንኩሰው በረድእነትና በመጋቢነት ዐጸደ ቤተ ክርስቲያንና አትክልት በመትከል ሕይወታቸውን በዚህ ታላቅ ገዳም ያሳለፉና ቅዱሳን ተብለው የተሰየሙ መነኮሳት:-

| | |
|---|---|
| አባ አኖሬዎስ | አባ ገብረ ኢየሱስ |
| አባ ኢሳይያስ | አባ ገብረ አምላክ |
| አባ ወረደ ቃል እግዚእ | አባ ማርቆስ |
| አባ ማማስ | አባ ፊቅጦር |
| አባ ዳንኤል | አባ ማማስ |
| አባ ዮሐንስ | አባ በክርስቶስ |
| አባ መሐሪ አብ | አባ ሲላስ |
| አባ እንድርያስ | አባ እስጢፋኖስ |

የተባሉት በደብረ በንኮል ገዳም ገድላቸውን ፈጽመው ያረፉ ናቸው::

በዚህ መሠረት አባ አብሳዲ ዘዘህ አምባ በለሳና አቡነ ያሳይ ጐርጐራ መንዳባ በስተቀር ሌሎቹ የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ተማሪዎች በአክሱም፣ በሽሬ፣ በአድዋ፣ በተንቤን፣ በእንደርታ በአሁኑ ወቅት የሚገኙ ታላላቅና ጥንታዊ ገዳማት አብዛኛዎቹ የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ የወይን ተክል ናቸው::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዘደብረ በንኮል ታላላቅ ገዳማትን የመሠረቱ ቅዱሳት መነኮሳትን በመንፈሳዊ ትምህርት አንፆ ማውጣት ብቻ ሳይሆን በተአምራዊ ተግባራቸውም ይታወቃሉ::

ከአስደናቂ ተአምሮቻቸው መካከል ልዩ ልዩ ዕፅዋት የነበረው የደብረ በንኮል ገዳም ከገዳሙ የ10 ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ያለው ሩባ ሽዊትን ዕጣን ዞሬ ወደ ተባሉ ወንዞች እርሳቸውና ተማሪዎቻቸው እንስራ ተሸክመው በመውረድ የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ተጉዘው ውኃ በመቅዳት ለመጠጥና ለምግብ ማዘጋጃ ብቻ ሳይሆን ዓለት የተነጠፈበት ተራራ በወይራና በጥድ ዛፎች ለመሸፈን ታላቅ ተጋድሎ በመፈጸም የአምባዪቱን ዙሪያ አረንጓዴ ገነት አስመስለው አለምልመዋታል::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ አንድ የሚያገለግላቸው አህያ ነበራቸው፤ አህያውም እንደ ሰው የሚፈልጉትን የሚያውቅላቸው ያሉትን ሁሉ የሚፈጽምላቸው ተአምረኛ አህያ ነበር:: በተለይም አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ካሉበት ሥፍራ ውኃ የሚገኝበት ቦታ እጅግ ሩቅ ስለ ነበር ያን ሁሉ በረሃ ሄዶ ውኃ የሚያመጣላቸው ይኸው አህያቸው ነበር:: ነገር ግን ከዕለታት አንድ ቀን አህያው አንበሳ አገኘውና ገድሎ ግማሽ ሰውነቱን በላውና ሄደ::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ካሉበት ተነሥተው የአህያው ተረፈ በድን ወዳለበት ሥፍራ ሄዱ፤ «ረዳቴ ይኸው አህያ ነበር:: የሚያስፈልገኝን ሁሉ የሚያመጣልኝ፣ የሚታዘዝልኝም ነበር:: ውኃ የሚያመጣልኝ እርሱ ነበር:: አሁንም አህያዬን የበላህ አውሬ እንድ ታነጋግረኝ እፈልጋለሁ» ቢሉ የአህያው ግማሽ አካል አፍ አውጥቶ የበላኝ አንድ አንበሳ ነው ብሎ ነገራቸው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእም በጣም ደስ አላቸው:: ፈጣሪያቸውንም እጅግ አመሰገኑ:: ዐይኖቻቸውንም ወደ ሰማይ አነሡ:: አቤቱ ጌታዬ አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ÷ እለምንሃለሁ፣ እማልድሃለሁም፤ ለባለሟሎችህ ለቅዱሳን ጻድቃን ሁሉ እንደ ድካማቸው ዋጋ ቸውን የምትከፍላቸው አንተ ነህ:: ለእኔም ለአገልጋይህ አስገራሚና አስደናቂ ተአምር አሳይተኸኛልና ዕፁብ ድንቅ ሥራህን በአንክሮ በተዘክሮ ምስጋናዬን አስቀድማለሁ:: የመጻሕፍት ርእስ /ምንጭ/ ከሆነው መጻሕፍት ውስጥ የበለዓም አህያ እንደ ሰው መናገርዋን የሚገልጽ ክፍል አግኝቼ አንብቤአለሁ:: ይኸውም የእኔን የኃጢአተኛውን ኀዘንና ጭንቀት ዐይተህ፣ ቃሌን ሰምተህ እስካሁን እንዲያገለግለኝ አንድ አህያ ሰጥተኸኛልና» እያሉ ጸለዩ:: ቀጥሎም አህያውን የበላውን አንበሳ አሰምተው ጠሩት፣ አንበሳውም ከአንበሶች መካከል ተለይቶ እየበረረ ወደ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ መጣ:: ከእግራቸውም ሥር ወድቆ ሰገደ፤ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም «አንበሳውን አንተ ነህ አህያዬን የገደ ልከውና የበላኸው? እርሱ ራሱ በሰው አንደበት ነገረኝ» አሉት:: አንበሳውም «አዎን÷ እኔ ነኝ» አላቸው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ዳግመኛ ከአምላክ ጋር በቅርርብ ገጽ ለገጽ ሆነው እየተያዩ እንደሚነጋገሩ ወዳጆች ወደ አምላካቸው አንጋጠው «አመሰግንሃለሁ፣ እማፀንህማለሁ» ብለው ልመናቸውን ሁለ ስለ ሰማ ላቸው ጸለዩ::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ እንዲህ ያለውን ልመና አቅርበው እንደ ጨረሱ አንበሳውን አሁን በአህያዬ ፈንታ ናና ተላከኝ አገልግለኝ አሉት:: አንበሳውም አምላክ እንዳስቻለው አቡነ መድኃኒነ እግዚእን ለማገልገልና ለመላክ አብሯቸው ገባ:: አባታችንም የትሩፋታቸውን ውጤት ሰዎች ዐይተው በተአምራታቸው እንዳይደነቁበት ወይም ውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንባቸው አልሸሸጉም:: እንዲያውም አህያው ያደርገው እንደ ነበረ በጀርባው ጭኖ ውኃ እንዲያመጣ ሰደዱት:: አንበሳውም እንደ አህያው ሄዶ ውኃውን ተሸክሞ አመጣላቸው:: የሚቀዳላቸውም ማንም አልነበረም:: በተአምር ግን ጀርባው ሞልቶ ያመጣላቸው ነበር::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በጀመሩት ተጋድሎ ጸንተው ከቀን ወደ ቀን፣ በጸሎታቸው በትሩፋታቸው ተአምራት ማሳየትን ቀጠሉ:: እግዚአብሔር አምላክም በመጨረሻ የጻድቁን ገድልና ድካም ዐየ፤ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስት ድንግል ማርያም እናቱን ይዞ፣ ቅዱስ ሚካኤልን በቀኙ፣ ቅዱስ ገብርኤልን በግራው፣ እልፍ አእላፍ መላእክት በፊቱ እየዘመሩ፣ በታቹም የብርሃን ሠረገላ ይመላለስ ነበር፤ ኃያላን መላእክት እልል እያሉ፣ ሊቃነ መላእክት እያመሰገኑ፣ ነቢያት ዳዊት የተነበየውን መዝሙሩን እያነበቡ፣ ሐዋርያት ወንጌል መንግሥቱን ተሸክመው፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ለሰው ልጆች ምሕረትና ቸርነት እንዲሆን ያሳስቡታል:: በዚሁ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብርና ምስጋና ወደ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ወረደ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእንም ጠርቶ በስሙ ቤተ ክርስቲያን ከምትታነፅበት ቦታ ከመሐልዋ ቆሞ «መድኃኒነ እግዚእ ሆይ÷ ና ላሳይህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልክና ቁመትዋ፣ የመሠረትዋም አግድም እንዲህ ነው» ብሎ ለክቶ አሁን ቤተ ክርስቲያኑ ያለበትን ሥፍራ አሳያቸው::

ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃያ አራቱን ካህናተ ሰማይን ጠርቶ፣ ጽንሐሕ ጽንሐቸውን ይዘው እየዞሩ ያጥኑአት ዘንድ በከበረ ደሙ እንደ ገዛት፣ በዕፀ መስቀሉ እንደ ባረካት ለካህናተ ሰማይ ነገራቸው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእን ደግሞ ጠራቸው:: እንዲህም አላቸው:: በእናቴ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ታቦት ቅረጽ፤ የከበረው ሥጋዬንና የከበረው ደሜንም አሳርግባት፣በኔ ስምና ባንተ ስም የጸለየባት ሰውም ጸሎቱንና



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ልመናውን እሰማለታለሁ:: እቀበልለታለሁም:: የሺህ ዓመት ምግብና መኖሪያ፣ የዘላለም ሕይወት እሰጠዋለሁ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ÷ ይህችን ቤተ ክርስቲያን ባርካት አለው:: ጌታም «እንደ መጀመሪያዪቱ እንደ ደብረ ጽዮን ትሁንልህ:: እንደ ሁለተኛዋ እንደ ደብረ ኤዶም፣ እንደ ደብረ ሲናና እንደ ደብረ ታቦር፣ እንደ ደብረ ዘይትና እንደ አገረ መድኃኒት እንደ ኢየሩሳሌም ትሁንልህ፣ ታሪኳም እንደ እነርሱ ታሪክ ይታወቅልህ:: በፍቃዴም፣ በምሕረቴም፣ በቸርነቴም፣ በክብሬና በግርማዬም እስከ መጣ ድረስ በክብሯ ገናና ሆና ትኑርልህ» ብሎአቸዋል::

ይህችም ቤተ ክርስቲያን በንጉሡ በዓምደ ጽዮን በስምንተኛው ዘመነ መንግሥቱ ቅዳሴ ቤትዋ ተከበረ:: ያን ጊዜ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የብርሃናት ብርሃን አምላክ በአፍህ ስለ እኔ ብለህ በተናገርከው መሠረት አመሰግንሃለሁ ብለው ጸለዩ:: ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ለልጆቻቸው እንዲህ አሏቸው:: የዘመኑ መኳንንት፣ ገበዝ አክሱምንና ምድሯን ያጠፏት ዘንድ እንደ ተማከሩ አውቄአለሁ፣ ሰምቻለሁ:: «ኑ÷ እንሂድ በዚያም እንሙት እኔ ስለኛ የሞተውን ክርስቶስን እመስለዋለሁ:: ይኸውም እኔ ለሷ ነፍሴን እለውጥላታለሁ:: እናንተም ደቀ መዛሙርቱን ምሰሉ:: ስለ ወንጌል እንዲሞቱ፣ እንድትደክሙና እንድትጋደሉ ሁኑ» ብለው ለልጆቻቸው መከሯቸው::

እነርሱም የአባታቸውን ምክር በደስታ ተቀብለው ጉዟቸውን ቀጠሉ:: ከመኳንንቱም ተገናኙ፤ መኳንንቱም አባታችንና ልጆቹን በደስታ ተቀብሏቸው:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእም በእውነተኛነታቸው ያምኑትና ያከብሩት ነበርና «ልጆቼ ይህ ያሰባችሁትን ክፉ ምክርና ክፉ ሥራ ተው፤ እግዚአብሔር በራሳችሁና በልጆቻችሁ ላይ እንዳይቆጣባችሁ የጽዮንን አገር አታጥፉ፤ እምቢ ካላችሁ በመጀመሪያ እኔ ቀጥሉም ልጆቼ ለመሞት ጨክነን መጥተናል» አሏቸው:: ነገር ግን መኳንንቱ ዓላውያን ሕዝብ ፈጽሞ እምቢ አሏቸው:: ጽዮንን ለማጥፋት ልጆችዋን ለመግደል ገቡ:: አባታችንም ከነልጆቻቸው ገቡ::

ነገር ግን አባታችን ብትርም ኮናትም ሌላም በእጅ አልያዙም:: ባዶ እጃቸውን ነበሩ እንጂ:: በጽዮን በር ለመሞት ገቡ:: ከነልጆቻቸውም በጽዮን በር ላይ ተጋደሙ:: ደቂቀ ጽዮን ፈርተው ወደ ጣራ ተሰባሰቡ:: ካህናቱም በጽዮን ግድግዳ ተጠጉ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ግን ለመሞት መቁረጣቸውን አረጋገጡ:: ከልጆቻቸው በፊት እንዲሞቱም ቆርጠው ጨክነው ገቡ:: መኳንንቱ ግን ቅንዓትና መዓት የለበሱ ስለሆኑ በላያቸው ላይ ኮናት አዘነሙባቸው:: ይሁን እንጂ አንድ ጦር ስንኳ አላገኛቸውም:: የእግዚአብሔር ረድኤትም ከነልጆቻቸው በዙሪያቸው ጠበቻቸው፣ ከነርሱም አባታችን አቡነ መድኃኒነ እግዚእን በእጃቸው እንዳይሞቱ ፈልገው ፈርተው እንዲሸሹ በጦርና በሰይፍ ያስፈራሯቸው ነበሩ:: የጽዮንን ደጅ በጦር ወቶት:: መቃኖችን በሰይፍ መቱት: - ይኸውም ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ አንገት አጠገብ ሳይቀር ነበር ጦራቸውን የሚያዘንሙት፤ የጦሩ፣ የሰይፉ ምልክት እስከ ዛሬ ድረስ አለ:: ነገር ግን አባታችን ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው ለመስጠት እንደማያወላውሉ ሆነው ስላገኙዋቸው እያደነቁ ከሁለት ተከፈሉ::

ይኸውም አንደኛው ክፍል እንደ ቆሬ ልጆች እሳት ከሰማይ ወርዶ እንዳያቃጥለን ጽዮንን ከማጥፋት እንራቅ፣ አሳባችንም እንለውጥ ሲል፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እንደ ዳታንና እንደ አቤሮን ምድር ተከፍታ እንዳትውጠን ማንም ሳያየን እንሽሽ አሉ:: ወደ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ሔዱና አባታችን እኛ ከክፉ ግብራችን ተመልሰናል:: ከደቂቀ ጽዮን አስታርቁን ብለው ወድቀው አስታረቋቸው:: ፀረ ደቂቀ ጽዮንም ለአባታችን «ለእርስዎ ልጆች እንሆናለን፣ እርስዎ ደግሞ ከዛሬ ጀምሮ አባታችን ነዎት፣ መቅደሳችንም ከእርስዎ መቅደስ ጋር አንድ ይሁን፤ እስከ ዓለም ፍጻሜም አይለያዩ» ብለው መላ ሕይወታቸውን በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ እጅ ጥለው ከልብ ተማፀኑ:: በዚሁም በሃይማኖት፣ በፍቅርና በአንድነት ጸንተው ኖሩ::

ከዚህም በኋላ ደጉ ንጉሥ ሠይፈ አርዕድ በአገሪቱ ላይ ነገሠ:: ነገር ግን በዘመኑ የሳባና የኖባ ሰዎች ዓምፀው ጦርነት ከፈቱ:: በዚህ ጊዜ አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ወደ ደገኛው ንጉሥ ወደ ሰይፈ አርዕድ ሄዱ:: «የሳባና የኖባ ሰዎች ታላቁ ንጉሠ ነገሥቱ ካሌብ በጸሎተ ጳንጠሌዎን ቃል እንደ ወጋቸው አንተም በኔ ኃጢአተኛ ቃል ሄደህ ውጋቸው፣ እግዚአብሔር አምላክ ይረዳሃል፣ድል አድርገህ ትመለሳለህ» አለው:: ሰይፈ አርዕድም «አባቴ ሆይ÷ እንደ ቃልዎ እታዘዛለሁ:: ነገር ግን በጸሎትዎ አትርሱኝ» ብሎ ከብዙ ሠራዊት ጋር ይጸልዩ ነበር:: የንጉሡ ሠራዊት ግን እስላሞቹን ሲያዩአቸው ጊዜ ፈሩአቸው:: ከጦርነቱም ሊሸሹ ፈለጉ:: ያን ጊዜ ንጉሡ በአባታችን ጸሎት ስለ ታመነ ልቡ ሳይወላውል ጸናበት::

አባታችን አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ከቤታቸው ውስጥ ቆመው እስላሞቹን ይነድፏቸው ዘንድ ልጆቻቸውን በነጭ ንብ አምሳል ላኳቸው:: በዚሁ ጊዜ በእስላሞቹ ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው:: ሠራዊቱም ተመልሰው እስላሞቹን ያሮጧቸውና ይፈጠፍጧቸው ጀመር:: ንጉሡም ያን ጊዜ እነርሱን ተከትለን እኛም በርትተን ጨረስናቸው:: ከእኛ ወገን ግን አንድስ እንኳ የሞተብን የተቀነሰብን የለም አለ:: ንጉሡም ሠራዊቱም የአባታችን የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን ጸሎትና ብሂል አደነቁ:: ምክን ያቱም በእርሳቸው ብዕዕና ቅድስና ጠላቶቻቸውን ድል ለማድረግ በቅተዋልና ክብር ለእርሳቸው ይሁን እያሉ ለዘለዓለሙ አምላክ ምስጋና አቀረቡ፣ የአባታችንንም ጸጋና በረከት አደነቁ:: ምክንያቱም በእርሳቸው ጸሎትና ረድኤት ኃይልና ድል አግኝተዋልና ክብሩ ለትውልደ ትውልድ ይሁን እያሉም ምስጋና ለፈጣሪያቸው አቀረቡ::

ንጉሡም በልቡ አሰበ፣ ወደ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም በሰላም መጣን፤ ድል አድርገንም በሰላም ተመልሰን በሰላም ወደ አገራችን ገብተናል፤ ብሎ ካበሠራቸው በኋላ ናና እንገናኝ ብለው ላኩበት፣ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ከመነኮሳት ልጆቹ እስከ ዲበ አእታር የሚባል ሥፍራ ድረስ ሄደ:: በዚያም ከንጉሡ ጋር ተገናኙ:: ንጉሡም ከፈረሱ ወረደ፣ ከአባታችን በረከት ተቀብሎ ተቀመጠ:: ሁለቱም እንደ መጀመሪያው ተነጋገሩ፣ ተጨዋወቱ፣ ንጉሡ አቡነ መድኃኒነ እግዚእም በጸሎታቸው በብፅዓታቸው ያደረጉትን ሁሉ ዐይተውና ተረድተው ሁሉም በጸሎት ኃይል እንደ ሆነ ተመልክቶ እጅግ አልቆና ከፍ አድርጎ አከበራቸው::

ስለሆነም ንጉሡ አባታችንን «አባቴ ሆይ÷ ምን ላድርግልዎ?» አላቸው:: አባታችንም እኔ እግዚአብሔር አለልኝ፣ ችግርም ሆነ ኀዘን የለብኝም፤ ነፍሴ ለእርሱ አስረክቤዋለሁና ይልቅስ ስለ እኔ ብለህ እስረኞችን ማርልኝ፤ ያዘኑትንም አጽናናልኝ፣ አስደስትልኝ አሉት:: ንጉሡም አቡነ መድኃኒነ እግዚእ እንዳሉት እስረኞችን ማሩላቸው ንጉሡም ጉልት ለተዝካራቸውና ለንጉሡ መታሰቢያ መሬት ሰጧቸው:: እስከ አሁን ንጉሡ ሰይፈ አርዕድ /ንዋየ ክርስቶስ/ እየተባለ ይታሰባል:: መታሰቢያውም ግንቦት 15 ቀን ይደረግላቸዋል::

ሁለተኛው በአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ስም የተሰጠ ነው ብሎ በሬዎቹን ከእርሻ መሣሪያቸው ጋር ያመጡ ዘንድ አዘዘ:: የዕቃ መሣሪያው በሐር ይጠመጥሙት ዘንድ፣ በሮቹም በከበረው ሐር ልብስ እንዲሸፈኑ አደረጉ:: ከዚህ በኋላ ያርሱ ዘንድ ዕርፉን ያዙ፣ በእምነትም እርሻውን አረሱ፣ ሠራዊቱም የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን በረከትና ረድኤት እንዴት እንደ ረዳቸው ዐይተው «ፊተኞች፣ ኋለኞች አባቶች ያላደረጉት እኮ ነው በእኒህ አባት ሲደረግ ያየነው ነው እያሉ በማድነቅና በመገረም ተናገሩ፤ ምክንያቱም የአባታችን በረከትና ረድኤት በጦርነቱ ጊዜ ንጉሡን ምን ያህል ድልና አሸናፊነት እንዳጎናጸፋቸውና ከሞት አደጋም እንደ ሰወሯቸው ተረድተዋል:: ሁለተኛም ጽዮንና ልጆችዋም በጸሎታቸውና በረድኤታቸው ከጥፋት አድነዋቸዋልና ነው::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ በቅዱስ መጽሐፍ ሰላምን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው ተብሎ የተጻፈውን ቃል ፈጽመው ተገኝተዋል:: እንደ እኒህ አባት ያሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ፣ እግዚአብሔር አቡነ መድኃኒነ እግዚእን እንደ ኤርምያስ ከእናታቸው ማኅፀን ሳሉ መርጧቸዋል:: በጀርባቸውም፣ በፊታቸውም መድኃኒት የሆነውን ትእምርተ መስቀል አሳያቸው፣ በተወለዱ ጊዜ እንደ ሰው እንዳይደሉና በእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተለወጡ የሚያመለክት ነበር::



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

አቡነ መድኃኒነ እግዚእ የእግዚአብሔርን ጥበብ ሲመገቡ አደጉ እንጂ የእናታቸውን ጡት ጠብተው አላደጉም፣ እግዚአብሔር መርጧቸዋልና::

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እርሳቸው መጣ:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ከዚህ ዓለም የሚሄዱበት /የሚለዩበት/ ጊዜ እንደ ደረሰም ሲነገራቸው «ደስተኛው መድኃኒነ እግዚእ ሆይ÷ ከድካም ወደ ዕረፍት የምትሄድበት ጊዜ ደረሰ» አላቸው:: ከኀዘን ወደ ደስታ ከድካም ለነፍስህ ሰላምና ዕረፍት ወደ ምታገኝበት ሥፍራ እንደ ምትሄድ እነግርህ ዘንድ መጣሁ:: እነሆ ጌታህ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም እናቱ ወደ ራሱ እንዲወስድህ /እንዲያወጣህ/ ከሰማይ ሠራዊት ሁሉ በልዕልና በክብር ይመጣል አላቸው:: ከዚህ በኋላ ሕማሙ በላያቸው ጸና፤ ለሞትም ደረሱ:: ኢየሱስ ክርስቶስም ወዲያውኑ በሠረገላ ኪሩቤል ወደ ርሳቸው መጣ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም መጣች::

አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ጌታን ባዩ ጊዜ በጣም ደስ አላቸው:: ከተኙበት ሆነውም ሰገዱለት:: ጌታም ወዳጄ መድኃኒነ እግዚእ ሆይ÷ ሰላም እልሃለሁ:: አትፍራ ደስ ይበልህ ሐሴትም አድርግ፤ እነሆ በዚሁ በደስታህ በዓል መጥቻለሁ:: አባታችንም በፊትህ እናገር ዘንድ ፍቀድልኝ አሉት:: ጌታም በፊቴ ተናገር ብዬ ፈቅጄልሃለሁ አላቸው:: «አባታችንም ስሜን የሚጠሩትን ማርልኝ፣ መቃብሬን ባርክልኝ፣ ልጆቼንም ቀድስልኝ» አሉት::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አቡነ መድኃኒነ እግዚእን ራስህ እንዳልክ አላስተባብልህም መመስገኛዬን ሰጥቼሃለሁ:: ለዚሁም ቃሌ ነው:: ከአፌም የወጣ ነው:: ይኸውም በአባቴ በመንፈስ ቅዱስ ስም በእናቴ ቅድስት ድንግል ማርያም በሰማያውያንና በምድራውያን ባለሟሎቼና አባቴም ባከበራቸውና በወደዳቸው ሁሉ በጸሎትህና በአማላጅነትህ የሚያምኑ በሙሉ ካንተ ጋር አኑራቸው፤ በአንድ ሺህ ዓመት ክብረ በዓልህ ልጆችህንም በየዘመኑ ይቅር እላቸዋለሁ፤ እባርካቸዋለሁ:: መቃብርህ ባለበት ሕማም፣ ልዩ ልዩ ደዌና መከራ አላቀርብብህም:: ልጆችህ ሥርዓቴን ከጠበቁ፤ ሴቶችም በወሊድ ምክንያት ሕመም ቢጸናባቸው፣ መካናትም ልጅ አጥተው በስምህ ቢለምኑኝ ፈጥኜ እሰማቸዋለሁ::

አባታችን አቡነ መድኃኒነ እግዚእም ይህንኑ በሰሙ ጊዜ ደስ አላቸው:: ፈጣሪያቸውንም አመሰገኑ፣ ጌታችንም አስከሬኑን አሳረፋት:: ሦስት ጊዜም ሰላም አላት፤ በሠረገላ ኪሩቤልም አውጥቶ ወደ ዓለመ መላእክት ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም አስገባው:: ዕረፍታቸው ኅዳር ሦስት ቀን ነው:: ልጆቻቸው መነኮሳትም መብራታቸው አቡነ መድኃኒነ እግዚእ ስለ ጠፋባቸው የፈሰሰው እንባና የተለቀሰው ልቅሶ እንደ ራሔል ልቅሶ እጅግ ከባድ ነበር:: አቡነ መድኃኒነ እግዚእንም ደናግል ልጆቻቸው በክብር ገነዟቸው:: ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በአመለከታቸው ቦታም በማቅና በአመድ ቀበሩአቸው:: የአቡነ መድኃኒነ እግዚእ መዋዕለ ዘመን 180 ሲሆን ከዚሁ ዕድሜያቸው የሚበዛውን ያሳለፉት በተጋድሎ፣ በትኅርምና በተባሕትዎ መሆኑን ገድሉ ያስረዳል::

## ደብረ በንኮል ገዳም

ወደ ደብረ በንኮል ለመሄድ ሁለት አማራጭ መንገዶች አሉ:: መነሻችንን ከአክሱም ገደማ ብናደርግ በእግር ተጉዞ ደብረ በንኮልን ለመጐብኘት በንግሥተ ሳባ ቤተ መንግሥት አድርጐ በመቃብረ ቀዳማዊ ምኒልክ አልፎ ምዕራፈ መድኃኒነ እግዚእ የተባለች ድንጋይ ተሳልሞ በንኮል ገዳም ከሦስት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ይደረሳል::

በመኪና ለመጓዝ ከሆነ ግን አክሱም ጐበዱራን አቋርጦ የውቅሮ ማራይ ከተማን ከደረሱ በኋላ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ዐሥር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ገዳሙ ይገኛል:: የመኪና አውራ ጐዳና ተጉዘው ከጨረሱ በኋላ የአቡነ አላኒቆስ ገዳም ማይበራዚዮን ወደ ምዕራብ እየተመለከቱ ወደ ምሥራቅ የአቡነ ሰላማ ገዳም አንጋጠው እያዩ በአረንጓዴ ደን የተሸፈነው የደብረ በንኮል ተራራ ከፊትዎ ተደቅኖ ሲያዩ:- «አቤቱ ጌታዬ መውጫዬ በየት አቅጣጫ ይሁን» እያሉ ከመጸለይ በስተቀር የሚታይ የተራራው መውጫ መንገድ የለም::

የደብረ በንኮል አምባ ለመውጣት ከግማሽ ሰዓት ያላነሰ ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም በአረንጓዴው ሥነ ውበታቸውና በጼና መዓዛቸው መንፈስን የሚያድሱ የደብረ በንኮል ዕዕዋት ተራራውን ያለ ድካም ለመውጣት አጋዥ የተስፋ ምርኩዝ ሆነው ያገለግላሉ:: በዚህ ረገድ በዓለም በተለይም በፈረንሳይ አገር ለሽቱ ቅመማ የምትታወቀውና በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዕፀ መዓዛ የምትባለው ተክል ትጠቀሳለች::

አቀበቱን ጨርሰን ለጥ ካለው አምባ ምድር ላይ ስንደርስ በዐፄ ፋሲል ሠራዊት አክሱም ጽዮንን ለማነፅ ጥዱ ተቆርጦ ወደ ወይራ መለወጥ፣ በተአምር የበቀሉትን ወይራዎች፣ መንፈስን የሚያድስ የአምባው ንጹሕ አየር እየተነፈስን የሴቶች ቤተ ክርስቲያን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አልፈን ወደ ደብረ በንኮል ቤተ ክርስቲያን እንገባለን::

የደብረ በንኮል ቤተ ክርስቲያን በረጅም ግንብ በተገነባ አጥር እንዲሁም በመነኮሳቱ ቤት ዙሪያዋ የተከበበች እንደ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሦስት ዙር /ማኅሌት፣ ቅድስትና ቤተ መቅደስ/ ያሏት ስትሆን መዝጊያዎችዋ ከአንድ ወጥ የዋንዛ እንጨት ተጠርበው የወጡ ከሦስት ሜትር ያላነሰ ርዝመት ያላቸው መስኮቶችዋ በዓይነ ርግብ እንጨት የተቀረጹ፣ በደብረ ዳሞ ቤተ ክርስቲያን እንዳሉት ሐረጐች መስል በዙሪያዋ የተቀረጹበት በአራቱ ማዕዘን ቤተ መቅደስዋ በሥዕልና በሐረግ ያሸበረቀ ነው:: በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም የሚጠራ የሴቶች ቤተ ክርስቲያንም በምዕራብ አቅጣጫ ይገኛል::

የገዳሙ ዕቃ ቤት ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ከቤተ ልሔሙ ጐን ለጐን የታነፀ ባለ ሁለት ፎቅ ዘመናዊ ሕንፃና በውስጡ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት ክፍሎች ያሉትና ከውስጥም ይሁን ከውጭ ሲያዩት የሚያምር በተለይም በረንዳው ላይ የተተከለውና የበቀለው ሣር ልምላሜው ልስላሴው ለየት ያለ መልክ ያለው ነው:: በዙሪያው ያለው «የደብረ በንኮል ሣር» ተብሎ የሚታወቅ ልዩ የሣር ዘር በላይ ሲቀመጡበት እንደ ስፖንጅ የለሰለሰ ግሩም ሣር ነው::

<u>ተግባር ቤት</u>

ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ የመነኰሳት ተግባር ቤት ወይም ቤተ ማኅበር ይገኛል:: በዚህ ቤተ ማኅበር የገዳሙ ሀብትና ንብረት በሙሉ የሚቀመጥበት፣ ምግብና መጠጥ የሚዘጋጅበት፣ የቀንድና የጋማ ከብቶች የሚያድሩበት፣ መነኰሳቱ የዕለት መቀነናቸውን የሚቀበሉበት፣ እንግዳ ሲመጣ ካህናቱ የእንግዳውን እግር አጥበው ተቀብለው እህል ውኃ የሚጋብዙበት ጐተራ ቤት፣ ወጥ ቤት፣ ጠላ ቤት፣ እንጀራ ቤት፣ ምጣድ መጋገሪያ ቤትና ሌሎችም አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች የሚገኙበት ቦታ ነው::

ይህ ጥንታዊና ታሪካዊ የአንድነት ገዳም የተለያዩ ችግሮችን ተቋቁሞ እዚህ ደርሷል:: በገዳሙ ከፍተኛ የውኃ እጥረት አለበት:: ውኃ ለማግኘት /ለመቅዳት/ የሚቻለው ከሦስት ሰዓት የእግር መንገድ በኋላ ነው:: እህል የሚያስ ፈጨበት ወፍጮም የለውም:: በእዚህና በመሳሰሉት ችግሮች የገዳሙ አንድነት እንዳይፈታ የሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያን አካላትና በጎ አድራጊ ምእመናን ሁሉ የበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል::

*<u>ከአዘጋጁ</u>:- የአቡነ መድኃኒነ እግዚእን ታሪክ ያቀረቡልን ንቡረ እድ ገብረ ዋሕድ ግርማይ ቀደም ሲል የደብረ በንኮል ገዳም አበ ምኔት በመሆን አገልግለዋል:: በአሁኑ ወቅት የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አስተዳዳሪ ናቸው:: ንቡረ እድ ገብረ ዋሕድ ግርማይ ስላበረከቱልን ጽሑፍ በአንባብያን ስም እያመሰገንን ለወደፊቱም በመሰል ትብብራቸው እንደማይለዩን ተስፋ እናደርጋለን::*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከመፋጠጥ መደማመጥ

/ጌታቸው በቀለ/

## መግቢያ

እግዚአብሔር አምላክ አስቀድሞ ይህን ዓለም ሲፈጥር በሥራ ነው የጀመረው:: በኋላም የሰውን ልጅ በአርአያው በአምሳሉ የፈጠረው ሥራ እየሠራ እንዲኖር ነው::በዘፍ.1÷28 ላይ እንደ ተገለጸው «ገነትን ጠብቃት አብጃት» በማለት ሥራን ሠርቶ ያስተማረ እግዚአብሔር ነው:: በዚህ ዓለምም የሰው ልጅ ሲኖር የተፈጥሮ ሀብቶችን እየተከባከበ እንዲጠቀም ከአምላኩ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ትእዛዝና የተፈጥሮ ግዴታ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል:: «በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፤ እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች÷ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፤» /ዘፍ.3÷17-19/ የሚለው ኃይለ ቃል የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ጥሮ፣ግሮ፤ ወጥቶ ወርዶ እየሠራ መኖር ያለበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው:: በዚህም መሠረት ሰው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ምድርን አልምቶ መጠቀም የተፈጥሮ ግዴታው የሕልውናው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ጸጋም ጭምር ነው::

በሃይማኖት ትምህርታችን ማኅበራዊ በሆነው የሰዎች ኑሮ እርስ በርስ መተሳሰብና መረዳዳት አስፈላጊና ግዴታ ቢሆንም ድሆች ድህነትን የልመናና የመንግሥተ ሰማይ መውረሻ ብቸኛ መሣሪያ አድርገው መቀበል፣ ባዕለ ጸጎችም ድሆች ለነሱ መጽደቂያ እንደ ተፈጠሩ አድርገው በመቁጠር የማንቲም ድቃቂና የጨርቅ ዕላቂ ብቻ ከመበተን አልፈው ድህነትን ለመዋጋት ለተያዘው ዘመቻ ሁሉም ክፍሎች የአመለካከት ለውጥና የተሻለ አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ይገባል:: ድህነት በራሱም ድኻን የዘላለም ሕይወትን ለማውረስ ተብሎ በተለየ መልኩ የተሰጠ ዕድል አይደለም::

እያንዳንዱ ሰው ወጥቶ ወርዶ በመሥራት ያተርፍበት ዘንድ እንደ የመጠኑ የተሰጠው የመክሊቱ ምሳሌ /ማቴ.25÷14-30/ የሚያስተምረን ሠርተው ያተረፉ ሰዎች ጌታቸውን እንዳስደሰቱ፣ ምስጋና፣ አድናቆት፣ ሹመትና ሽልማት እንዳገኙ ሲወሳላቸው በተሰጠው ሳይሠራበት፣ ዋናውንም /ዓይነቱን/ በተለያየ ሰበብና ምክንያት ቀብሮ ያኖረው ሰው ግን መወቀሱን ነው:: እንዲያውም ያንኑም ተቀምቶ ለሌላቸው እንደ ተጨመረላቸው እሱ ግን፣ ወቀሳ፣ ዘለፋና ተግሣጽ፣ ሐፍረትና ውርደት እንደ ደረሰበት አልፎ ተርፎም «ላለው ይሰጠዋል፡ ይበዛለታልም፡ ከሌለው ግን ያውያለውም እንኳ ይወሰድበታል» ተብሎ ለሌሎች በተሰጣቸው ዕውቀት፣ ጉልበትና ጤንነት ተጠቅመው ሠርተው ለማያተርፉ ሁሉ ትምህርት፣ መመሪያና ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ይገልጻል:: የሚሠራ፤ ሠርቶ የሚያተርፍ ሰው ሁል ጊዜ ለራሱ ደስታን፣ ኩራትንና ክብርን ያገኛል፤ ለአገርና ለወገንም ትምክህት ነው::

በሌላው ገጹ ከዚህ ምሳሌ የምንማረው በተሰጠ ሀብት ሠርቶ ማትረፍ የሚጠቅመው የዚህን ዓለም ኑሮ አሸንፎ በደስታ ለመኖር ብቻ ሳይሆን ለጽድቅ የሚያበቃ መልካም ሥራ የሌለው፣ የተሰጠውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጤንነት ሳይሠራበት ያመከነ ሰው ለዘለዓለም ሕይወት ወራሽነት የማይበቃ መሆኑንም ነው:: እያንዳንዱ ሰው በተሰጠው አእምሮ ተጠቅሞ ሠርቶ ማግኘትንና በራሱ የመተማመን ባሕሉን በውስጡ ካሳደገ የሚሠራበት እንጂ ለልመና የሚዘረጋው እጅ÷ የሚናገርበት እንጂ የሚለምንበት አንደበት አይኖረውም::

በሌላም አንቀጽ «መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ለመቅጠር በየአደባባዩ እየተዘዋወረ ያለ ሥራ የሚኖሩ ሰዎችን ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ጀንበር ጥልቀት ሲያፈላልግ የዋለ ሰው እንደምትመስል» የተጻፈ ትምህርት አለ:: ሁሉም እኛን ለማንቃት ለሥራ ለማነሣሣትና ለማትጋት የተጻፈ ምክር፣ ትምህርትና መመሪያ ነው::

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥራ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚመሩበት የእግዚአብሔር ቃል ነው:: መመሪያነቱም ለመንፈሳዊም ለሥጋዊም ሕይወታቸው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን ከመጀመሪያው አንሥተን እስከ መጨረሻው ያለውን ብናነብ የሚያስተምረው የሥራን ክቡርነት ነው:: ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ንስሐ መግባት፣ ቃለ እግዚአብሔርን መማር ሥጋ ወደሙን መቀበል እንዳለብን ያስተምረናል:: ለሥጋዊ ኑሮአችንም ሥራን ሳንንቅ መሥራት እንዳለብን፣ ሥራ ፈት መሆን እንደሌለብን ያስተምረናል:: ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መመሪያ መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ኑሮ በትክክል ለመምራት የሚያስችላቸው ፍጹም ሕግ ነው::

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር በተገቢው መንገድ ሕይወቱን እየመራ መኖር አለበት:: የክርስትና ጉዞ በተሠማሩበት የሥራ መስክ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ውጤታማ ለመሆን መቻል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል የደረቀውንና የጠወለገውን ሕይወታችንን አለስልሶ ነፍስን እንደ ሚያረካት ሁሉ፣ተግቶ መሥራትም ምድርን አለምልሞ ሰዎችን ያጠግባል:: «ምድሩን የሚሠራ ሰው እንጀራን ይጠግባል» እንዲል:: ምሳ.12÷11:: ሰው ለራሱ የሚሻሻለው፣ ለቤተሰቡ የሚተርፈው ለአገሩ ብልጽግና የሚበጀው በተለያዩ የልማት ሥራዎች ሲሳተፍ ሰብአዊ ግዴታውን ሲወጣ ነው:: የልማት እንቅስቃሴ መጠናከር ደግሞ ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻልና ለአንድ አገር ዕድገት ወሳኝ ነው::

የክርስቲያኖች መመሪያቸው መጽሐፍ ቅዱስ በመሆኑ፣ በልማት ሥራ ውስጥ ተሳትፏቸው ከፍተኛ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ለሥራ ታጥቆ የተነሣ መሆን እንዳለበት ሲያስገነዝብ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው» ዘፍ.2÷15 ይላል እንጂ ተዘልሎ በዝንጋዔ /የቅምጥል ኑሮ/ እንዲኖር አደረገው አይልም:: «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» /2ኛ ተሰ.3÷10/ እያለ የሚያዝዘው የእግዚአብሔር ሕያው ቃል ነው:: ስለዚህ ለሌሎች አርአያ የሚሆን ፣ሕጉን የሚጠብቅ ትእዛዙን የሚፈጽም መሆን እንደ አለበት ነው:: በዚህም መሠረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ በገዳማትና፣በአድባራት የተለያዩ የልማት ተግባሮችን እያከናወነች ትገኛለች::

## የሥራ ባሕል በቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች የምታስተምረው ከእግዚአብሔር የተገኘውን ትምህርት ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ያስተማረው «...የምትኖርባትን ምድር እረሳት ቆፍራት፣ ዓልማት፣ ጠብቃት፣ ተከባከባት፣ ሠርተህ በላብህ፣ በወዝህ እንጀራህን ብላ» የሚል ነው:: እግዚአብሔር በነቢያትና ሐዋርያት ሁሉ አድሮ ያስተማረው ይህንን ነው:: ቤተ ክርስቲያንን የሰማት እንጂ ሰምቶ በትምህርቷ የተጠቀመ ብዙ አይደለም:: መጸሕፍትንም ብዙዎቻችን እናነባቸዋለን ግን ምክራቸውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አናደርግም:: «...በግንባርህ ወዝ ብላ» የተባለው መለኮታዊ ቃል የቤተ ክርስቲያን መመሪያ ነው::

ስንኳን በዓለም ላይ ለሚኖሩ ዓለማውያን ከዓለም ተለይተው በገዳም በምናኔ ለመኖር ለወሰኑ ገዳማውያንም ከዚህ የተለየ፣ ከዚህ የሚበልጥና የከበረ መመሪያ የላቸውም:: ከዓለም አኗኗር ከተለዩበት መንፈሳዊ ዓላማቸው ጾምና ጸሎት፣ ቁመትና ስግደት ጎን ተምሮ በማስተማር ብርቱው ደካማውን በመርዳት ሕይወታቸውን የሚመሩት በሥራ ተደጋግፈው ነው:: በዓለም ካለው ይልቅ በገዳማት ያለው ተግባሩም ተጋድሎውም ይበረታል::

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን ሰማያዊ ጥበብ ምድራዊ ዕውቀት እያስተማረች ቆይታለች:: ትምህርቷ ለነፍስም ለሥጋም የሚበጅ ነው:: ልጆቿ የሚመጣውን ዓለም ለመውረስ እንዲበቁ፣ ዛሬም በሚኖሩበት በዚህ ዓለም ተደስተው እንዲኖሩ የሥራን ክቡርነት አጥብቃ ታስተምራለች:: ሊቃውንቱም የቃል ብቻ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሳይሆኑ የተግባርም አስተማሪዎች ናቸው::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለልማትም ሆነ ለተግባረ እድ ባለቤት እንጂ እንግዳ አይደለችም:: ቤተ ክርስቲያን የሥራ፣የፈጠራ ማዕከል /ተቋም/ በመሆኗ በውስጧ ሥራ ፈትቶ የሚኖር የለም:: ተማሪዎች መምህሮቻቸውን ብርቱዎች ደካሞቹን እየረዱ ሁሉም እንደ ሞያው የሚሠራባት ተቋም ናት:: ካህናቱም በሥራ የሚሠማሩት ገና ወደ ትምህርት ቤት ሲገቡ ጀምሮ ነው:: በጽሕፈት፣መጽሐፍ በመደጐስ /ድጐሰት/፣ በመማር ማስተማር፣በጸሎት፣ በስግደት ወዘተ... በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ጽሙዳን ሆነው ዘመናቸውን ያለ ዕረፍት ያሳልፋሉ::

ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶቿ ሁሉ የጥበበ እድ መቅሰሚያዎች ናቸው:: ብራና ፍቃ ፣ቀለም አውጥታ፣ ብርዕ ቀርጻ ከፊደል ጀምሮ ብርቅና ድንቅ የሆኑ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የቁጥር መጽሐፍ ወዘተ ያበረከተችው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው:: ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባልተስፋፋበት ዘመን ከአንድ ወጥ ቋጥኝ የተሠሩ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በፍጡር እጅ የተሠሩ የማይመስሉ የሚገኙባት ቤተ ክርስቲያን የሥራም የጥንታዊና ዘመናዊ ሥልጣኔም ምንጭ ለመሆኗ ምስክሮች ናቸው::

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ካህናቱ እየቀደሱ፣ እየጸለዩ በልማት መስክም እንዲሳተፉ ትምህርት ቤት ፣ክሊኒክ ...ወዘተ እንዲከፈቱ ለራሳቸውም መተዳደሪያ ለሌሎችም የሥራ ዕድል እንዲፈጥር በሰበካ ጉባኤ የዕቅድና ልማት እንዲሁም የምግባረ ሠናይ /በጎ አድራጎት/ ክፍሎች አማካይነት የተለያዩ አመርቂ እንቅስቃሴዎች እየታዩ ናቸው:: በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ገዳማትና አድባራት ወፍጮ ቤት፣ የከብት ርባታ...ወዘተ የልማት ሥራዎች መቋቋም ጠቀሜታቸው ለካህናት ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ኅብረተሰብም ነው:: ይህ የሚያሳየን ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የሥራ ፈጣሪ በመሆኗ የሥራ ባሕል ያላት መሆኑን ነው::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን «በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ»/ዘፍ.3÷14/ የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት በማድረግ ሁሉም ሰው ባለው ዐቅሙ ሠርቶ የድካሙን ፍሬ እንዲመገብ እንጂ ሌላው የደከመበትን ለመመገብ እንዳይቃጣ አበክራ ታስተምራለች:: ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን፣ከበጐ አድራጊዎች ጋር በመቀናጀት የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም፣ የተለያዩ ተቋማትን በመሥራት ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረገች ከመሆኑም በላይ የሥራ ዕድልን በመፍጠር፣ ሕዝቡ እንዲጠቀም እያደረገች ነው:: ለአብነትም ያህል በአዲስ አበባ የሚገኙትን የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ፣የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልና የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አብያተ ክርስቲያናት ወዘተ እያከናወኑ ያለው የልማት ተግባራት ተጠቃሾች ናቸው::

ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ የሥራ ክቡርነትን ታስተምራለች:: ቃሉን መስማትና በተግባር ማዋል የእኛ ድርሻ ነው:: በተሠማራንበት የሥራ መስክ ውጤታማ ይልቁንም ለሌሎች አርአያ መሆን ይጠበቅብናል:: መንፈሳውያን ነን ብለን መጽሐፍ ቅዱስን የማናነብ ለሕይወታችንም የማንማርበት ከሆነ ኑሮአችን የተሟላ አይሆንም:: እንዲሁም ለኑሮ የሚያስፈልገውን ሥራ ሳንሠራ መንፈሳዊ ነኝ በማለት በስንፍና መያዝ አይገባም:: እግዚአብሔርን መፈ ታተን በራስ እንደ መቀለድ ነውና:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መምህረ ወንጌል ቢሆንም ያለ ሥራ አልኖረም:: በርግጥ በወንጌል የወለዳቸው ሊረዱት የሚችሉ የመንፈስ ልጆች ነበሩት፤ ለራሱ ኑሮ መሥራት ባላስፈለገው ነበር:: ነገር ግን «እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደ ሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንም፤ ከእናንተ ዘንድ በአንዱ እንኳን እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም» /2ተሰ.3÷7-10/ እንዳለ ከወንጌል ማስተማር ጋር የራሱን ኑሮ የሚያሸንፍበትን የድንኳን መስፋት ሥራ እየሠራ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: ስለዚህ እኛም በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሆነን በሥራችን ውጤታማ መሆን ይጠበቅብናል::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነገ ተረካቢዎቿን ማለትም የነገ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ ዲያቆናት እንዲሆኑ ወጣቶችን እየኮተኮተች ከምታሳድጋቸው ተቋማት አንዱ ሰንበት ት/ቤት ነው:: ወጣቶች የቤተ ክርስቲያናቸውን ታሪክ እንዲያውቁ ትምህርተ ሃይማኖትን አስተምራ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲጐለብቱ በሥጋዊም ሕይወታቸው እንዳይጐዱ መልካም ዜጐች ሆነው ለቤተ ክርስቲያንም ለአገራቸውም ብቁ እንዲሆኑ እያደረገች ነው:: ለአብነትም ያህል አንዳንድ ሰንበት ት/ቤቶች ወንጌልን እየተማሩ በልማት ሥራም እየተሳተፉ የሥራቸውን ውጤት ለገቢያ የሚያቀርቡ አሉ:: በዚህ መልካም ሥራቸው በርቱ ተበራቱ ልንላቸው ይገባል:: በሰንበት ት/ቤት ያሉ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን የልማት ሥራ ሠርተዋል ለማለት ባያስደፍርም የሥራ ባሕል የለም ለማለት ግን አንችልም:: ወደ ፊት መሻሻል፣ መጠናከር ብዙ መሥራት እንደ ሚጠበቅባቸው ግን ግልጽ ነው::

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሥራ እየሠራ እንዲኖር አዝዞታል:: ዛሬ በአንዳንድ ወጣቶች የሚታየው ነገር ሥራን ማማረጥ ነው:: ተሯሩጠ ያገኙትን ከመሥራት ይልቅ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ እንደ አማራጭ የተያያዙት አሉ:: ሰው ከሠራ ያገኛል÷ ይለማል፤ ካልሠራ ደግሞ ይቸገራል፤ ያስቸግራል:: ሰው ምንም እንኳን መልካም ሥራ ቢኖረውም ከሌሎች በልጫለሁ፣ የተሻልኩ ነኝ ብሎ በሥራው ሊመካ አይገባም:: «እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ» ነው የተባልነው:: ሉቃ. 17÷10::

ከታሪክ ሒደት እንደምንማረው በሕይወት ጉዞ ወደ ፊትም ወደ ኋላም መመልከት ያስፈልጋል፣ ወደ ፊት መቀጠል የሚቻለው ከነበረውና ካለው ተነሥቶ ነው፣ መነሻ የሌለው ቅድድም መድረሻውም የት ሊሆን እንደሚችል አጠያያቂ ነው የሚሆነው፣ ካለፈው ኑሮአችን ብዙ ተምረናል፣ የደስታም የችግርም ዘመናት አልፈዋል:: ያለፈውን ማጤን የሚጠቅመው ችግሩን በማስታወስ ከቀጣዩ ጉዞ የተሻለ ኑሮ ለማምጣት ትምህርትና መገሥገሻ እንዲሆን ነው:: ወደ ኋላ መለስ ብለን የቅርብ ጊዜያትን ትዝታ እንኳ ብንመለከት ለርዳታና ለጥገኝነት ያጋለጡንን ችግሮቻችንን እያሰብን ወደ ፊት እንዳይከተሉን የሥራ ፍጥነታችንን ጨምረን ካሰብነውና ከተመኘነው ለመድረስ ይረዳናል::

አገራችን ለራሷ ዜጎች ይቅርና ለጎረቤት ሕዝቦች የሚተርፍ፣ በከርሠ ምድሯ የተከማቸ ማዕድንና የተለያየ የተፈጥሮ ሀብት እንዳላት ይታወቃል:: የስጡትን የሚያበቅል ለም አፈር፣ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ምርት መስጠት የሚያስችሉ ወንዞችና ሐይቆች እንዲሁም ከዓመት እስከ ዓመት ተስማሚ የአየር ጠባያት እንዳሉንም የማንክደው ሐቅ ነው::

በዚህም ሆነ በዚያ አገራችን ሠራተኞችን ትፈልጋለች፣ ሰፋፊ የወይንና የአትክልት ቦታዎች በአጠገባቸው የሚያልፉ ወንዞችን ጠልፎና ገድቦ የሚያለማቸው ባለሞያዎችን ይሻል፣ ለችግራችን ጥግና ምክንያት ከምንሻለት ይልቅ ከድህነታችን ለመውጣት መላ ብንፈጥርለት ይሻላል:: ሌሎች በጥረትና በድካማቸው የለሙና የበለጸጉ አገሮችን አሻግሮ በተስፋ መመልከት፣ በተቸገሩና በተራቡ ቁጥር የርዳታ እጆች ከሌሎች እንዲዘረጉ መጠበቅ ለተፈጥሮ ነጻነት ተቃራኒ የሆነ የሐፍረት ምልክት ነው::

በጥንተ ታሪክ በገነት የነበሩ ሰዎች ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ለጥፋታቸው የደረደሩት ምክንያት ወይም የፈለጉት ሰበብ ከፍትሕ አላዳናቸውም፤ እኛንም የዓለም ኅብረተሰብ መጠቃቀሻና መዘባበቻ ካደረገን ድህነት የሚገላግለን፣ በኅብረት፣ በግልም በጋራም ለሥራ መነሣት እንጂ ምክንያት መፈለግ አይደለም::


በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውም ሰው በስንፍና ምክንያት በሚመጣ ችግር እንዳይጠቃ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይል ተግቶ ሠርቶ ለውጤት እንዲበቃ ታስተምራለች:: ሐዋርያው «ለሥራ አትለግሙ፣ ሊሠራ የማይወድ አይብላ» እንዳለ /ሮሜ. 12÷11፤ 2ኛተሰ.3÷10/ እኛም ተግተን ሠርተን የሥራችንን ዋጋ ማግኘት አለብን:: ሠርተን ለሌሎች ልንተርፍ እንጂ የኅሊናዊ ነጻነትና የቁሳዊ ጥቅም ጥገኞች ልንሆን አልታዘዝንም:: ኤፌ.4÷23:: ቤተ ክርስቲያን ለሥራም፣ ለበዓላት አከባበርም ሥርዓትና ገደብ አላት፤ በበዓላት ሰበብ ማንም ሥራ ፈትቶ እንዲቀመጥ አታስተምርም:: የሃይማኖት መጽሐፍ ራሱ ማንም ሥራ ፈትቶ በመዋል ሌሎች ሠርተው ካስናዱት ማዕድ ቀርቦ እንዲሳተፍ አይፈቅድም፤ ብንስማማ፣ ብንግባባና አንዱ የሚለውን ሌላው ቢረዳለት መልካም ነው:: ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔር እየተማርን በዓለም ሳለን ጥረን የድካማችንን ፍሬ ማየት በምድርም በሰማይም የሚያስመሰግን ነው:: በተሰጠን ጊዜ በተሠማራንበት ሥራ ተግተን እየሠራን ለአገር ለወገን አኩሪ የሆነ ታሪካዊ ሥራ ለመሥራት እንዲያበቃን፤ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ልጆቻችን ኢትዮጵያዊ ኾነው እንዲያድጉ የደረስንበት ውሳኔ አሜሪካ ኾነው ካደረግንላቸው ክብካቤ ይበልጣል»

/አቶ አክሊሉ አረጋና ወ/ሮ እማዋይሽ ወልዴ



*ምንም እንኳን አንዳንዶች በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያዊ መልካቸውን ለውጠው የእነሱ ያልሆነውን «ሲለብሱ» ወይም «ለመልበስ» ሲናፍቁ ቢታዩም ቅዱስ መጽሐፍ «በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?» /ኤር.13÷23/ ያለውን ቃል ጠብቀው ያሉ ኢትዮጵያውያን በሃገር ቤትም ይሁን በውጭ መኖራቸው የማይታበል ሐቅ ነው። የራሳቸውን ኢትዮጵያዊ ልብስ በንጽሕናና በጥንቃቄ «ለብሰው» ልጆቻቸውም «እንዲለብሱ» የሚጥሩ፣ ሌሎችም «ይለብሱ» ዘንድ የሚያተጉ ጥሩ ኢትዮጵያውያን አሉ። በዚህ እትማችን አንድ ይህንኑ ሐቅ በተግባር የምናረጋግጥበት ቃለ ምልልስ ይዘንላችሁ ቀርበናል።*

*እንግዳችን አቶ አክሊሉ አረጋ ይባላል። ኑሮውን በአሜሪካ አትላንታ ካደረገ ዘጠኝ ዓመታት ተቆጥረዋል። በቀላል ቁጥር የማይገመቱ ሰዎች የውጩን ዓለም በሚናፍቁበትና ራሳቸውንና ልጆቻቸውን በአፍርንጁ ቋንቋና አነዋወር «የሠለጠኑ» ለማድረግ በሚጥሩበት ወቅት የጠቀመ ሥራውን ትቶ ራሱንም ኾነ ልጆቹን ከባለቤቱ ለይቶ ከሁለት ልጆቹ ጋር ወደ አገር ቤት በመመለስ የአገሩን ባሕልና ቋንቋ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት እንዲማሩ ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛል። በዋነኝነት በዚህ ጉዳይ ላይ በማተኮር የዚህ እትም የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምድ እንግዳችን አድርገነዋል። መልካም ንባብ።*

<u>ሐመር</u>:- *በመጀመሪያ ግብዣችንን ተቀብለህ እዚህ ድረስ በመምጣትህ በዝግጅት ክፍሉና በአንባብያን ስም እናመሰግናለን። እስኪ ለትውውቅ እንዲረዳን ሙሉ ስምህንና ዕድሜህን ብትነግረን?*

አክሊሉ :- ስሜ አክሊሉ አረጋ እባላለሁ፤ ዕድሜዬ 43 ነው።

ሐመር :- *አሜሪካን አገር ከሄድክ ምን ያህል ሆናሃል?*

አክሊሉ :- የሚመጣው ሰኔ ዘጠኝ ዓመት ይሆነኛል።

ሐመር :- *ክርስቲያናዊ ሕይወት በአሜሪካ ምን ይመስላል?*

አክሊሉ:- አዎ፥ በርግጥ የሰው ልጅ ኑሮውን ይመስላል ነው የሚባለው። አካባቢም ወሳኝነት እንዳለው ነው። አልፎ አልፎ በጣም ጠንካራ ክርስቲያኖች ቢኖሩም እኔን ጨምሮ ብዙዎች በአሜሪካ የሚገኙ ምእመናንን ስመለከት ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ደከም ያለ ነው። ምክንያቱም ቀደም ብሎ የነበረው ሥርዓትም በሃይማኖት እንድናድግ በር የከፈተልን ባለ መሆኑ ብዙዎቻችን ሃይማኖታዊ ትምህርት «ሀ» ብለን የጀመርነው ጊዜው ከገፋ በኋላ ነው ማለት ይቻላል። መሠረታዊ ዕውቀት ስላልያዝንም መናፍቃኑና ሌሎች የውስጥ ጠላቶች ይኽንን ድክመታችንን በመጠቀም እና በጐሳ በመከፋፈል እርስ በርስ ፍቅር እንዳ ይኖረን በማድረግ ዓላማቸውን ለማሳካት ይሯሯጣሉ። በዚህ ላይ እንደ አገር ቤቱ ሳይሆን ቅዳሴ እንኳ የሚቀደሰው ካለው የኑሮ ሁኔታ አንጻር በሳምንት አንዴ እሑድ ብቻ ስለሆነና የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት በበቂ ሁኔታ ለመማር ስላልተመቻቸልን በክርስትና ሕይወታችን ብዙም ጠንካራ አይደለንም። ጠንካራ እንኳ የሚባሉትን ደከም ያሉ መስለው ሊታያቸው ትችላለህ። በአጠቃላይ አሜሪካ ለክርስቲያን የፈተና ቦታ ነው።

<u>ሐመር</u> :- *ብዙ አበው ካህናት፣አብያተ ክርስትያናትና በውስጣቸው የሚገኙ ሰንበት ት/ቤቶች እንደ መኖራቸው መጠን የክርስትናውን ሕይወት ጠንክር እንዲል አላደረጉትም ወይ?*

<u>አክሊሉ</u> :- በእኔ አስተያየት የአብያተ ክርስቲያናቱና የካህናቱ መብዛት ጥንካሬ ሳይሆን ስፋትን ነው እየጨመረ ያለው። ቤተ ክርስቲያን በመስፋፋት ላይ ናት። ይሁንና እርስ በርስ ፍቅር ከሌለ ጥንካሬ አለ ብሎ መናገር ያዳግታል። ተመሳሳይ ታቦት በአንድ አካባቢ የሚተከልበት ሁኔታ አለ። የውድድር የቢዝነስ ዓይነት ሥራ ነው የሚመስለው። እንግዲህ በዚህ መልኩ የሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ቢጨምርም ለምእመኑ ግን በክርስትና ሕይወት መጠንከር ያደረገው አስተዋፅዖ የለም።

<u>ሐመር</u> :- *በሀዋቂነት ደረጃ ያሉት ምእመናን ሕይወት እንዲህ ከሆነ እዚያው የተወለዱትስ ሕፃናት ሕይወት እንዴት ነው በተለይም ደግሞ በሃይማኖት፣በትውፊትም ይሁን በባሕል ኢትዮጵያዊ መልክን ይዞ ከማደግ አኳያ?*

አክሊሉ :- በእውነቱ ሕፃናቱን በኢትዮጵያዊ መልክ ለማሳደግ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ነው ያለው። በአሜሪካ አንድ ሰው በአንድ ሥራ ራሱን አሸንፎ ቤተሰቡን ችሎ ለማኖር ትንሽ ከበድ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ስለሚል ብዙ ጊዜ ሁለት ሥራ ማለትም ከስምንት ሰዓት ወደ 16 ሰዓት ቢያንስ ደግሞ ለ10 እና 12 ሰዓት ያህል ይሠራሉ። ወላጆችም ያን ያህል ጊዜ በሥራ ተጠምደው ውለው መጥተው ከልጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው ጊዜ በጣም አናሳ በመሆኑ ወይም ልጆች ተኝተው፣ ባይተኙም ደግሞ ወላጆች ከመድከማቸው የተነሣ አብረው የመጫወት ዕድል አይኖርም። ስለዚህም ልጆችን በጥሩ ሥነ ምግባር ኮትኩቶ ለማሳደግ ችግር ይኖረዋል። ልጆችም ከወላጆቻቸው ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩት ጓደኞቻቸውና ሲያዩት ከሚውሉት ቴሌቪዥን የሚቀስሙት ትምህርትና ልምድ ነው የሚኖራቸው።ያንን ይዘው ያድጋሉ፤ ወላጆቻቸውን ለመከተል ያዳግታቸዋል።

*ሐመር :- ከወላጆቻቸው አነስተኛ ጥረት ባሻገር በተናጠልም ይሁን በተደራጀ መንገድ ከልጆች አስተዳደግ አንጻር ያለውን ችግር ለመቅረፍ የሚደረግ ጥረት አለን?*

አክሊሉ :-አዎ፥ ችግሮችም ቢኖሩም አንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። የእነሱ ጥረት ጥሩ ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት ያመጣል ብሎ መገመቱ ግን አስቸጋሪ ነው። በዕለተ ሰንበት ወላጆች ወደ ቅዳሴ ሲገቡ ልጆችን ወደ ት/ቤት ወስዶ ፊደል ለማስቆጠር የሚደረግ ጥረት አለ። ይህ ግን በሳምንት አንድ ቀን ብቻ የሚደረግ ስለሆነ ውጤት ያመጣል ብሎ መጠበቅ ከባድ ነው። በአሜሪካ የኢትዮጵያውያን የጋራ ችግር ደግሞ አብሮ መብላት እንጂ በኅብረት ተስማምቶ መሥራት አለመቻላችን ነው። እንደ ሌሎች አገሮች በጋራ ሙዓለ ሕፃናት ከፍተን ልጆቻችንን ልናስተምር እንችል ነበር።

በእኛ ዘንድ ግን እንደዚያ ያለ ኅብረት የመፍጠር ሁኔታ አይታይም፤ የአገራችንን ቋንቋዎች እንኳን ለመጠቀም የማይፈልጉ ወላጆች አሉ። የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ልጆቻቸው እንዳይናገሩ የሚፈልጉ ወላጆችም አጋጥመውኛል። በአጠቃላይ አልፎ አልፎ ጥረቶች ቢደረጉም ይህን የመሳሰሉት ችግሮች ደግሞ አሉ።

*ሐመር:- እዚህም አገር ቤት ልጃቸው አንድ የኢትዮጵያን ቋንቋ አቀላጥፎ ከሚናገር እንግሊዘኛ/ፈረንሳይ/ ቋንቋን እንዲለምድላቸው የሚፈልጉ ወላጆች አሉ፤ እዚያስ እንዲሁ ልጆች ኢትዮጵያዊ መልክ ይዘው እንዲያድጉ በማኅበር የሚደረገው ጥረት እንደ ጠቀስከው ሆኖ በግል ያለው የወላጆች ሙከራ ምን ይመስላል?*

አክሊሉ :- እንዲህ ለመጠየቅ እኮ በመጀመሪያ ወላጅ ራሱ ምን ያህል በኢትዮጵያዊነቱ ይኮራል የሚለው ጉዳይ መታየት አለበት። ኢትዮጵያዊነታቸውን ደብቀው አሜሪካዊ ወይም የሌላ አገር ዜግነት እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ወላጆች እኮ ብዙ ናቸው። የዚያኑ ያህል እኔ በግሌ የማውቃቸው ልጆቻቸው በኢትዮጵያዊ ሰብእና ተቀርጸው እንዲያድጉላቸው የሚፈልጉ ወላጆች ብዙ ናቸው። ሁኔታዎች ምቹ ያልኾኑላቸው ናቸው እንጂ። ብዙ ቢጥሩም ልጆች ወላጆቻቸው የሚፈልጉትን ያህል መሆን አልቻሉም። አንዳንድ ወላጆች እንዲያውም ልጆቻቸውን የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ የሚያደርጉበት ወቅት አለ። ይኸውም ልጆች የአገራቸውን ቋንቋ አውቀው እንዳያድጉ ወደ ኋላ ይጎትታቸዋል።

በሌላ በኩል አያቶች ያሏቸው /በአያት የሚያድጉ/ ልጆች አያቶች በቀላሉ በእንግሊዘኛ ለመናገር ስለሚከብዳቸው ልጆች ከእነርሱ ጋር ለመግባባት ሲሉ አማርኛን ለምደው በተቀላጠፈ ሁኔታ ሲናገሩ ይታያል። በሥነ ምግባርና ባሕሉንም በተመለከተ አያቶቻቸው የሚያደርጉትን እየተከተሉ ጥሩ ዜጋ ሆነው የሚያድጉ ልጆች አሉ።

*ሐመር:- አንተ ከልጆችህ ጋር ነው ወደዚህ የመጣኸው፤ እስኪ እነርሱን አስተዋውቀን?*

አክሊሉ:- የመጀመሪያ ልጄ ኪሩቤል ይባላል። የሰባት ዓመት ልጅ ሲሆን ሁለተኛዋ ልጄ ሩት ትባላለች። ዕድሜዋ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ነው።

*ሐመር:- ስማቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው። እንዴት ነው ስማቸው የወጣላቸው? እነርሱስ ስለ ስማቸው ምንነት ጠይቀውህ ያውቃሉ?*

አክሊሉ:- አዎ፥ ትውልዱ ጠያቂ ነው። ወንዱ ልጄ ስሜ ረጅም «long name» ነው ይላል። እኛም ኢትዮጵያዊ ስም ነው፤ የመልአክ ስም ነው ስንለው ተቀብሎታል። አሰያየሙላይ በአሜሪካን አገር ልጆች ሲወለዱ ከሆስፒታል ሳይወጡ ነው ስም ሊወጣላቸው የሚገባው። ኪሩቤል የቅድስት ሥላሴን መንበር በመሸከም የሚያገለግሉ መላእክት ሲሆኑ፣ የኛም ልጅ ኪሩቤል እግዚብሔርን በማገልገል እንዲኖር ካለን ፍላጐት አንጻር ኪሩቤል ብለነዋል። ሁለተኛዋን ደግሞ ስም በማውጣቱ ባለቤቴ እድሉን ለኔ ሰጥታኝ ነበርና ቀደም ሲል እርሷ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ያሳለፈቻቸው በርካታ ፈተናዎች ስለ ነበሩ ያንን አልፋ ለዚህ ደረጃ መድረሷ ከሩት ሕይወት ጋር ስለ ተመሳሰለብኝ ልጄን ሩት ብያታለሁ።

*ሐመር :- ልጅን እንዴት ነው ያሳደግኸውና ያስተማርከው? ወደ ቤተ ክርስቲያንም ለማቅረብ ያደረግኸውስ ጥረት?*

አክሊሉ :- የልጆች ዕድገት ላይ የማኅበራዊ ሕይወት ገጽታው ወሳኝ ይመስለኛል። ኪሩቤል ከተወለደ በኋላ ባለቤቴ ወደ ት/ቤት መሄድ ነበረባት። ከልጃችን ጋር የምናሳልፈው ጊዜ በጣም አጭር ነበር። እርስዋ ከት/ቤት ስትመጣ ጥናት አለባት፤ የቤቱን ሥራ ሙሉ በሙሉ የምትሸፍነው ደግሞ እርሷው ናት። አሜሪካ ውስጥ የኑሮ ገቢ በአንድ በኩል ሆኖ ስለሚከብድ እኔም በበኩሌ የበለጠ ሰዓትና ከበድ ያለ ሥራ መሥራት ነበረብኝ። ደክሞኝ እመጣለሁ፥ለልጄም በቂ የአባትነት ፍቅሬን መስጠት አልችልም ነበር። በዚህ መልክ ሦስት ዓመት ያህል አሳለፍን። ነገር ግን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁንና በየሰንበቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ለይተነው አናውቅም። ከሚገርመኝ ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድን ከመልመዱ የተነሣ እንደ አንደኛ ቤቱ የሚያይበትም ጊዜ ነበር። እኛ በቤት ውስጥ አማርኛ የምንነጋገር ቢሆንም ብዙ ጊዜውን የሚያሳልፈው ቴሌቪዥን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በማየትና «ጌም» በመጫወት ስለሆነ እርሱ የሚያዘነብለው ወደ እግሊዝኛው ነው:: አማርኛ ስለሚከብደውም ሰምቶ ለመመለስ ይቸገራል፤ ወጣ ብሎ ከጓደኞቹ ጋር እንግሊዝኛ ሲነጋገር በመካከል አማርኛ ቃላትን ሲጠቀም ሌሎች ይስቁበታል:: ጉራማይሌ ነበር የሚናገረው :: በዚህ ዓይነት አስተዳደግ ጥሩ ውጤት መጠበቅ አስቸጋሪ ነው::

ሐመር :- *ወደ ት/ቤትስ እንዴት ገባ?*

አክሊሉ :- ከሦስት ዓመቱ ጀምሮ ወደ ሙዓለ ሕፃናት ይሄድ ነበር:: እዚያ አንደኛ ክፍልን ጨርሶ ወደ ሁለተኛ ሲዛወር ነው እዚህ የመጣው:: እዚያ አገር ትምህርት አሰጣጣቸው ቀለል ያለና ልጆች በማይከብዳቸው ሁኔታ የሚቀርብ ነው:: በአሁኑ ጊዜ እኛም አገር የትምህርት አሰጣጡ የተሻሻለ ይመስለኛል::

ሐመር:- *ወደ አገር ቤት ልጆችህን እንድታመጣ ያደረገህ ምክንያት ምንድን ነው?*

አክሊሉ:- አባቴ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዳድግ ይፈልግ ነበር:: እኔ ግን የቤተ ክርስቲያን ፍቅር ይኑረኝ እንጂ በትምህርቱ አልገፋሁበትም:: ሆኖም ግን አንዲቱ እውነትና ትክክለኛዋ እምነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እንደ ሆነች አምናለሁ:: ይህም በእኔ ሳይወሰን ለልጆቼ እንዲደርስ እፈልጋለሁ:: ስለዚህ የኔ ድርሻ መንገዱን ማሳየት ብቻ ነው የሚሆነው:: በእውነቱ ትምህርቱ የሚጀምረው ከማኅበራዊ ኑሮ ነው:: ባሕላችን እምነታችንን የሚያንጸባርቅ ነው:: ታድያ ይህንን አሜሪካ ውስጥ ለልጆች እንዲህ ነው ብሎ ለማስተማር ያዳግታል:: ስለሆነም ባሕላችን መልኩ ሥርዓቱ ምን እንደ ኾነ ካወቀ ሃይማኖቱንም ይጠብቃል የሚል እምነት አለኝ:: አማርኛ ቋንቋ ማንበብና መጻፍ እንዲችል ከሁሉም ቅድሚያ የምሰጠው ነገር ነው:: ቢቻል ግእዙን ዐውቆ ቅኔውንና ሥርዓተ ዲቁናውን ተምሮልኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ እንዲያድግልኝ ስለፈለግሁ ነው ወደዚህ ያመጣሁት:: በእውነቱ በዚህ አጋጣሚ አሳቤን ተቀብላ ስለ ረዳችኝ ባለቤቴንም ሳላመሰግናት አላልፍም::

ሐመር :- *ለመሆኑ ባለቤትህ ማን ትባላለች? እሷ ብቻዋን እዚያ ቀርታ አንተና ሕፃናት ልጆቻችሁ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመጡ እንዴት ፈቀደች? አልተቸገረችም?*

አክሊሉ:- እማዋይሽ ወልዴ ትባላለች:: ትልቁ ልጄን በሰባት ዓመቱ ነው ያመጣሁት፡ ትንሽዋ ልጄ ገና ሁለት ዓመቷ ነው:: የመምጣታቸውን ዓላማ ብትደግፈውም መራቃችንና ከእኛ መለየትዋ እየከበዳት ነው:: የእኔ ግፊት ስላለ እኔንም ለማስደሰት ጭምር ማለት ነው:: መሥዋዕትነቱን የከፈለችው እርስዋ ነች:: እኔ እንኳን ከልጆቼ ጋር ነው የመጣሁት:: ከአንድ ዓመት በፊት ለአንድ ወር ጊዜ ያህል መጥተን ነበር:: ከእኔም ከእርስዋም ቤተሰቦች ጋር ልጆቹ ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይፈጥሩ ነው የተመለሱት:: ቤተሰቦቻችን በአማርኛ ነው የሚያወሩት ቋንቋውን መረዳትና መግባባት ባለመቻላቸው እንዲሁ ብቻ እየተሳሳቁ ቆይተው ነበር የተመለስነው:: ያ ሁኔታ አእምሮዬ ውስጥ መጥፎ ሁኔታን ነው የቀረፀብኝ:: በአጋጣሚ እኛ አንድ ነገር ብንሆን እንኳን ልጆቹ ወገኖቻችን ወደሚሏቸው መጥተው መገናኘት መቻል አለባቸው:: በቋንቋ መግባባት ካልተቻለ ለዚህ ችግር ይፈጥራል ከሃይማኖቱ ባሻገር:: በልጆች አስተዳደግ ረገድ ላለብን ችግር ጥሩ መፍትሔ ይመስለኛል::

በተለያየ የሥራ መስክ ያሉ ጓደኞች አሉኝ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን የቀረቡቱ ዓላማውን ሲደግፉ ስለ ሃይማኖታቸው ግድ የሌላቸው ደግሞ ፊት ለፊት እርስዋን «እንዴት ባልሽን ትሰጂዋለሽ?» እኔንም «ምን መኾንህ ነው?» ብለው በከፍተኛ ሁኔታ ነው ያወገዙኝ:: ዓላማውን የጠሉ ብዙ ሰዎች አሉ:: አንዳንዱ ስለ እምነቱም ስለ አገሩም ግድ የሌለው ሰው ነው:: ግማሹ ስለ አገሩ ቢጨነቅም ስለ እምነቱ ግድ የለውም፤ እንዲህ ያለውን ዓላማ አይደግፍም:: ስለ ሃይማኖታቸው ግድ ያላቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያበርታችሁ÷ ያጠንክራችሁ በማለት ድጋፍ ሰጥተውናል:: አሁንም ባለቤቴን እያረጋጉዋትና እያጠናከሩዋት ነው:: በሌላ በኩል ልጆቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ አሳድገው ወደ አሜሪካ ከሄዱ በኋላ የጠፉባቸው የተለወጡባቸው ብዙዎች አሉ:: እነዚህን የተመለከተ ሰው «ይህን ሁሉ ዓመት ቆይተው መጥተው እንዲህ ከኾኑ ሁለትና ሦስት ዓመት አገር ቤት ስለ ተቆየ ምን ለውጥ ይመጣል?» የሚሉም አሉ::

የእኔ ግምት በአንድና በሁለት ዓመት ውስጥ ብዙ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚል አይደለም:: ቢሆንም እንደ ቤተሰብ ኃላፊነቴ ግዴታዬን መወጣቱ ላይ ነው ቁም ነገሩ:: ልጄ የምፈልገው ዓይነት ቢሆንልኝ ምኞቴ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያገለገለ ሕይወቱን እንዲመራልኝ እፈልጋለሁ:: ዐቅሜ በፈቀደ መጠን ለዚህ ዓላማ ስኬት እረዳዋለሁኝ:: በእኔ ቁጥጥር ስር እስከ ኾነ ድረስ ግን የማምነውን እንዲከተል እፈልጋለሁ:: አሜሪካ ውስጥ ባለው ዴሞክራሲ ሰው የራሱን እምነትና ፍላጎት እንዲከተል ይተዋል:: እኔ ጋር እንኳን ይህ ነገር ተቀባይነት የለውም:: የምከተለው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጥርጥር የሌለበት ስለሆነ በዚያ እንዲወሰን ጥረት አደርጋለሁኝ::

ሐመር :- *ወደዚህ ስትመጣ ከልጆችህ ጋር በተለይ ከኪሩቤል ጋር እንዴት ተነጋገራችሁ? እንዴት ነው ያሳመንካቸው?*

አክሊሉ :- አሁን ያለው ትውልድ በእውነቱ ፈጣን /ንቁ/ ነው:: ከኪሩቤል አንጻር ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ስትመለከተው ማለቴ ነው:: በቅድሚያ የነገርናቸው እናታቸውም አብራቸው እንደምትመጣ ነበር:: በይበልጥ ኪሩቤል ከእናቱ ጋር ከፍተኛ ቅርበት /attachement/ አለው::

ኪሩቤል ያስቸግረናል የሚል ፍራቻ ስለነበረን ሳንነግረው ነበር እስከ አየር ጣቢያ የሄድነው:: ኤርፖርት ላይ ባለቤቴ ስትሰናበተን «ነዬ እንጂ ÷የት ልትሄጂ ነው» አላት:: «በሚቀጥለው በረራ /ፍላይት/ እመጣለሁ» ስትለው ያለችውን አምኖ ወደ አውሮፕላኑ ገባን:: ከገባን በኋላ አየር መንገዱ ውስጥ የብዙ አውሮፕላኖች እንቅስቃሴ ስለነበር «ይኸኛው ነው የእርሷ? የእርሷ ይሄ ነው?» እያለ አስቸግሮኝ ኒውዮርክ ደረስን:: እኔም እያዘናጋሁ እያታለልኩኝ ቆይቼ ኢትዮጵያ ከደረስን በኋላ «እርስዋ ትሠራለች፤ ሠርታ ገንዘብ ትልክልናለች፤ አንተም በጠባይህ በጣም ጎበዝ ልጅ ኾነህ አማርኛ ማንበብ፣መጻፍ ስትችል የዚያን ጊዜ እንሄዳለን» አልኩት:: በተለያየ ጊዜም የራሱን፣የእኅቱን፣የእናቱንና የእኔንም ስም እየጠራ «we are one fa mily »/ ቤተሰቦች ነን/ «we have to live together» /አብረን በአንድነት መኖር አለብን/ ይላል:: ይህ ግልጽ ነው:: ዓላማችንን ለማሳካት ብለን ለዚያ መሥዋዕት ለመሆን ብለን እንጂ:: ይህን በተናገረበት ዕለት ስቄ አለፍኩት:: እስከ አሁን ድረስም ያስቸግረኛል:: በዚያውም ላይ ሩት ቅርበቷ ከኔ ጋር የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ዕድገትና ብስለት ታክሎበት ከእናትዋ ጋር ያላት «attachement» እየጠበቀ በመምጣቱ ባለቤቴ ተመልሳ ስትሄድ ትንሽ ሳታስቸግር አትቀርም የሚል ፍራቻው አለኝ::

ሐመር :- *ባለቤትህ የመጣችው ልትጎበኛችሁ ነው ማለት ነው?*

አክሊሉ:- አዎ÷ ለልደት በዓል ለመምጣት ነበር ያቀደችው፤ የሥራ መደራረብና የትኬትም አለመስተካከል ችግር ተፈጠረና የጥምቀትን በዓል ተመርኩዞ ለአንድ ወር ተኩል የዕረፍት ጊዜዋን ከእኛ ጋር ለማሳለፍ መጣች:: እኛ ከመጣን ጊዜ ጀምሮ ብቸኝነትም እንዳይሰማት ቀንና ሌሊት ያለ ዕረፍት ራስዋን በሥራ ትጠምድ ስለነበር ደካክማ ነበር:: በዚያውም የተቀሩት ቤተሰቦቿን ለመጠየቅ ጭምር ነው የመጣችው::

ሐመር:- *ከቋንቋውም ሆነ ከባሕሉ መቀየር ጋር በመጣችሁ ሰሞን ልጆቹ አላስቸገሩህም?*

አክሊሉ:- አዎ:: በተለይ ኪሩቤል አስቸግሮኛል:: ኢትዮጵያ በመጣን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በሦስተኛው ቀን ሌሊት ተኝተን ባልጠበኩት ሁኔታ በጣም ተንሰቅስቆ አለቀሰ:: ደንግጬ «ምን ሆንክ?» ብለው፤ "I miss mammy - እማማን አጣሁአት» አለኝ:: በተለያየ መንገድ ሳባብለው ሞከርኩ:: ነገር ግን ዝም ሊል አልቻለም:: ከዚያም ቆጣ ብዬ ለቅሶውን እንዲያቆም አደረግሁት:: ትንሽ ቆየና "Daddy let me ask you a question; አባባ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?» አለኝ:: «ጠይቀኝ» አልኩት:: "Do you have wife; ሚስት አለችህን?» አለኝ:: እኔም በጥያቄው ተገርሜ "Yes, of course; አዎን!» አልኩት:: እርሱም "Where is she? የት አለች?» አለኝ:: " She is in America; አሜሪካ ነች» አልኩት:: ትንሽ ቆየና በእጅጉ የገረመኝንና የፈተነኝን ንግግር ተናገረ:: "If you don't love her, if you don't live with her, how she gonna' be your wife ÷ እርሷን ካልወደድካት፣ አብሩህም ካልኖረች እንዴት ሚስትህ ልትሆን ትችላለች?» አለኝ:: በእውነት ይህ ንግግሩ በእጅጉ ገርሞኛል፤ ከዚያም አልፎ ውስጤን አውኮታል:: ነገር ግን ዓላማ ስለሆነ መታገል ይኖርብናል::

*ሐመር :- የት ግዛት /ስቴት/ ነው የነበራችሁት?*

አክሊሉ :- በጆርጅያ ስቴት አትላንታ ከተማ ውስጥ ነው የምንኖረው::

*ሐመር :- እዚህ ከመጣህ በኋላ ካሰባችሁት ዓላማና ዕቅድ አንጻር እያደረግህ ያለኸውን ነገር ብትነግረን?*

አክሊሉ :- በርግጥ ይህ ጅምር ነው፤ ከወዲሁ ይህ ነው ብሎ አሳብ ለመስጠትም ይከብደኛል:: እግዚአብሔር ፍጻሜውን ያሣምረው:: ልጆች አእምሮአቸው ክፍት ነው፤ በአጋጣሚ ት/ቤቱም፣የጤንነቱም ሁኔታ እንዳይጓደል በትምህርቱም ወደ ኋላ እንዳይቀር በሚል በግሪክ ኮምዩኒቲ ት/ቤት አስገብቼዋለሁ:: ት/ቤታቸው የግሪክ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ያስተምራሉ:: አማርኛም እንዲሁ:: መደበኛ ትምህርቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነው የሚሰጠው:: ይህም ወደ ዚያው ሲመለስ ትምህርቱ ላይ ምንም ችግር አይፈጥርበትም:: በዚህ ደስ ይለኛል:: በተጨማሪ ቤት ውስጥ አስተማሪ ተቀጥሮለት ት/ቤት የተማረውንና የአማርኛ ቋንቋ ችሎታውን እንዲያዳብር እያገዝነው ነው:: አሁን የአማርኛ ፊደላትን ከመለየት አልፎ መጻፍም ማንበብም የቻለበት ደረጃ ላይ ነው:: የተቀላጠፈ ባይሆንም መንገድ ላይ ሲጓዝ ሁሉ ጽሑፎችን ያነብባል::

አሜሪካ ውስጥ በአማርኛ ካልኾነ በእንግሊዝኛ አልመልስለትም ነበር፤ እዚህ ግን በትምህርቱም ለማገዝ ስል በአማርኛም የመነጋገር ዕድሉ ሰፊ ስለሆነ እንግሊዘኛ እየቀላቀልኩም እረዳዋለሁ::

ይህ እንግዲህ ጅምሩ ሲሆን ትልቁ ዓላማዬ ግን ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩልህ ሥርዓተ ዲቁናን ተምሮ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ነው::

*ሐመር :- በወገናችው መካከል መኾናቸው መልካም ነው፤ አንተም ለበዓል ይዘሃቸው መጥተህ አይቼሃለሁ፤ ነጭ ልብስ አልብሰህ ወደ አባቶች ጋር ማቅረብ፣ወደ ንግሥ በዓላት መውሰድ ፣ታሪካውያንና ቅዱሳት መካናትን ማሳየት፣ትምህርቶች በሰንበት ት/ቤት እዚያ እንዲገኙ ማድረግ፣ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ሥርዓተ አምልኮውን በጨቅላ አእምሮአቸው እንዲቀርጹቸው በማድረጉ ረገድ ምን አድርገሃል?*

አክሊሉ :- በርግጥ ያልካቸው ሁሉ መደረግ አለባቸው:: ለልጆች በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይትና ትምህርት ብዙም አያስተምራቸውም:: ከነባራዊው ሁኔታ እንዲማሩ እንጂ:: በዚህ መሠረት የደመራን፣ የልደትንና የጥምቀትን በዓል እንዲያዩ በልቡናቸው ሰሌዳም ተቀርጾ እንዲቀመጥ ጥረቶችን አደርጋለሁ:: በየእሑዱ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ እናስቀድሳለን:: አልፎ አልፎም ይቆርባሉ:: እንዲያውም በሆነ አጋጣሚ ሳይሄዱ ቢቀሩ እንኳን ለምን ቀረን ብለው ይጠይቃል:: የእኔም ዋናው ዓላማዬ ይኸው ነው:: በርግጥ ያለ እናት ቤተሰብን መምራት ቀላል አይደለም:: በውጭ ብቻ ሳይሆን ቤት ውስጥም መከባከብ አለብኝ:: እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ፊት ሁኔታዎች ሲመቻቹ የተለያዩ ገዳማትንና አድባራትን ሄደው እንዲጐበኙ አደርጋለሁ::

*ሐመር :- ኢትዮጵያዊውን መልክ በመላበሱ ረገድ አሁን የደረሱበት ደረጃ ምን ይመስላል፤ ስለ ባሕላቸውም ይሁን ሌላ ጉዳይ ይጠይቁሃል?*

አክሊሉ :- እንደ ነገርኩህ ትንሽዋ ሩት ሁለት ዓመት ከሰባት ወሯ ነው:: ስትመጣ አንዳንድ ቃላት ከመናገር ውጭ አፏን አልፈታችም ነበር:: አሁን አፍ የፈታችው በአማርኛ ነው:: ኪሩቤል አማርኛ ማንበብና መጻፍ ችሏል:: ሌላው በየመንገዱ ባየ ቁጥር ድሃ ናቸውና ፍራንክ እንስጥ እያለ ከእኔ ወስዶ ለመስጠት የሚያደርገውም እንቅስቃሴም እያስደሰተኝ ነው::

*ሐመር :- የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት የአገራቸውን ባሕል የሚያስጠና ሰው አግኝተሃል?*

አክሊሉ :- አዎ÷ ለአሁኑ የቀለም ትምህርቱ ላይ ትኩረት ሰጥቼ አንዲት አስተማሪ አግኝቼለታለሁ:: ከት/ቤት መልስ በየቀኑ ለአንድ ለአንድ ሰዓት የሠራውን የቤት ሥራ ትከታተላለች:: እኔም አንዳንድ ምዕራፍ ወደ ፊት እንድታስጠናው እያደረግሁ ነው:: የቤተ ክርስቲያኑን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ለማግኘት ከሰዎች ጋር እየተነጋገርኩ ነው:: በቅርቡ ጥሩ ሰው ካገኘሁኝ ዓላማዬ እንደ ተሳካልኝ ያህል ደስተኛ እሆናለሁኝ::

*ሐመር :- በመጨረሻ በውጭም ኾነ በአገር ቤት ላሉት ኢትዮጵያውያን የምታስተላልፈው መልእክት ካለህ?*

አክሊሉ :- በእውነቱ ማንም ወላጅ ለልጆቹ የማይቆረቆርና የማያስብ የለም:: ልዩነቱ ግን የሚመኝለትና ልጁ እንዲያድግ የሚፈልገው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝና ለልጁም ዘላለማዊ ሕይወት ጠቀሜታ ባለው መንገድ ነው ወይ? ነው ጥያቄው::

እዚህ ያሉ ኢትዮጵያውያን ልጆቻቸውንና ባሕላቸውን ለማስተማር ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ ብዙ ችግር የለባቸውም:: ዋናው ልጆቹ የባሕላቸውና የሃይማኖታቸው ፍቅር እንዲያድርባቸው ወላጆች አርአያ ሆነው መገኘት ብቻ ነው::

በሌላ አንጻር በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ግን ልጆቻቸውን ወደ ተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ገዳማት በመውሰድ ስለ ሃይማኖታቸው ለማሳወቅ እንዲሁም በኢትዮጵያዊ ባሕል ለማሳደግ ሁኔታዎች ላይመቻችላቸው ይችላል:: ቢሆንም ግን እቤት ውስጥ ያላቸውን ትርፍ ጊዜ በመጠቀም ፊደል ቢያስቆጥሯቸው እንዲሁም እቤት ውስጥም ይሁን በተቻለው አጋጣሚ ሁሉ በአማርኛ እንዲናገሩ ማድረግ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ስለ ሃገራቸው የተጻፉ መጻሕፍትን በሥዕልና በቪዲዮ የቀረቡ ኢትዮጵያንና ባሕሏን የሚያንጸባርቁ ነገሮችን ቢያሳዩዋቸው ልጆቹ ስለ ሃገራቸው ፍቅር ያድርባቸዋል ብዬ አምናለሁ:: በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን አንድ ላይ በመሆን ልጆቻቸው ከት/ቤት መልስ የሚገናኙበትና አብረው የሚያሳልፉበት ቦታ /ለምሳሌ እንደ ሙዓለ ሕፃናት/ ቢያመቻቹ ጥሩ ነው እላለሁ:: በውጭ ያሉ መንፈሳዊ አባቶችም በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ትውልድ እንዲፈጠር የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ቢያደርጉ መልካም ነው::

ከዚህም ባለፈ ምንም እንኳን ችግር እንዳለው ባውቅም ልጆች እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ የሚኖራቸውን ደግ ወይም መጥፎ ጠባይ የሚቀርጹት በሕፃንነታቸው ጊዜ በመሆኑ በተቻለ መጠን በውጭ የሚኖሩ ወላጆች እንደምንም ብለው ልጆቻቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ባሕላቸውን፣ ትውፊታቸውንና ቋንቋቸውን እንዲሁም ሥርዓተ እምነታቸውን እንዲያውቁ ቢያደርጉ ጥሩ ነው:: ዛሬ እሬት የሆነው ነገ ይጣፍጠናልና::

◈ ◈ ◈

*ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከወ/ሮ እማዋይሽ ወልዴ ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ እናቀርባለን:: ከፍ ሲል ካቀረብነው ቃለ ምልልስ ለመረዳት እንደቻልነው የአቶ አክሊሉ አረጋ ባለቤት ወ/ሮ እማዋይሽ ወልዴ ከወራት ናፍቆት በኋላ ከሚወዷት ቤተ ሰዎቿ ጋር ለመገናኘት ወደ ኢትዮጵያ መጥታ ነበር:: ይህንን ቃለ ምልልስ*




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያደረግነው ከቤተ ሰዎቿ ጋር የነበራትን የሰቀቀን ቆይታ አጠናቅቃ ለዓላማዋ ስትል ከነምሬቱ የተቀበለችውን የብቸኝነት ኑሮ ልትቀጥል ወደ ምድረ አሜሪካ ጥቂት ቀናት ሲቀሯት ነው::

ሐመር:- በምትኖሩበት ሃገር በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንደምትሳተፊ ሰምተናል:: ለመሆኑ በየትኛው አጥቢያ በምን መልኩ ነው የምታገለግይው?

እማዋይሽ:- እግዚአብሔር ይስጥልኝ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን የምሔደው እንደ ተባለው ለማገልገል ሳይሆን ለመገልገል ነው:: ስለዚህ የምገለገለው በአትላንታ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው:: ከሌሎች እኅቶቼና ወንድሞቼ ጋር በመሆን ከ15 ቀናት አንድ ቀን በመሔድ በሰንበት ት/ቤት በጋራ እየዘመርን እንገለገላለን::

ሐመር:- እናትነት በአሜሪካ እንዴት ነው?

እማዋይሽ:- እናትነት በአሜሪካ በጣም ከባድ ነው:: ያው እንደ ሚታወቀው አንዲት ከሌላ ሃገር የሔደች እናት በአሜሪካ ኑሮን የማሸነፍ ኃላፊነት ስላለባት ሙሉ ጊዜዬን ለልጆቼ ሰጥቼ ቤት ውስጥ ልቀመጥ ማለት አትችልም:: ስለዚህ ልጆች ቤት ውስጥ ወይም ሕፃናት ማቆያ ትቶ ሲሠሩ መዋል አለ፣ ማታ ሲገባም ድካም አለ፣ እናትም ሆነች ልጆች የሚፈልጉትን ያህል ፍቅር መለዋወጥ አይቻልም:: ስለዚህ በእኔ አስተያየት በአሜሪካ እናትነት ከባድ ነው::

ሐመር:- ኪሩቤልና ሩት በኢትዮጵያዊው ሥርዓትና ትውፊት እንዲያድጉ በማድረጉ ረገድ ያደረግሽው ጥረት ምን ይመስላል?

እማዋይሽ:- እንግዲህ በሚቻለኝ ሞክሬ ነበር:: ትርፍ የሚባል ጊዜ ባይኖርም እንደምንም ቋንቋቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያውቁ ጥረት አድርጌ ነበር:: ነገር ግን እኔም ሆንኩ አባታቸው አልረካንም:: ስለዚህ በምንፈልገው መጠን ለውጥ እንዲያመጡ ይህንን ውሳኔ መወሰን ነበረብን:: በእርግጥ መጀመሪያ አሳቡን ያመጣው ባለቤቴ ነበር:: በጉዳዩ ከተወያየን በኋላ ለወዲያው ቢከብደኝም መሆን ስላለበት ተቀበልኩት:: ስለዚህ ልጆቼ ኢትዮጵያውያን ሆነው እንዲያድጉ አሜሪካ ሆነው ካደረግሁላቸው ክብካቤ ይህ ውሳኔዬ የበለጠ ይጠቅማቸዋል የሚል እምነት አለኝ::

ሐመር:- ለምን?

እማዋይሽ:- እዚህ ኢትዮጵያዊውን እምነት፣ ባሕልና ሥርዓት የሚማሩት በስማ በለው ወይም በጠረጴዛ ዙሪያ ሳይሆን በቀጥታ እየኖሩት ነው:: በዚህ የተነሣ ምንም እንኳን ለጊዜው እነሱም ሆኑ እኛ ወላጆቻቸው ብንጐዳም ልጆቼ እድለኞች እንደ ሆኑ ይሰማኛል::

ሐመር:- አንቺ እዛ ብቻሽን ቀርተሽ የምትወጃቸው ባለቤትሽና ልጆችሽ ወደዚህ ሲመጡ አልከበደሽም?

እማዋይሽ:- በእርግጥ በጣም ከባድ ነው:: እኔ በሰው ሀገር ሆኜ በአንድ ጊዜ ሦስቱ ም ቤተሰቦቼ ሲለዩኝ ምንም እንኳን ጓደኞቼ ሁል ጊዜ ቢያጽናኑኝም እቸገር ነበር:: ሥራ ውዬ ስገባ እጨነቅ ነበር:: የሆነው ሆኖ አስብ አስብና የዛሬው የእኔ ችግር ከነገው የልጆቼ የማንነት ማጣት ችግር አይበልጥም በማለት ተጽናንቼ እኔም ሆንኩ አባታቸው ያሰብነው እንዲሠምር እጸልያለሁ::

ሐመር:- ለመሆኑ ይህንን ,የዩ ወዳጆቻችሁ እዚያ ምን ይሉሻል?

እማዋይሽ:- ሁለት ዓይነት አስተያየት ነው የሚሰጡኝ:: የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆኑት ትልቅ መሥዋዕትነት ነው:: ጥሩ ነው÷ ወደፊት የምትኮሩበት ነው ይሉኛል:: ሌሎቹ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን የማያውቋት፣ ስለ ኢትዮጵያዊ ባሕልና ሥርዓት ግድ የሌላቸው ይኸ እብደት ነው:: አብዳችኋል:: ልጆች በአባት ፍቅር ብቻ ማደግ የለባቸውም:: የአንቺንም ፍቅር ይፈልጋሉ ይላሉ:: ነገር ግን እኔ ሁላችንም በሕይወት እስካለን ድረስ እናታቸው ነኝ:: አያጡኝም:: ነገር ግን ዛሬ ካጡት እስከ መጨረሻው የሚያጡት ነገር አለ:: ይኸውም ኦርቶዶክሳዊው የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት፣ ኢትዮጵያዊው ባሕል ነው:: ስለዚህ ውሳኔያችን ትክክል ነው እላቸዋለሁ::

ሐመር:- ለመሆኑ የእናንተን አርአያነት ለመከተል ያሰቡ ሰዎች አጋጥመውሻል?

እማዋይሽ:- አዎ÷ አንድ ሁለት ቤተሰቦች አጋጥመውኛል:: ምንም እንኳን አሁን ልጆቻቸው ገና ጨቅላዎች ቢሆንም እነርሱም ወደ ፊት እንደ እኛ እንደ ሚያደርጉ ነግረውኛል::

ሐመር:-አንቺ እዚህ፤ እነሱ እዚህ ሆነው እንዴት ነበር የምትገናኙት?

እማዋይሽ:- ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ ስልክ እደውላለሁ:: ሰዎች ሲሄዱና ሲመጡም በደብዳቤና በፎቶ ግራፎች እንገናኛለን::

ሐመር:- ከሰባት ወራት በኋላ እነ ኪሩቤልን እንዴት አገኘሻቸው?

እማዋይሽ:- በጣም ጥሩ ኢትዮጵያውያን ልጆች ሆነው ልኛል:: ኪሩቤል አማርኛ በሚገባ ይናገራል:: ይጽፋልም:: መጀመሪያ ቋንቋውንና ባሕሉን ማወቅ ስለ ነበረበት በቤተ ክርስቲያን ትምህርት በኩል ገና ጅምር ላይ ነው:: ከአሁን በኋላ በሳምንት አንዴ ከማስቀደስ ባለፈ ሁኔታ ከበሮውንም ጸናጽሉንም ሌላውንም የቤተ ክርስቲያን ባሕል እንዲለምድ ሁኔታዎች እየተመቻቹለት ነው::

ሐመር:- እዚያ ላሉ እናቶች የምታስተላልፊው መልእክት ካለ?

እማዋይሽ:-ልጆች ለእምነታቸው፣ ለታሪካቸው፣ለባሕላቸው ሁሉ ባዕዳን እንዳይሆኑ፣ በኢትዮጵያዊ ማንነታቸው እንዳያፍሩ ወላጆች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው:: ቢቻል ልጆቹ በቀጥታ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ወደ ሚያገኙበት አገራቸው በተወሰነ ደረጃ እያመጡ እንዲማሩ ቢያደርጓቸው፤ ካልተቻለ ግን እዚያው ባላቸው ጊዜ ቋንቋቸውን፣ እምነታቸውንና ባሕላቸውን ቢያስተምሯቸው መልካም ነው:: እኔ ያጋጠመኝ አንድ የ13 ዓመት ኢትዮጵያዊ ልጅ አለ:: እርሱ ኢትዮጵያዊ ነህ ሲባል በጣም ያፍራል፤ ያለቅሳልም:: ስለዚህ ልጆቻችን ሲያድጉ በማንነት ጥያቄ እንዳይቸገሩ በውጭ የምንኖር ወላጆች ከባድ ኃላ ፊነት አለብን:: በእኛ ጉዳት ልጆቻችን መጠቀምና ሰው መሆን አለባቸው::

ሐመር:- እግዚአብሔር ይስጥልኝ::

እማዋይሽ:- አሜን::

የካቲት ፳፮ 1996 ዓም

[illegible]

[illegible]

[illegible]



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «ተገናኝተን ስንጫወት እኔ እኮ በተክሊል ባገባ ነው አሉኝ፤ 'ለዩ እንዲህ ያለ አነጋገር በእርስዎ እንደበት መነገር የለበትም' አልኳቸው»/ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ/



ካለፈው የቀጠለ

ባለፈው እትማችን ከ94 ዓመቱ የዕድሜ ባዕለ ጸጋ ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ጋር ያደረግነውን ውይይት የመጀመሪያ ክፍል አቅርበናል:: በዝግጅቱም ብፁዕነታቸው ስለ ትምህርት ሕይወታቸውና በዚያ ወቅት ስላጋጠሟቸው አስደሳችና አስከፊ ነገሮች አጫውተውናል:: በዚህ እትም ደግሞ የቀረውን ያወጉናል:: አያይዘንም ብፁዕ አባታችንን በቤታቸው ተቀብለው እየረዷቸው ካሉት ከአቶ ብርሃኑ ወዳጄ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ አቅርበናል:: በዚህ አጋጣሚ በጽሕፈት ረገድ በነበረው የኮምፒዩተር ችግር ለታዩት አንዳንድ የሆሄያት ግድፈቶች ከፍ ያለ ይቅርታ እንጠይቃለን::

ሐመር- ብፁዕ አባታችን በገለ ጹልን ሁኔታ የካ ሚካኤል ዘግተው ሲ ኖሩ ወደ ቤተ ክህነቱ እንዴት ታዋቂነትን አግኝተው ለዚህ ታላቅ መዓረግ ሊበቁ ቻሉ?

ብፁዕ አባታችን - በዚያ ጊዜ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ባለቤት ነበር የሚቀደሰው:: በፍልሰታ አባ ሐና ቅዳሴ ማርያምና ውዳሴ ማርያም ከሚተረጉሙት አንዱን ይላኩልን ብለው ወደ አለቃ ልሳነ ወርቅ /በወቅቱ የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል አለቃ/ ይልካሉ:: እኔን «ሂድ» ይሉኛል:: «አይ! እኔ ከባላገር ነው የመጣሁት:: የከተማ ልምድ የለኝም» አልኳቸው:: እርሳቸው ግን «አይሆንም፤ አንተ ነህ የምትሄደው» አሉኝ:: እኔም በአሳቤ ጸንቼ «አይሆንም፤ አልሔድም» አልኳቸው:: ግን ተሸንፍኩና ወደ ምስካየ ኅዙናን ሔድኩኝ:: በዚያም የሐዲስ ኪዳን መምህር ተብዬ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ተርጓሚ ሆንኩ:: ታድያ ወቅቱ ፍልሰታ ስለነበር ውዳሴ ማርያሙን በሚገባ ሳሔደው ቆየሁ:: በዚህም የገዳሙ አስተዳዳሪዎችና እነ አባ ሐና ወደዱኝ:: ከዚያ ከፍልሰታ በኋላ በወር 50 ብር አውጥተንልሃል:: ድርጎም አሠጥተንልሃል ተባልኩ:: ልብሴንም ሙሉ እጀ ጠባብ አለበሱኝ:: መኝታም ሰጡኝ:: አልጋም ፍራሽም አንድ ነገር ሳይጐድል ሰጡኝ:: እዚያ ሳለሁ አቡነ ይስሐቅ የትግራይ ሊቀ ጳጳስ ባሕታዊ ነበሩ:: ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ከቤተ መንግሥት ነበሩ:: ታድያ ምስካየ ኅዙናን ሳለሁ መጽሐፈ መነኮሳት የሚተረጉም ጠፍቷል:: አንተ ተማር አሉኝ:: መጽሐፈ መነኮሳት ላቁዮኝምና ከዚያ ከምስካየ ኅዙናን ወደ እቲሳ ገዳም ተሾምኩ::

በእቲሳ ገዳም ሳለሁ በአካባቢው የሚኖሩት ካህናትና ደብተሮች የገዳሙን እኽል እየተካፈሉ እየወሰዱ ብዙዎቹ መነኮሳት እየተሰደዱ አለቁ:: ታድያ አጠናሁ አጠናሁ እና ካህናቱንና የደብሩን ደብተሮች ሰብስቤ «የገዳሙ ገቢ በገዳሙ የሚኖሩ ረዳት የሌላቸው ሽማግሌዎች እንዲረዱበት፣ አሳዳጊ የሌላቸው የድሆች ልጆች እንዲ ያድጉበት ቅዱሳን ባሕታውያን እንዲ ረዱበት ነው:: እናንተ ቤት ንብረት መሬት አላችሁ፤ የገዳሙን ንብረት እየተካፈላችሁ ገዳሙን እንዳልነበረ የምታደርጉት እግዚአብሔር ይፈርድጠ ብናል ብላችሁ አትፈሩም እንዴ! እንደ ቀድሞው እንጀራ ይጋገር፣ ዳቦውም ይጋገር፣ ንፍሮውም ይቀቀል በማኅበርም እንመገብ» አልኩና ከዚያ በኋላ የገዳሙን እኽል ማንም እንዳይወስድ አዘዝኩ::

ከዚያ እህሉም ለገዳሙ ይገባ ጀመር፤ እንጀራም ይጋገር፣ ንፍሮም ይቀቀል ጀመር:: ከዚያ ጥቅሙ ስለ ቀረባቸው የአካባቢው ሰዎች ተሰብስበው መጡና «አንካሳ፣ በእንፉቅቅ የሚሄድ፣ እከካም ውዳቂ ማኅበር ምን ያደርግሎታል? መነኰሳቱ አልሠሩ:: እርስዎም ይብሉ፤ እኛም እንብላ:: ሰጋር በቅሎ እንግዛልዎ:: ለአሽከሮችዎም ልብሳቸውን እናልብስ» አሉኝ:: እኔም ነገሩ ገባኝና «እሺ ላጥናው ጊዜ ስጡኝ» አልኳቸው:: ከዚያ በሳምንቱ ተመልሰው መጡና ጉች ጉች አሉ:: «ተቃጥረን ነበር» አሉኝ:: «አዎ÷ ተቃጥረን ነበር» አልኳቸው:: «ታዲያስ?» አሉኝ:: እኔም «እንደ





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እናንተ አሳብ መራመድ አልችልም:: ከእነዛ ጋር መፏቀቁ ይሻለኛል» አልኳቸው:: መልስ አልሰጡኝም:: ብድግ ብድግ እያሉ ሄዱ:: ታዲያ እንደበድበዋለን እያሉ ያስወሩ ጀመር:: እኔም «ምንም ይሁን አልፈራም ይምጡ፤ የገዳማውያኑ ጸሎት ይጠብቀኛል» አልኩ:: ደግሞ አጋፋሪ ይገዙ የሚባሉ ነበሩ:: ዑራኤል ነው የሚያገለግሉት:: አስማማን ብለው ወደ እኔ ይልኳቸዋል:: እርሳቸውን አልቀበልም አልኳቸው::

ሁሉም አልሳካላቸው ቢል «የኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ጃንሆይ፤ የአባተ ሣህለ ሥላሴ ገዳም ተሾሞልህ በገዳሙ ንብረት ዘጠኝ ደጃፍ ሱቅ ሦስት ፎቅ ቤት ሠሩበት» ብለው ጻፉብኝ:: ጎጆ እንኳን ያልሠራሁትን፤ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ምስካየ ኅዙናን ሳለሁ ያውቁኛል:: «ሰውየው እንኳ እንደዚህ ያለ ሥራ አይሠራም» ብለው ጉዳዩን ወደ አቡነ ባስልዮስ ያስተላልፉታል:: አቡነ ባስልዮስም አቶ ሰይፉን /በወቅቱ የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ ነበሩ/ አዝዘውት መጣ:: እርሱም ጉዳዩን ግራ ቀኝ ካየ በኋላ በእኔ ምንም ዓይነት ጥፋት ባለመገኘቱ የከሰሱኝን ሰዎች ከገዳሙ ጠራርጎ አስወጣቸው:: እኔም ጥቂት በገዳሙ ከተቀመጥኩኝ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተዛውሬ በግር ማዊነታቸው ፈቃድ በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ተሾምኩ::

*ሐመር- ለጵጵስና ታጭተው የተሾሙት የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም አስተዳዳሪ በነበሩ ጊዜ ነው ማለት ነው?*

ብፁዕ አባታችን- አዎ:: በዚያ ሳለሁ ቀድሞ ከየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል እንድመጣ ያደረጉኝ አባ ሐና ለአቡነ ባስልዮስ «ያ አባ ጽጌ የሚባል ሰው ተራ ሰው እንዳይመስሎት:: ከጳጳሳት ውድድር እንዲያስገቡት» እያሉ ይነግሯቸው ነበር:: ከዚያ ለጵጵስና ተመርጬ ተሾምኩና አቡነ ባስልዮስ እኔን ጋሞ ጎፋ መደቡኝ:: አቡነ ቴዎፍሎስ ግን «እርሱ ጐጃም መሄድ አለበት:: ጐጃም የሊቃውንት አገር ነው:: እሱ ነው መሄድ ያለበት፤ የተማረበት አገር ነው:: እርሱ ነው መሄድ ያለበት» ብለው ተከራከሩ:: ለጃንሆይም ነገሯቸው:: ጃንሆይ የተማረበት አገር ነውና ወደ ጐጃም ይሒድ አሉ:: ከዚያ ወደ ጎጃም ሔድኩ::

*ሐመር- ብፁዕ አባታችን መጀመሪያ ሲሾሙ አባ ሰላማ ነው የተባሉት፤ ማርቆስ ብለው ስምዎን የለወጠው ማን ነው?*

ብፁዕ አባታችን - የዚያን ጊዜ እዚህ ብንሾምም ወደ እስክንድርያ ሔደን የፓትርያርኩን ቡራኬ እንድናገኝ ይደረግ ነበር:: ታድያ በዚያ ዓይነት ወደ እስክንድርያ ሔደን ፓትርያርኩ «ይደልዎክ፤ ይገባሃል» ብለው ቡራኬ ከሰጡኝ በኋላ የተሾምኩበት አገሩ ማርቆስ ከሆነ ስምህም «አባ ማርቆስ የጐጃም ጳጳስ» ይሁን ብለው እንደገና ስም አወጡልኝ::

*ሐመር- ወደ ግብፅ በምን ነበር የተጓዙት?*

ብፁዕ አባታችን - በአውሮፕላን ነበር የሄድኩት:: የተለያዩ ቅዱሳት መካናትን አይቻለሁ::

*ሐመር-አብረዎት የተሾሙትን ብፁዓን ጳጳሳት ስም ቢነግሩን?*

ብፁዕ አባታችን- በተለያዩ ጊዜያት አቡነ ሉቃስ ፣አቡነ ሳዊሮስ እና እኔ ሦስታችን ነን የተሾምን::

*ሐመር- በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ልዩ ልዩ ሽልማቶችን እንዳገኙ ሰምተናል:: ለመሆኑ የተሸለሙትን አንድ በአንድ መዘርዘር ይችላሉ? ሽልማቶችስ የት ይገኛሉ?*

ብፁዕ አባታችን-ለቤተ ክርስቲያን የሰጠሁት ወርቅ ብዙ ነው:: ለደብረ ማርቆስ ጵጵስና የተሾሙኩበትን ልብሰ ተክህኖ ሰጥቻለሁ፤ ለተማርኩበት ለዲማ ጊዮርጊስም ልብሰ ተክህኖና አርዌ ብርት ገዝቼ ሰጥቻለሁ፤ ለእቲሳ ገዳም ደግሞ አርዌ ብርት ሰጥቻለሁ፤ ለሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አንድ የወርቅ አክሊል ሰጥቻለሁ::

*ሐመር - ኮርዶን ኒሻን ከጃንሆይ ተሸልመዋል ይባላል:: እውነት ነው?*

ብፁዕ አባታችን - እውነት ነው:: ሽልመውኛል ጃንሆይ::

*ሐመር - አሁን ኮርዶን ኒሻኑ አለ?*

ብፁዕ አባታችን - ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሰጥቻለሁ::

*ሐመር- ለሐዋርያዊ ጉዞ የተጓዙባቸውን አገሮች ቢነግሩን?*

ብፁዕ አባታችን - ወደ ግብፅ፣ ምዕራብ ጀርመን ፣አስትሪያና ኢየሩሳሌም ተጉዤአለሁ::

*ሐመር- ወደ እነዚህ አገራት ለምን ነበር የተጓዙት?*

ብፁዕ አባታችን- አብዛኛው ለስብሰባ ነው:: አስትሪያ በሄድኩ ጊዜ ንግግር እንዳደርግ ተጋበዝኩ:: በዚህ ጊዜ ለሁለት ቀን ያህል ስብሰባውን አቋርጬ የማደረገውን ንግግር አዘጋጀሁ፣ በጽሑፍ ያዘጋጀሁት ንግግር ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለተሰብሳቢዎች ተነቧል:: በዚህ ጊዜ ሞቅ ያለ ጭብጨባ መልሶ መላልሶ ተጨበጨበ:: ዋናው ስብሰባውን ያዘጋጁት ፓትርያርኩ «ለእርስዎ ሽልማት አዘጋጅተን ነበር፡ ነገር ግን እርስዎን ብቻ ስንሸልም ሌሎቹ የተሰበሰቡት ቅር ይላቸዋል:: አሁን እኛ መምጫዎንም መመለሻዎንም እንከፍላለን» አሉኝ:: እሺ አልኩና መጣሁ:: ወዲያው በመጣሁ በሳምንቱ «የመምጫዎንና የመመለሻዎን የአውሮፕላን ወጪ ከፍለናልና እንዲመጡ» የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ:: ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነገርኳቸው:: እሳቸውም «ባለተራ ነው የሚሄደው፤ እርስዎ አይሄዱም» አሉኝ:: «እሺ» ብዬ ቀረሁ:: ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ እንድመጣ ደብዳቤ ተጻፈ:: አሁንም ቀረሁ::

*ሐመር- በንጉሡ ዘመነ መንግሥት ብፁዓን ጳጳሳት በፓርላማ ጉባኤ ላይ ትሰበሰቡ ነበር ይባላል:: ለመሆኑ በወቅቱ በፓርላማው የእናንተ ሚና ምን ነበር?*

ብፁዕ አባታችን - ለቡራኬ ነበር፤ ጉባኤውን እግዚአብሔር ይባርክ ለማለት ያህል ነው:: ክርክር ውስጥ አንገባም::

*ሐመር- ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጥቂት ቢነግሩን?*

ብፁዕ አባታችን -ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጣም ትሑት፣የተማሩ፣ አስተዳደር የሚያውቁ፣ ደግ አባት ነበሩ ታድያ ምን ይሆናል ሰዎች ቀን ተውባቸው ስማቸውን አክፋፍተው በወታደሮች እንዲገደሉ አደረጓቸው:: /ለጥቂት ጊዜ ተከዙ/:: በእርሳቸው የቀኑ ሰዎች ቅዳሴ እንደ ውጪ አገር በሁለት ሦስት ካህናት ብቻ ይቀደስ ብለዋል እና ሌላ የውንጀላ ንግግር ሲያደርጉባቸው ነበር:: ሃይማኖታቸው ፍጹም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነበሩ:: /ዝምታ/:: መጥፎ የሚያስወሩባቸው ሰዎች እንዳሰቡት ሆነና የሁላችን መመኪያ የነበሩትን አባት ወታደሮቹ አሰሯቸው:: ቅዱስነታቸው ሊገደሉ ሲሉ በራእይ ያየሁት ነገር ነበር:: ጸሎት ሳደርስ ቆይቼ ሲነጋጋ ሸለብ አደረገኝ:: ከዚያ ከቅዱስነታቸው ጋር ቀደም ሳይታሰሩ እንደሚያደርጉት ተገናኝተን እንጫወት ጀመር:: በውይይታችን መካከል «እኔ እኮ በተክሊል ላገባ ነው» አሉኝ:: እኔም በንግግራቸው ደንግጬ «አይ እንዲህ ያለ አነጋገር በእርስዎ አንደበት መነገር የለበትም» አልኳቸው:: እርሳቸውም ሳቅ እያሉ «አንተ የዋህ» እያሉ ሦስት ጊዜ መላልሰው «በተክሊል ላገባ ነው» አሉኝ፤ እኔም በስጨት ብዬ «ፓትርያርክ ደግሞ ከመቼ ወዲህ ያገባል?» አልኳቸው:: ከዚያ በኋላ ብንን አልኩ:: ታድያ «አይ እኒህን ደግ አባት እነዚህ ወታደሮች ሊገድሏቸው ነው፤ በተክሊል ላገባ ነው ማለታቸው በሰማዕትነት ሊያልፉ ነው» ብዬ በተኛሁበት ምርር ብዬ አለቀስኩ:: ይህንን ባየሁ በሦስተኛው ቀን ገደሉአቸው የሚል ወሬ ተሰማ:: እወዳቸው ነበር አባቴን!! /ረጅም ትካዜ/::

*ሐመር- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንዲገደሉ ከፈረሙት መካከል የእርስዎም ፊርማ በጋዜጣ ላይ ወጥቷል? እንዴት ሊፈርሙ ቻሉ?*

ብፁዕ አባታችን-እኔ ዐውቄ አል ፈረምኩም:: መቼም ሌላ ፊርማ አስ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መስለው አስፈርመውኝ ይሆናል:: ለእርሳቸው ዐሥር ጊዜ ብሞትም እንኳ አልፈርምም፤ እወዳቸዋለሁ÷ ይወዱኛል፤ እንዲያውም እሳቸው ይሙቱ ብለው ይፈርሙ ብሎ ያነሣብኝ ሰው የለም:: ግን የሌላ ሰው ቃለ ጉባኤ አስመስለው አስፈርመውኝ ይሆናል:: እንዲያውም እርሳቸው ... /የግርምት ሳቅ ሳቁ/ ለእኔ ረዳቴ ወዳጄ ነበሩ:: ሕይወቴ አልነበሩም እንዴ?! መቶ ጊዜ ብሞት አላደርገውም::

ሐመር - ብፁዕ አባታችን በአሁኑ ሰዓት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ራቅ ብለው ነው የሚኖሩት:: ወደ ዚህ እየመጡ የሚጠይቁዎት ብፁዓን ጳጳሳት አሉ ወይ?

ብፁዕ አባታችን - አሁን ከተሾሙት ጋር አልተዋወቅንም:: ግን የደቡብ አፍሪካ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ለሰኔ ሚካኤል ጠይቀውኛል:: ከጥንታውያኑ አቡነ ማቴዎስ መጥተው ይጠይቁኛል:: እርሳቸውም ወዳጄ ናቸው:: /ይህንን ቃለ ምልልስ ስናደርግ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ በሕይወት ነበሩ/::

ሐመር - እንደ ሚታወቀው በአሁኑ ጊዜ የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ነዎት:: አሁን ገዳሚና ገዳማውያኑ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?

ብፁዕ አባታችን - የበላይ ጠባቂ ሆኜ በተለያዩ በዓላት ላይ በመሄድ ቡራኬ እሰጥ ነበር፤ አሁን እየደከመኝ ስለሆነ አልሄድም::

ሐመር-በአሁኑ ሰዓት በቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ይሳተፋሉ?

ብፁዕ አባታችን- እሳተፍ ነበር:: አሁን ግን በሽታው እየጎሰመኝ፤ መናገር፣ መሔድና በወግ ማድመጥ ስለ ተሳነኝ አልሔድም::

ሐመር-በአሁኑ ጊዜ ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ በአገራችን ላይ ተስፋፍቷል፤ ለዚህ ለወጣቱ ትውልድ የሚመክሩት ምንድን ነው?

ብፁዕ አባታችን-ወጣቱ መጠንቀቅ አለበት:: አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ነው የተፈቀደው፤ በፍትሐ ነገሥትም የተከለከለ ነው:: ሚስቱ የሞተችበት ቆራቢ ከሆነ ቆራቢዋን አግብቶ መኖር::ያም ካልሆነ ንጽሕናን ጠብቆ መኖር ያስፈልጋል::አለቁርባን የሚያገባ አንድ ክርስቲያን ስንኳ አይኑር፤ ካገቡም በቁርባን መጋባት አለባቸው:: በሞት የተለየችበት ወይም በሞት የተለየባት መንኩሶ መኖር ነው፤ ዕድሜውን /ዕድሜዋን/ በዚህ ማሳለፍ አለበት/አለባት:: በሕጉ ለመኖር እግዚአብሔር እንዲያጸናቸው እግዚአብሔርን መለመን ነው፤ በተረፈ መመጽወት÷ ለተቸገረ መርዳት ነው:: ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር ይረዳል::

ክህነት ለሚቀበሉ ወጣቶች ግእዝ ሳያውቁ ክህነት ሊቀበሉ አይገባም:: እኔ በአንድ ወቅት ግእዝ ለማያውቁ ክህነት አልሰጥም ብዬ ከአቡነ ባስልዮስ ዘንድ ተከስሼ ነበር:: ፓትርያርኩ ስልክ ደወሉና «በሕዝቡ የምትጫወትበት ለምንድን ነው» አሉኝ:: ምን ብዬ ነው የተጫወትኩባቸው ተማሩ ማለት ነው ወይ መጫወት፤ ሳይማር ሕዝቡ ይሾም ይሉ እንደሆን ደብዳቤ ይጻፉልኝ አልኳቸው፤ መልስ አልሰጡኝም÷ ዝም አሉኝ፤ ሁለት መቶ የሚሆኑ ግእዝ ካላወቃችሁ÷ በሚገባ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ካላወቃችሁ ክህነት አልሰጥም አልኳቸው፤ የሚያነበውን የማያውቅ እንዴት ካህን ይባላል?!

ሐመር - ብፁዕ አባታችን ከዚህ በፊት የሚኖሩት መንበረ ጵጵስናው ባለበት ነበር፤ አሁን ያሉት በመንደር ከግለሰብ ቤት ነው ?

ብፁዕ አባታችን-ያለሁት ካህን ቤት ነው፤ ባለቤቱም ቆራቢ ናት፤ እርሱም ቆራቢ ነው፤ የምኖረው ከእነርሱ ጋር ነው፤ ልጆቻቸውም ዲያቆናት ናቸው:: ኑሮ ጥሩ ነው፤ የወለዱት ልጅ እንኳን እንደ እነሱ አይረዳም፤ ጻድቃን ናቸው:: ልጆቻቸውም እንደ ባሕታውያን ናቸው፤ የልጅ ጠባይ አይታይባቸውም፤ ገሮች ናቸው:: ወንዶቹም ሴቶቹም ታዛዦች ናቸው:: እግዚአብሔር እነሱን ሰጥቶኝ ምንም ችግር የለብኝም::

ሐመር:- ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሩባት ዳዊት በእጅዎ ትገኛለች::

ብፁዕ አባታችን:- አይ ለሰው ሰጥቻለሁ በእጄ የለም:: በእጄ የሚገኙት የድሮ የሐዲሳት መምህሬ የሰጡኝ ፍትሐ ነገሥት፣ አርባዕቱ ወንጌላት፣ ሐዲሳትን በሙሉ የያዘ ነው:: ይኸውም አንተ ተጠቀምበት ወደፊት ግን ለዲማ ጊዮርጊስ እንድትሰጥልኝ ብለውኛል:: ወደ ፊት ዐይኔ እየደከመ ሲሄድ ለዲማ ጊዮርጊስ እንዲሰጥ አስቀምጬዋለሁ:: አሁን የየዕለቱን ወንጌለ ዮሐንስ አነበዋለሁ:: /አባታችን በሚያስገርም ክብካቤ የያዙትን ጥንታዊ የአርባዕቱ ወንጌል መጽሐፍ አስመጥተው አሳይተውናል/

ሐመር:- መጽሐፉ መሐል መሐሉ ተበላሽቷል፤ ምን ሆኖ ነው?

ብፁዕ አባታችን- በጣልያን ጊዜ ፍንጣሪ ያቃጠለው ነው፤ እኔ ያለሁበት ቦታ የበላይ ዘለቀ ምሽግ ስለ ነበረ ጣልያን አካባቢውን በቦንብ ይደበድብ ነበር፤ ያን ጊዜ ነው የተቃጠለው::

ሐመር -እግዚአብሔር ይስጥልን ብፁዕ አባታችን::

ብፁዕ አባታችን - ተባረኩ ልጆቼ:: አቡነ ዘበሰማያት::

ሐመር- አቶ ብርሃኑ ወዳጄ ፣ ብፁዕ አባታችን ከመቼ ጀምሮ ነው እርስዎ ዘንድ መኖር የጀመሩት?

አቶ ብርሃኑ--ብፁዕ አባታችንን የማውቃቸው ከ1955 ዓ.ም. ጀምሮ ነው:: የተገናኘነውም የተዋወቅነውም ጐጃም ክፍለ አገር ነው:: በተለይ አሁን አብረን መኖር የጀመርነው ከየካቲት 16 ቀን 1983 ዓ.ም. ጀምሮ ነው:: አብረን ለመኖር የቻልንበት ምክንያት ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አካባቢ ቤት ነበራቸው÷ ረዳትም ነበራቸው፤ ታመው መኝታ ቤት የላቸውም፤ የሚተኙት ወንበር ላይ ነው:: የሚቀመጡትም ጸሎትም የሚያደርሱት እዚያው ጠረጴዛ ላይ ነው:: ወድቀው አድረው የሚያነሣቸው ጠፍቶ ስልክ ተደውሎልኝ ስመጣ ቤታቸው እንደ ተቆለፈ ነበር:: በር ሰብረን ገባን:: ያን ጊዜ ወድቀው አገኘናቸው:: ከዚያ ወደ ሆስፒታል ወሰድናቸው:: መንግሥት ሆስፒታል ብዙ ወስጃቸዋለሁ፤ ለማስተኛትም ሆነ በቂ ሕክምና እንዲያገኙ ፈልጌ ነበር:: ነገር ግን ወቅቱ የጦርነት ዘመን ስለነበር ቦታ የለንም እያሉ ይመልሱኝ ነበር:: በመጨረሻ ንፋስ ስልክ አካባቢ ቅዱስ ገብርኤል ክሊኒክ የሚባል አለ፤ እዚያ ወሰድኳቸው:: አጠቃላይ ምርምራ አደረጉላቸው:: እዚህ እናስተኛቸውና ሻል ሲላቸው ወደ መንግሥት ሆስፒታል ብትወስዷቸው ጥሩ ነው አሉኝ:: ቦታ የለንም ነገ ይዘሃቸው ና ተባልኩ:: ከዚያ ወደ ቤታቸው ወስጄ እዚያው አደሩ:: በማግሥቱ አቶ ወልዴ የሚባሉ ወዳጅ ነበራቸው:: እርሳቸው እኔ የምታከምበት ሐኪም ቤት አለ÷ እዚያ እንውሰዳቸው አሉኝ:: የምርመራውን ውጤት ይዘን ሄድን:: ምርመራው ቀደም ብሎ ያለቀ ስለሆነ አልጋ ተሰጣቸውና ተኙ:: መድኃኒት ሲወስዱ ተሻላቸው፤ በጐ ከሆኑ በኋላ አቶ ሞገስ እኝህን ሰው ወደ ኪዳነ ምሕረት ብንልካቸው በቂ ተከባካቢ የላቸውም:: ችግር ላይ ይወድቃሉ:: አንተ ዘንድ ወይም እኔ ዘንድ ይሁኑ:: እኔም አያያዛቸውን አይቼ «ቀድሞ እኔ ዘንድ ልውሰዶት ብያቸው ነበር:: ነገር ግን የሚረዱአቸውን ሰዎች ትተው ወደዚያ መሄድ ቅር ስላላቸው ነው የተውኳቸው፤ አሁን ፈቃዳቸው ከሆነ ልወስዳቸው እችላለሁ:: ደስ ይለኛል::» አልኩ ሕይወታቸውን አያውቁም ነበር፤ በሁለታችን ፈቃድ እኔ ዘንድ አመጣኋቸው:: እነሆ አሁን ሰባት ዓመት ይሆናል÷ አብረን ነው የምንኖረው::

ሐመር-ከዚያ በፊት ትውውቃችሁ እንዴት ነበር?

አቶ ብርሃኑ-እኔ ከሸዋ ቅኔ ለመማር ወደ ጐጃም ሄድኩ፤ የቅዳሴ መምህር ነኝ፤ ቅዳሴ እያስተማርኩ እዚያው ደብረ ማርቆስ ቅኔ እየተማርኩ እኖር ነበር፤ እዚያ ቤተ ክርስቲያን በምስጠው አገልግሎት እርሳቸው እያስቀደሱ ነበር:: ተዋውቀን እዚያው ቁርስም





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ምሳም ይጋብዙኝ ነበር:: ከዚያ ቤተሰብነታችን ከቀን ወደ ቀን እያደገ ሄደ:: የወንድማቸው የልጅ ልጅ ታማ እያስጠመቁ ከርሳቸው ጋር ትኖር ነበር:: ተሻላት÷ እኔ እንዳገባት እርሳቸውም ሆኑ ቤተሰቡ ፈቅደው በሥርዓተ ተክሊል ተጋባን:: ስምንት ልጆች ወልደናል:: የተወሰኑት ውጭ ሃገር ናቸው፤ የተቀሩት እዚሁ ከአገር ውስጥ ይገኛሉ:: ከእኔ ጋር ትውውቃችን ከዕውቅና ወደ ሥጋ ዝምድና ሄደ::

*ሐመር:- ጠቅላይ ቤተ ክህነት ለብፁዕ ነታቸው የሚያደርገው ክብካቤና ክትትል አለ?*

አቶ ብርሃኑ:- ደሞዛቸውን እንደ ማንኛውም ሊቀ ጳጳስ በየወሩ ይሰጣል:: እኔ እየተቀበልኩ ለእርሳቸው በእጃቸው እሠጣለሁ፤ ለእሳቸው የሚያስፈልገውን ነገር አሰመልክቶ ለሠራተኛ፣ ለጥበቃ ምግብ ለሚያዘጋጅ ያው ከራሳቸው ገንዘብ ይከፍላል:: እንዲሁም በፈቃዳቸው እረዳቸዋለሁ ለሚሉ ገዳማትና ዘመዶቻቸው ይረዳሉ::

*ሐመር:- እየመጡ የሚጠይቋቸው አሉ?*

አቶ ብርሃኑ:- አንድ ጊዜ ቅዱስ ፓትርያርኩ መኪና ልከው አምጧቸው ብለው ነበር:: እኔ ዘንድ መኪና ስላለ እኔ ወስጃቸዋለሁ:: ቅዱስነታቸውም «እኔ ልመጣ ነበር፤ ሹፌሩ መንገዱን አላውቀውም ስላለኝ ነው የቀረሁት፤ እንኳን ይዘህልኝ መጣህ፤ ናፍቀውኝ ነበር፤» አሉኝ:: ከዚያ አገናኟቸው:: ከዚያን ወዲህ እጅ ነስቼ ልምጣ ሲሉ እየወሰድኳቸው እየተገናኙ ይመጣሉ::

*ሐመር:- አሁን ጤንነታቸው እንዴት ነው?*

አቶ ብርሃኑ:- ብፁዕ አባታችን ሕመም የለባቸውም፤ ያው ዕድሜ ያመጣባቸው ድካምና ጆሯቸው ድምፅ መስማት ካለመቻሉ በስተቀር ደኅና ናቸው:: በ24 ሰዓት አንድ ጊዜ ይመገባሉ:: ትንሽ ትንሽ÷ ሻይ በሰዓት እናቀምሳቸዋለን:: እንደ ተለመደው በ24 ሰዓት አንድ ጊዜ ከፍተኛ በዓላት ሲሆኑ እሑድ እንደ ቁርስ እናቀርብላቸዋለን፤ ከዚህ ውጪ የሚወስዱት የለም?

*ሐመር- ብፁዕ አባታችን ጉጃም ሳሉ ከሕዝቡ ጋር የነበራቸው ሕይወት ምን ይመስል ነበር?*

አቶ ብርሃኑ:- ጎጃም ሳሉ የድኻ ልጅ እያሰባሰቡ ይረዱ ነበር:: እቤታቸው በወር አራት ኩንታል ጤፍ ነበር:: አራት ኩንታል ጤፍ ተፈጭቶ በወር ነበር የሚያልቀው:: ዘመናዊ ትምህርት ለሚማሩም ሆነ ለቆሎ ተማሪዎች ቢያንስ 30 የሚሆኑ እቤታቸው ይመገቡ ነበር:: እኔም ለምግብ ጋብዘውኝ ሄጄ ነው የተዋወቅነው፤ እንደ እኔ ሁሉ እየተማረ የሚገባ ብዙ ነበር::

## ለብፁዕ አቡነ ማርቆስ ከተበረከቱ ቅኔዎች በጥቂቱ

### መውደስ ቅኔ

*ዓምደ ሃይማኖት ማርቆስ የዋሃ ልቡና*
*እንዘ መሠረታ ይከውን ለኢትዮጵያ ቤተ መቅደስ*
*አረፋቲሃ ካህናት ወመሳክዊሃ አልባበ*
*ቴዎፍሎስ ጠፈረ ዚአሃ አኮኑ ሐዲስ ወወረደ በውስቴታ*
*ዘግልባቤሁ እሳት ኃይለ ሥላሴ መንፈስ ቅዱስ*

### ለዓለም

*ሰበከሂ ወዜነወ እስከ አድማስ*
*ወንጌለ ማርቆስ ዘይጽሕፍ የማነእዴየ ጳውሎስ*
*ወማርቆስ ግዮን ክፍለ ጤግሮስ*
*የውኅዝ በበዕለቱ ሀሊበ መንፈስ ዘይትቀደስ*

መምህር ወልደ ቂርቆስ

አባታችን ያበረከቱት ቅኔ በብፁዕ አባታችን ለሃይማኖት ምሰሶ መሆናቸው አባታችን በምሶሶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጣራ መስለው የተቀኙት ቅኔ ነው::

የአንድ ቤት ህልውና የሚጸናው ምሰሶና ጣራ መሠረት ሲኖረው እንደሆነው ቤተ ክርስቲያን በጳጳሳት ምሰሶነትና ጣራትነት በካህናት መሠረትነት ጸንቶ መኖሯ የሚገልፅ ቅኔ ነው::

*አይንሐል ብነ እመካነ ዕድሜ*
*ሕንፃ ሃይማኖት ማርቆስ ለመንፈስ ቅዱስ ጽርሑ*
*ወይኑኅ ለነ ዓምደ ማቱሳላ ዕድሜሁ*
*ኤልያስ ወዕዝራ ይቁሙ ቅድሜሁ*
*እስመ አነ እስእሎ ለአምላከ ምሕረት ወሣህል አይርኃቅ እምኔሁ*

### ለዓለም

*ማርቆስሂ ለእመ ጸንሐ*
*ለሊቀ ጳጳሳት ደዴሁ*
*የዓርር ወይበልዕ ሊቀ ጵጵስና*
*ባዕመ ፍሬሁ*
*በኢትዮጵያ ገራህት*
*አምባነ አብቈለ ናሁ*
*ዓራሬ መንግሥት ኃይለ ሥላሴ*
*ለዘርዐ ባስልዮስ ዚአሁ*

ቅኔ የመልካም ስሜት መግለጫ ሆኖ የሚያገለግል ሥነ ጽሑፋዊ ሀብት ነው:: ባለ ቅኔው ለብፁዕ አባታችን ረጅም ዕድሜን የተመኙበት ቅኔ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ የሆነ የሃይማኖታችን ሕንፃ ማርቆስ አይፍረስብን፤ ዕድሜው እንደ ማቱሳላ ይርዘምልን በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል:: አክለውም ኤልያስና ዕዝራ በፊታቸው እንዲቆሙ ተማፅነዋል:: ኤልያስና ዕዝራ ሞተ ሥጋ ያላገኛቸው ነቢያት ናቸው:: ባለቅኔው እነሱ በፊትህ ይቁሙ ማለታቸው እነሱ እንዳልሞቱ አንተም አትሙት በአገልግሎት ጸንተህ ኑርልን ለማለት ፈልገው ነው::

*አ ማርቆስ ዘመልዕልተ ኵሉ*
*ሥልጣን ወኀይል ወስም ዘይሰመይ*
*ሲዖሜ ካህናት አንተ ወወሀቤ ሥልጣን ዐቢይ*
*እስመውስተ ልብከ ዘተኀንፀ*
*ይመልዕ መዝገበ ጥበብ ወንዋይ ኅሩይ*
*ወበኃይለ ጸሎት ዕንቈ ባሕርይ*
*እምኵሉ ታርኅቅ ጽልመተ ኀዘን ወብካይ*

### ለዓለም

*ለስብእሂ ነዳያን እለአልቦሙ ሲሳይ*
*ትሴሲ ተግባረከ በክረምት ወበሐጋይ*
*ዘበገራህተ ሕገ ተዘርዐ ዘርዐቃልከ ሠናይ*
*በዝናመ ጸሎት እስመ በቈለ ወበሰለ በፀሐይ*

እዚህ ላይ ባለቅኔው የብፁዕ አባታችንን ጸሎት ከዕንቁ ጋር መስለው ተቀኝተዋል:: ዕንቁ የሚያበራ ማዕድ ነው:: እርሳቸውም በጸሎታቸውን ምእመናን እንደሚረዱ «እምኵሉ ታርኅቅ ጽልመተ ኀዘን ወብካይ፤ ከሁሉ ዘንድ ችግርና መከራ ታርቃለህ» በማለት ባለቅኔው ተቀኝተዋል:: ብፁዕ አባታችን በተለይም ጎጃም ክፍለ አገር በነበሩ ጊዜ የሙት ልጆችን ሰብስበው ያስተምሩ የተቸገሩትን ይረዱ ስለነበር ባለቅኔ ቅን አሳቢነታቸውን ለመግለጽ «ለሰብእሂ ነዳያን እለአልቦሙ ሲሳይ ተሴሲ» የሚበሉት የሚቀምሱትን ያጡትን በክረምትም በበጋም ትመገባለህ፤ መልካም የቃልህ ትምህርትና ልግሥናህ ተዘራ:: አንድ ዘር ሲዘራ ብዙ ቦታ እንደሚያካልል የብፁዕነታቸው ቅን አሳቢነታቸው መልካም ሥራቸው የተገለጠ መሆኑን ለመግለጽ ተፈልጎ የቀረበ ቅኔ ነው::

በመጨረሻም በዚህ ዓይነት በሁለት እትሞች ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ ጋር ቆይታ እንድናደርግ አባታችን ወደ ሚገኙበት ቦታ በመውሰድ ያስተዋወቁንንና ከብፁዕነታቸው ጋር ከጉጃም ጀምሮ ትውውቅ እንዳላቸው የነገሩንን፤ እንዲሁም ቤት በደረስን ጊዜ በአብርሃማዊው ሥርዓት በአክብሮት ተቀብለው ያስተናገዱንን የአቶ ብርሃኑን ቤተ ሰቦች ከልብ እናመሰግናለን:: እግዚአብሔር የድካማቸውን ይስጥልን:: አሜን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዝክረ ቴዎፍሎስ፡ጴጥሮስ ወሚካኤል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአገራችን ሁለንተናዊ ማንነት ላይ ግንባር ቀደም ተዋናይት ናት ሲባል ሁል ጊዜ እንደሚባለው በሥነ ጽሑፍ ወይም በሥነ ሕንፃው፣ በሥነ ሥዕሉ ወይም በሥነ ትምህርቱ ብቻ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ማንነት ላይ የነበራትና ያላት አስተወፅዖ ፍጹም ስለሆነ ለአገሪቱ የመጣን ደግ ነገር የመካፈሏን ያህል ጉዳቷንም ተቀብላለች። ኀዘኗን አዝናለች፣ሕማሟን ታማለች። የአገሪቷም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችን ያለፈ ታሪክ የሚያስረዳን ይኸንኑ ነው።

ጥንት የሚባለው ታሪካችን እንዳለ ሆኖ ባለፉት መቶ ዓመታት የተመዘገበውን ታሪክ ብንመለከት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአገራችን በተከሰተው ውጣ ውረድ ቀደምት ተጠቂ እንደ ሆነች እንረዳለን። ይህ ደግሞ ለአገሪቱ ህልውና የቤተ ክርስቲያን ሚና ወሳኝ እንደ ሆነ ያረጋግጣል።

በዚህ ጽሑፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ወልዳ ለወግ ለመዓረግ ካበቃቻቸው በኋላ የሰጠቻቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ደፋ ቀና ሲሉ በገፉዐያን የተገደሉትን ሦስት አባቶች ዜና ሕይወትና የሰማዕትነት ዕረፍት እናዘክራለን።



1. ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ

## 1.1 ዜና ሕይወት

- ቀድሞ ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ይባሉ ነበር፤
- ከአባታቸው ከአቶ ጀንበሬ ውቤ ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘሪቱ አደላሁ በቀድሞው የጐጃም ጠቅላይ ግዛት፣ በደብረ ማርቆስ አውራጃ፣ በማቻከል ወረዳ፣ ደብረ ገነት ኤልያስ በሚ ባለው ታላቅ ደብር ሚያዝያ 16 ቀን 1902 ዓ.ም. ተወለዱ።
- በደብረ ኤልያስ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ /የንባብና የዜማ/ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ተምረው ከግብፃዊው አቡነ ማቴዎስ መዓረገ ዲቁናን ተቀበሉ።
- በዚያው ደብር ከመምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመረቁ።
- በርእሰ አድባራት ደብረ ጽዮን አዲስ ዓለም ማርያም ከንቡረ እድ ሐዲስ ተክሌ /በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ/ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ በሚገባ አሔዱ።
- በ1930 ዓ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖስ በመውረድ መዓረገ ምንኩስናን ተቀበሉ፤ ብዙም ሳይቆዩ ከአቡነ አብርሃም መዓረገ ቅስናን ተቀበሉ።
- በ1935 ዓ.ም. በወቅቱ መካነ ሥላሴ ገዳም ይባል በነበረው በዛሬው መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መምህር ሆነው ተሾሙ።
- ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ.ም በካይሮ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሳብ አንብሮተ እድ ከሌሎች አራት አባቶች ጋር «አባ ቴዎፍሎስ ጳጳስ ዘሐረር» ተብለው ተሾሙ።
- ከ1943-1963 ዓ.ም አገረ ስብከታቸውን ከማስተዳደር ጋር የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና በኋላም ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገለገሉ።
- በ1963 ዓ.ም. ሁለተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ።
- እስከ መጋቢት 1968 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያንን በቅንነትና በትጋት አገለገሉ።
- መጋቢት 3 ቀን 1968 ዓ.ም. ዘውዳዊውን መንግሥት በኃይል አውርዶ ሥልጣን በያዘው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ መንግሥት ለእስር ተዳረጉ።
- ከ28 ወራት እስርና እንግልት በኋላ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም. በሰሜን አዲስ አበባ፣በወረዳ 12 በቀበሌ 22 በሚገኘው የራስ ዓሥራተ ካሣ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቤት በሚያስቅቅ ሁኔታ በገመድ ታንቀው ተገደሉ፡፡

- አስከሬናቸውም የእርሳቸውን ዓይነት የሞት ጽዋ ከተቀበሉ ሰዎች ጋር በዚያው ቅጽር ግቢ ተቀብሮ ከቆየ በኋላ በወቅቱ አሚሚታቸውንና የተቀበሩበትን በተመለከተው የደርግ ባለሥልጣን ጥቆማ ዐጽማቸው ወጥቶ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም. በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በክብር ዐረፈ፡፡
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የመከራ ጽዋዕ ተቀብለው ያለፉትን ቅዱስ አባት በሰማዕታት መዝገብ ውስጥ እንዲሰፍር÷ በክብራቸውም «ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ» እንዲባሉ ወስኗል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ቅዱስነታቸው በደርግ ወታደሮች ከተያዙበት ቀን ጀምሮ በእስር ቤት ያሳለፉትን የመከራና የእንግልት ሕይወት፣ በመጨረሻም በሚያስቅቅ ሁኔታ እንዴት እንደ ተገደሉ እናቀርባለን፡፡ ለምናቀርበው ሐተታ ምንጫችን የቅዱስነታቸው የሥጋ ወንድም የአቶ አበራ ጀንበሬ የዐይን ምስክርነት ነው፡፡ አቶ አበራ ጀንበሬ በወቅቱ እርሳቸውም ለእስር ተዳርገው የቅዱስነታቸውን የእስር ቤት ሕይወት ከመጀመሪያው ጀምሮ ተከታትለው በመዘገብ <u>የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት</u> ከ1966–1974 ዓ.ም. በሚል ርእስ በ1995 ዓ.ም. አንድ መጽሐፍ አሳትመዋል፡፡

✪ ✪ ✪

«...በታላቁ ቤተ መንግሥት ታስረው የነበሩ የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣኖች ንጹሕ አየር ለማግኘት፣ በፀሐይ አካላቸውን ለማሞቅ፣ የተሳሰሩ እግሮቻቸውን ለማፍታታት በዙፋን አዳራሽ አጠገብ በሚገኝ በሸቦ በታጠረ ጠባብ ክልል ውስጥ ይንከላወሳሉ፡፡ ቀኑ መጋቢት 3 ቀን 1968 ዓ.ም. ከእኩለ ቀን በኋላ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ታላቁ መንፈሳዊ አባት ሁለት እጆቻቸውን በአንድ ላይ በሰንሰለት ታስረው እየተገፈተሩ ያለ ጫማ በባዶ እግራቸው ሲመጡ የተመለከቱት እነዚያ እስረኞች ባሉበት ክው ብለው ቀሩ፡፡ በዚህ ወቅት ነበር አንዱ እስረኛ ልቡ ተነክቶ «አዲዮስ የኢትዮጵያ ሰብአዊነትና መንፈሳዊነት!!» ያለው፡፡

«... የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብረ ገብነትና መንፈሳዊነት በእነዚህ ጋጠ ወጦች አይለካም» አለ ሌላው በድርጊቱ መብገኑን ሁኔታው እየነገረበት፡፡ «ካህኑን እንደ ፖለቲከኛ፣ መንፈሳዊ አባቱን እንደ ወንጀለኛ የሚመለከት ወታደራዊ ቡድን በዚህች ቅድስት አገር መነሣቱ ያሳዝናል፡፡ መንፈሳዊ አባት በግፍ ሲንገላታ ከማየት መሞት ይመ ረጣል» አለ ሌላው በመበሳጨት፡፡

«የአደፈ ሽሮአማ ቀሚስ እንደ ለበሱ ከቀኝም፣ከግራም፣ ከኋላም ሳንጃ የተሰካበት ጠመንጃ ተደግኖባቸው ወደ ዚያች የፖለቲካ እስረኞች መቀየጃ ቅጥር ግቢ ሲገቡ መንፈሳዊው አባት "የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" በማለት ግፍ ለሚፈጽሙባቸው የሚጸልዩ እንጂ የተበሳጩና የተሸበሩ አይመስሉም ነበር፡፡

«እስረኛው ከድንጋጤው ገና ሳይላቀቅ፣ ምን እንደሚልና እንደ ሚያደርግ አሰላስሎ ሳይጨርስ፣ከቆመበት ሳይላወስ ነበር ከአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ አስገብተው የቆለፉባቸውና እግራቸውን በእግረ ሙቅ እጃቸውን በሰንሰለት ጠፍረው ከአልጋ ጋር ያሰሯቸው፡፡ 'ይህን አዚመኛ ቄስ ተጠንቀቃችሁ ጠብቁ' በማለት ለወታደሮቹ ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶ የዘቡ አዛዥ ከአጥሩ ወጥቶ ሄደ፡፡

«መንፈሳዊው አባት የታሰሩበት ክፍል በማግሥቱ የአሳሪዎች ምልልስ ታየባት፡፡ ሹማምንት በመፈራረቅ ጎበኟት፡፡ ፈንጠር፣ፈንጠር፣ ቀበጥበጥ ብለው እንዳልገቡ ተስፋ ቆርጠው ሲወጡ ተስተዋሉ፡፡ ይህ ሁሉ ምልልስ፣ ይህ ሁሉ ጋጋታ የተከሰተው ከአንድ ክፍል ውስጥ እግር እጃቸው ከአልጋ እግር ጋር የታሰረው መንፈሳዊ አባት ምግብ አልበላም ብለው በመወሰናቸው ነበር፡፡ ሻለቃ ዳንኤል አስፋውና ሌሎች የእስር ቤቱ ኃላፊዎች የሚመጣላቸውን ምግብ እንዲመገቡ ለማድረግ ቢሞክሩም ጽኑዑ አባት አልተበገሩም፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ምግብ አልበላም በማለት ማስቸገራቸውን በመግለጽ ሻለቃ ዳንኤል ለደርግ የጸጥታ ጥበቃ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ባቀረበው ማስታወሻ ግርጌ ላይ 'ምግብ እንዲገባላቸው አድርጉ እንጂ ቢበሉ ባይበሉ የራሳቸው ጉዳይ ነው' ሲል ሻለቃ ተካ ቱሉ ምልክት ያደረገው፡፡

«እኒያ አባት በዚያች መስኮት በሌላት ጠባብ ክፍል ምግብ ብቻ ሳይሆን ንጹሕ አየርም ሳያገኙ ሰባት ቀን ጦማቸውን ውለው አደሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ነበር ሌሎች እስረኞች አግባብተው ምግብ እንዲበሉ እንዲያደርጉ ለአንድ ቁጥር ክፍል ኃላፊ ትእዛዝ በመስጠት አሳሪዎቻቸው ከሰው እንዲቀላቀሉ ያደረጉት፡፡ እግር እጃቸው ከብረት ተላቆ ከመንፈስ ልጆቻቸው ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ለጸሎት እንዲያመቻቸውም ወደ ዙፋን አዳራሽ በመግቢያው ዋና በር ደረጃ ሥር የሚገኘው ጉሮኖ ለእርሳቸው መኝታ ተለቀቀላቸው፡፡ በአንድ ቁጥር ክፍል ውስጥ የሚገኙት እስረኞች በተለይም ብርጋዴር ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ዐቅማቸው በፈቀደ መጠን የሚጉድላቸውን አሟልተውና አንጥፈው ተቀበሏቸው፡፡ ምግብ ሲያቀርቡላቸው ግን 'እግዚአብሔር ይስጣችሁ አልበላም' የሚል ሆነ መልሳቸው፡፡ የደረቀ ጉሮሮአቸውን በውኃ እየተጉመጠመጡ ብቻ ምግብ ሳይበሉ፣ውኃ ሳይጠጡ መጾሙን ቀጠሉ፡፡ ጠንካራነታቸውን አስመሰከሩ፡ የመንፈስ ብቻ ሳይሆን አካላዊ ምግባቸውም ጾም ጸሎት ሆነ፡፡ የዕለት ተዕለት ሁኔታቸውም ለሌሎች እስረኞች መንፈሳዊ ጽናትን ሰጠ፡፡»

«ይሁንና ፋሲካ በዋለ ማግሥት ከእስረኞች መካከል በዕድሜ የገፉት እንደነ ደጃዝማች ሐረጎት ዓባይ ያሉት አጥብቀውና አስጨንቀው ስለ ለመኗቸው እህል ሊበሉ መቻላቸውን አብረዋቸው ታስረው ከነበሩት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡»

የቅዱስነታቸውን የእስር ቤት የሰቆቃ ቆይታ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የተረከው የአቶ አበራ ጀንበሬ <u>የእስር ቤቱ አበሳ በታላቁ ቤተ መንግሥት</u> 1966–74 ዓ.ም. የተሰኘው መጽሐፍ በመጨረሻ እንዴት ጽውዐ ሰማዕትነትን እንደ ተቀበሉ በሚከተለው መልኩ ያስረዳል፡፡

«ከሐምሌ 3–10 ቀን 1971 ዓ.ም. ከታላቁ ቤተ መንግሥት እስር ቤት ክፍል 1፣2 እና 11 እስረኞች በየሦስተኛው ቀን ሁለትም ሦስትም ኾነው እየተጠሩ ተወስደው የግፍ ግድያ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም ከክፍል 1 የተጠሩትና የተወሰዱት ከደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያምና ከብርጋዴር ጄኔራል ሳሙኤል በየነ ጋር በዕለተ ቅዳሜ ሐምሌ 7 ቀን 1971 ዓ.ም. ከቀኑ በአምስት ሰዓት አካባቢ ነበር፡፡ ቅዱስነታቸው የሰማዕትነት ጽዋን እንዲቀበሉ የተወሰዱት በሰሜን አዲስ አበባ ወረዳ 12 ቀበሌ 22 ወደ ሚገኘው የራስ ዓሥራተ ካሣ ሕንፃ ቤት ነበር፡፡ በዚህ ዘመናዊ ሕንፃ ቤት ውስጥ የተገደሉት እስረኞች ቁጥር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ጨምሮ 33 ሲሆን አንገታቸውን በገመድ ታንቀው እንዴት እንደ ተገደሉ በዐይን ምስክር የተነገረው ቀጥሎ ካለው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

✪ ✪ ✪

ሚያዝያ 20 ቀን 1984 ዓ.ም. የቅዱስነታቸውን መቃብር በተጠቀሰው የራስ ዓሥራተ ካሣ ግቢ ይፈልግ ለነበረው ኮሚቴ ገለጻውን ያደረገው በደርግ መንግሥት የደኅንነት ሹም የነበረ ኮሎኔል ነው፡፡ የኮሎኔሉን ገለጻ በትክክል መረዳት እንዲቻል የተገደ ለብትን ቤት ውስጣዊ ክፍል እንዲወክል ተደርጐ የተሣለውን ባለ 8 ቁጥር ሥዕል ከገለጻው ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሀ/ የሚገደሉት እስረኞች ከሕንፃው ውጪ ከደረጃው በታች ቁጥር 1 አካባቢ ተሰልፈው እንዲቆዩ ይደ ረጋል፡፡ ሕንፃው ከፍ ብሎ የተሠራ በመሆኑ ቁጥር 1 አካባቢ ሆኖ ወደ ውስጥ ማየት አይቻልም፡፡ ወደ ሕንፃው መግባት የሚቻለው በረጅም ደረጃ ወጥቶ ሲሆን እስረኞቹ ተሰ ልፈው ሞታቸውን የሚጠብቁት ከቤቱ ደረጃ በታች ነበር፡፡

ለ/ አንድ ኮማንዶ ቁጥር 2 አካባቢ ሆኖ የሚገደሉትን እስረኞች አንድ በአንድ እየጠራ ወደ ሕንፃው ውስጥ ያስገባል፡፡

ሐ/የተጠራው እስረኛ የሞት ጉዳና የሆነውን ቀስት ተከትሎ በመ ሄድ ቁጥር 3 አካባቢ ሲደርስ የኮማንዶዎቹ አዛዥ ቁጥር 4 አካባቢ ከክፍሉ በር ላይ ቆሞ እስረኛውን «ወደዚህ ና» ይለዋል፡፡

መ/ እስረኛው ወደ ቀኝ በመዞር አሁንም ቀስቱን ተከትሎ « ወደዚህ ና» ወደ አለው የኮማንዶ አዛዥ በመሄድ ላይ እንዳለ ቁጥር 5 አካባቢ ሲደርስ ቁጥር 6 አካባቢ በጨለማ ኮሪ ዶር ውስጥ ተደብቀው ከሚጠባበቁት ገዳይ ኮማንዶዎች መካከል አንዱ እስረኛውን ሳያስበው በድንገት በሲባጐ ያንቀዋል፡፡ ኮማ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ንዶው በሁለቱ እጆቹ ላይ ጠምጥሞ አጥብቆ የያዘውን ሲባጐ በእስረኛው አንገት ላይ ካጠለቀ በኋላ ሲባጐው እንዲሸረብ ከእግሩ ሽብርክ በማለት በራሱ ዙሪያ ይሽከረከርና ቀና ብሎ በአንገቱ ላይ ሲባጐ ያገባበትን እስረኛ ነፍሱ እስክ ትወጣ ድረስ በጀርባው ላይ ይሽከ መዋል:: ነፍሱ በዚህ ሁኔታ ከወጣች በኋላ ከመሬት ላይ ይጥለውና የእስረ ኛውን ሬሳ ጐትቶ በመውሰድ ቁጥር 7 ውስጥ ያስቀምጠዋል::

ሠ/ከውስጥ ምልክት ሲያገኝ ቁጥር 2 አካባቢ ያለው ኮማንዶ የሚቀጥ ለውን እስረኛ ስም ይጠራል:: ከእርሱ በፊት ተጠርቶ የገባው እስረኛ ዕጣ ፈንታ ምን እንደ ሆነ የማያውቀው ተረኛ እስረኛ ተጠርቶ ይገባል፤ ቁጥር 5 አካባቢ ሲደርስ በተረኛው ገዳይ ኮማንዶ በሲባጐ ታንቆ ይገደልና ሬሳው ወደ ቁጥር 7 ይወሰዳል:: ቁጥር 7 በእስረኞች ሬሳ ከሞላ በኋላ ሬሳ የማከማቸቱ ተግባር ወደ ቁጥር 8 ተዛወረ:: በዚህ ሁኔታ እስረኞቹ በሙሉ ተገደሉ:: ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም በገመድ ታንቀው ጽውዐ ሰማዕትነትን የተጐነጩት በዚህ ዘግ ናኝ ሁኔታ ነው:: ይህ ዘግናኝ ሁኔታ መንፈሳቸውን የነካው ጸሐፊ እንዲህ ሲሉ በግጥም ገል ጸውታል:–

*«አንች የሐምሌ ሳምንት ሥቃይ የታየብሽ*
*የሕዝብ ደም እንደ ጐርፍ በግፍ ፈሰሰብሽ*
*እንደ እስስት በገመድ አቡን ታነቁብሽ»*

ረ/ እስረኞቹ በሙሉ ከተገደሉ በኋላ ሬሳቸው በሁለቱ ክፍሎች ውስጥ በሸራ ተሸፍኖ ዋለ:: ግድያው የተጀ መረው ጧት አካባቢ ነበር:: ግድያው ከበላይ አካል በታዘዘው መሠረት ስለ መፈጸሙ ሪፖርት ቀረበ:: ባለ ሥልጣኖች መጥ ተው ዐይተው ከአረጋገጡ በኋላ የእስ ረኞቹ ሬሳ እንዲቀበር ታዘዘ:: ቀብሩ የተፈጸመው በዚያው ዕለት ከምሽቱ 3:00–4:00 ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር:: በዚሁ ወቅት የእስረኞቹ ትርፍ ልብሶች ተሰብ ስበው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከተጨመሩ በኋላ ኖራ ተነስንሶባቸው ተቀበሩ::


የእስረኞች ሬሳ የተቀበሩባቸው ጉድጓ ዶች በቁጥር 10 እና 11 አካባቢ ግንቡን አስጠግቶ በሰሜን ወደ ደቡብ በረጅሙ የተቆፈሩት ግድያው ከመፈጸሙ ከጥቂት ቀናት በፊት እንደ ነበር ቦታውን ጠቁሞ ካሳየ የደኅንነት ክፍል ወታደር ለመረዳት ተችሏል:: የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አስከሬን ተጥሎ የተገኘው በቁጥር 11 በተመ ለከተው ጉድጓድ ከተቀበረው ከዶ/ር ኃይሌ ፊዳ ጋር ነበር::»

ዝክረ ቴዎፍሎስ ሰማዕት በሚል ርእስ ሐምሌ 4 ቀን 1989 ዓ.ም በወጣው መጽሔት እንደ ተገለጠው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አስከሬን ከራስ ዓሥራተ ካሣ ግቢ ከተጣለበት ተቆፍሮ ወጥቶ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዐርፎ ከቆየ በኋላ ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ.ም. በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዐውደ ምሕረት ጸሎተ ፍትሐት ተደርጐለት ሲያበቃ ያን ጊዜ ዓቃቤ መንበር የነበሩት ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ በቅዱስ ሲኖዶስ ስም የሚከተለውን መልእክት አስተላለፉ::

«ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከዛሬ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰማዕት ተብለው እንዲጠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል::»

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከላይ በተገለጠው ሁኔታ በሰማዕትነት እስካለፉበት ጊዜ ድረስ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያበረከቱት አስተዋፅዖ ሲዘከር ይኖር ዘንድ በአዲስ አበባ አገረ ስብከት በሚገኘው መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብር ኤል ቤተ ክርስቲያን ቤተ መዘክር ተቋቁሞላቸ ዋል:: ሐውልትም ታንፆ ላቸዋል:: የቅዱስ ነታቸው በረከት ይደርብን:: በሚቀጥለው እትማችን ደግሞ የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊን ዜና ሕይወትና የሰማዕትነት ዕረ ፍት ይዘን እንቀርባለን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር




# ሰሙነ ሕማማት...

ከገጽ ፲፱ የዞረ

1ኛ. ቀዳም ስዑር ይባላል፤ ይህ በዚህ ዕለት በመጾማችን /ጾመ አክፍሎት/ ያመለክታል::

2ኛ. ዐቢይ ሰንበት ይባላል፣ ሰንበት ዕረፍት ማለት ስለሆነ ይህ ቀን ጌታ ሁሉንም ሥራ ፈጽሞ በመቃብር ዐርፎበታልና::

3ኛ. ቅዱስ ቅዳሜ ይሉታል፤ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን በመቃብር ያኑት በመዘጋጀት ቀን /በመከራው ቀን - ዓርብ ማታ/ ነበርና:: «ሰንበትም ሊጀምር ነበር ቅዳሜም ከገባ በኋላ እንደ ትእዛዙ ሰንበት ስለሆነ ዐረፈ» ተብሎ እንደ ተጻፈ:: ሉቃ.23፥55::

በዚህ ዕለት በአዳም ስሕተት ምክንያት የተዘጋጀ የገነት ደጃፍ በጌታችን ቤዛነት ተከፍቷል:: ጥንተ ርስታችን ገነት ተመለሰችልን:: አባታችን አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀልን «ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሃደ፤» እንዲል በመስቀሉ ሰላምን እንደ ሰጠን የትንሣኤውን ብርሃን እንደ ገለጠልን በማሰብ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከቤት ወደ ቤት እየዞሩ ቄጤማ ለምእመናን ይሰጣሉ:: ምእመናንንም ለቤተ ክርስቲያን የሚውል ገጸ በረከት ያቀርባሉ:: ከትንሣኤው በኋላ ግብረ ሰላም የተባለ ግብር ካህናቱ ያገባሉ:: ካህናቱና ዲያቆናቱ ቄጤማ ማደላቸው ከዘመነ ኖኅ ሲያያዝ የመጣ የምሥራች መገለጫ ነው:: በኖኅ ዘመን ከኅ የተላከች ርግብ የጥፋት ውኃ እንደ ጐደለ ለማብሠር በአፍዋ የሰላም ምልክት ዕፀ ዘይት /የወይራ ቅጠል/ ይዛ መጥታለች:: ዘፍ.8÷11::

ሐዋርያት ጌታችን ከተያዘ ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ድርስ እህል አልበሉም:: በዚህ መሠረት በቤተ ክርስቲናችን ከዓርብ ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ድረስ እህል አይበላም:: ይህ ለሚቻለው ሲሆን ለማይቻለው ግን ከቅ ዳሜ ጀምሮ እስከ ትንሣኤው ድረስ ሊቆይ ይችላል:: ይህም አክፍሎት ተብሎ ይጠ ራል:: ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ ሙሀ ራው የሚወሰድበት ጊዜ ያመጣል:: «መሸራው በሚወሰድበት ዕለት ያን ጊዜ ይጾማሉ» /ማቴ.9÷15/ ብሎ እንዳስተማረ ሙሽራው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላት ተወስዶ በመስቀል ተሰቅሎ ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ በመቃብር ስለ ዋለ የወልደ እግዚአብሔርን ሞት የምና ስብበትና አበው ይናፍቁት የነበረውን ብር ሃነ ትንሣኤውን የምንናፍቅበት ዕለት ነው::

የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ትዝ ስላላቸው ደቀ መዛሙርቱ እንዳይሰርቁት ብለው መቃብሩን በጣባቂዎቻቸው/ /ጭፍሮቻቸው /አስጠበቁት:: ማቴ.27፥62-66 ይኸውም ጌታ በሥልጣኑ እንደሚነሣ ስለ አላመኑ ነው:: ጌታ ግን ጠባቂዎቻቸው እንደ ሞቱ ያህል አድርጐ እርሱ ተነሣ ማቴ.28፥3:: እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሰን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

አቡጊዳ የግእዝ ቋንቋ ትምህርት

/ዲ. ደሳለኝ ቀለብ/

ባለፈው ዝግጅታችን ግሶች በተግባር ሂደታቸው ለሁለት እንደሚከፈሉ፣ የሚሻገሩና የማይሻገሩ ተብለውም እንደሚጠሩ ተመልክተናል:: አያይዘንም ተሻጋሪ /ገቢር/ ግሶች ፊደልን በመለወጥ ባለመለወጥ፣በተጸውዖ ስም ላይ የገቢር /ተሻጋሪ/ ግሶችን ጠባይ፣ባለቤት ተውላጠ ስም ወደ ተሳቢ ተውላጠ ስም እንደሚለወጡ፣እንዲሁም ለተሳቢም ለተገብሮም የሚያገለግሉ ቃላትን ደንቦች ዘርዝረናል:: በዚህ እትማችን ደግሞ ስለ ቅጽልና የቅጽል ዓይነቶች ይዘንላችሁ ቀርበናል:: መልካም ትምህርት::

## ቅጽል (Adjectives)

**ቅጽል፡-** ማለት በስም ላይ እየተጨመረ የስምን ኩነት፣ አካል፣ መልክእ፣ ቅርጽ፣ ቅርበት፣ ርቀት፣ ዓይነት፣ መጠን ወይም ማንነት የሚገልጥ የስም አጐልማሽ /ገላጭ/ ነው::

ምሳሌ፡-

ሠናይ ወልድ - ቆንጆ ልጅ - A handsome boy
ሠናይ ወለት - ቆንጆ ሴት ልጅ - A beautiful girl
ንዑስ ወልድ - ትንሽ ልጅ – A small boy
ዐቢይ ወልድ - ትልቅ ልጅ - A great boy
ሠናይ ወልድ - ጥሩ ልጅ - A good son
ዐቢይ ዓሣ - ትልቅ ዓሣ - A big fish
ዝንቱ ወልድ - ይህ ልጅ- This boy (son)
ዝንቱ ብእሲ - ይህ ሰው - This man
ዛቲ ብእሲት - ይቺ ሴትዮ -This woman
ውእቶን አዕዋፍ - እነዚያ ወፎች - Those birds
ሐፂር ወልድ - አጭር ልጅ - A short son (boy)
ነዊኅ ወልድ - ረዥም ልጅ - A tall boy (son)
አብድ - ሰነፍ - Lazy /passive/
ሥሉጥ - ንቁ - active

❖ የተሰመረባቸው ቅጽሎች ሲሆኑ ያልተሰመረባቸው ደግሞ ስሞችን ይገልጻሉ ወይም ያጎላምሳሉ::

## የቅጽል ዓይነቶች /Kinds of Adjectives/

1. **ገላጭ ቅጽል** /Descriptive adjective/ :- ይህ የቅጽል ዓይነት የአንድን አካል /ስም/ ግብረ ኩነት/Quality/ የሚገልጽ ነው::

ቀይሕ ወልድ - ቀይ ልጅ
ጸሊም ወልድ - ጥቁር ልጅ
ጸዓዳ መልበስ - ነጭ ልብስ

**ገላጭ ቅጽል እንደሚከተለው ይከፋፈላል**

**ሀ. የተጸውኦ ስማዊ ቅጽል /Proper adjective/**

ኢትዮጵያዊ ወልድ - An Ethiopian son /boy ኢትዮጵያዊ (የኢትዮጵያ) ልጅ
ኢትዮጵያውያን ተማሃርያን - Ethiopian students- የኢትዮጵያ ተማሪዎች
ኢትዮጵያዊ ተማሃሪ - An Ethiopian student - የኢትዮጵያ (ኢትዮጵያዊ) ተማሪ
ዐምሐራይ ልሳን - Amharic language- አማርኛ ቋንቋ
ዐምሐራዊ ልሳን - Amharic language- አማርኛ ቋንቋ
ኦሮማይ ልሳን - Oromic language - ኦሮምኛ ቋንቋ

**ለ. ስም እንደ ቅጽል**

- ዘተቅዋም ወለት - የተቋም ተማሪ - a college girl
- መምህር ዘቤተ ትምህርት - የትምህርት ቤት መምህር – a school teacher

2. **የመጠን / Quantity /፣ የከፍታ /Degree/፣የቁጥር /Numeral/ ቅጽሎች :–**

ሀ. የመጠንና የከፍታ
ሕቀ፣ ሕዳጥ፣ ንስቲት፣ - some - ትንሽ
ብዙኀ፣ ፍድፉድ - Several, much, a lot, many /ብዙ /ለመጠን፣ ለቁጥር/

ለ. **የአኃዝ ቅጽል (Cardinals, Numbers, Numerals)**

## ሮማዊ ቁጥር

| | | |
|---|---|---|
| ፩. አሐዱ | 1. አንድ | I |
| ፪. ክልዔቱ | 2. ሁለት | II |
| ፫. ሠለስቱ | 3. ሦስት | III |
| ፬. አርባዕቱ | 4. አራት | IV |
| ፭. ኃምስቱ | 5. አምስት | V |
| ፮. ስድስቱ | 6. ስድስት | VI |
| ፯. ሰባቱ | 7. ሰባት | VII |
| ፰. ሰመንቱ | 8. ስምንት | VIII |
| ፱. ተስዓቱ | 9. ዘጠኝ | IX |
| ፲. ዓሠርቱ | 10. ዐሥር | X |

| | | |
|---|---|---|
| ፲ወ፩ ዓሠርቱ ወአሐዱ | 11 ዐሥራ አንድ | eleven |
| ፲ወ፪ ዓሠርቱ ወክልዔቱ | 12 ዐሥራ ሁለት | tewelve |
| ፲ወ፫ ዓሠርቱ ወሠለስቱ | 13 ዐሥራ ሦስት | thirteen |
| ፲ወ፬ ዓሠርቱ ወአርባዕቱ | 14 ዐሥራ አራት | fourteen |
| ፲ወ፭ ዓሠርቱ ወኃምስቱ | 15 ዐሥራ አምስት | fifteen |
| ፲ወ፮ ዓሠርቱ ወስድስቱ | 16 ዐሥራ ስድስት | sixteen |
| ፲ወ፯ ዓሠርቱ ወሰባቱ | 17 ዐሥራ ሰባት | seventeen |
| ፲ወ፰ ዓሠርቱ ወሰመንቱ | 18 ዐሥራ ስምንት | eighteen |
| ፲ወ፱ ዓሠርቱ ወተሰዓቱ | 19 ዐሥራ ዘጠኝ | ninteen |

፳ ዕሥራ - 20 - ሃያ - Twenty
፴ ሠላሳ - 30 - ሠላሳ - Thirty
፵ አርብዓ - 40 - አርባ - Forty
፶ ኀምሳ - 40 - አምሳ - Fifty
፷ ስሳ - 60 - ስድሳ - Sixty
፸ ሰብዓ - 70 - ሰባ - Seventy
፹ ሠማንያ - 80 - ሰማኒያ - Eighty
፺ ተሰዓ - 90 - ዘጠና - Ninety
፻ ምዕት - 100 - መቶ - Hundred
፲፻ ዓሠርቱ ምዕት /ሺህ/ - 1000 - ሺ. - One Thousand
፻፻ እልፍ - 10,000 ዓሥር ሺ. - Ten Thousand
፲፻፻ አእላፍ - 100,000 - መቶ ሺ. Hundred Thousand
፻፻፻ አእላፋት - 1,0000o,000 - ሚሊዮን Million
፲፻፻፻ እልፊት - 10,000,000 - ዐሥር ሚሊዮን Ten Million
፻፻፻፻ እልፊት - 100,000,000- መቶ ሚሊዮን Hundred Million
፲፻፻፻፻ ዓሠርቱ ምእልፊት -1,000,000,000 አንድ ቢሊዮን Billion

ዓሠርቱ ምዕት - ሺህ ትእልፊት - ሺህ እልፍ
አእላፍ - ዓሥረ እልፍ ምእልፊት - እልፍ ጊዜ እልፍ
አእላፋት - መቶ እልፍ ዓሠርቱ ምእልፊት-ዓሠርቱ ጊዜ ምእልፊት - እልፍ ጊዜ እልፍ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የእምነት ነጻነት በኢትዮጵያ ሕግ

እምነት ማለት አንድን ነገር በእውነት አለ ብሎ ተጨባጭ ወይም ቁሳዊ ማረጋገጫ ሳይኖር መቀበል ወይም የኅሊና ግንዛቤ መውሰድ እንደ ሆነ ተደርጐ ሊተረጐም ይችላል:: በመሆኑም አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ እምነት ሊኖረው የሚችለው በነጻ ኅሊና አውጥቶና አውርዶ አስቦ አእምሮው የፈቀደለትን ያህል ሲረዳው ነው::

የእምነት ነጻነት ሰፋ ባለ መልኩ ሲታይ «የኅሊና ነጻነት» ማለትም ማንም ሰው ያለ ፍላጐቱ ማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖት ወይም እምነት እንዲቀበል አይገደድም ማለት ነው:: ማንም ሰው በማንኛውም መንገድ አንድን ሃይማኖት ከሌላው በመምረጡ ወይም ምንም ዓይነት ሃይማኖት እንዳይኖረው በመፈለጉ ምክንያት በምንም መንገድ አይቀጣም:: የአንድ ሰው የሃይማኖት እምነት የግል ጉዳይ እንጅ በመንግሥት ባለ ሥልጣናት ወይም በሌሎች ሰዎች አስገዳጅነት የሚመረጥ ወይም የሚተውና የሚለወጥ ጉዳይ አይደለም::

ይህ ግላዊ የሆነውን የሃይማኖት ወይም የእምነት ነጻነት ሰዎች ወይም መንግሥት በኃይል ሌሎችም የራሳቸውን ወይም ሌሎች የሚያምኑበትን ሃይማኖት ወይም እምነት እንዲከተል ለማስገደድ የሞከሩበት ጊዜ እንዳለ በታሪክ ተደጋግሞ ታይቷል:: የቅዱሳን ሐዋርያትን መከራና ስቃይ ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከቱ ለዚህ በቂ አስረጅ ነው::

ሃይማኖት ወይም እምነት እንደ የግለሰቡ እና የማኅበረሰቡ የአስተሳሰብ ሁኔታ በትምህርት፣ በፍላጐትና በነጻ ኅሊናው በሚኖረው ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ እንጅ መንግሥት በሚያወጣው ሕግና በኃይል በማስገደድ አንድን እምነት ማጥፋትና ሌላውን ማስፋፋት አይቻልም:: ይህንንም ከታሪክና ከሁሉም በላይ የእምነት መመሪያ በኾነው የአምላክ ቃል የሰው ልጅ በሂደት እየተማረ መጥቶ÷ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በብዙ አገሮች ብሔራዊ ሕጐች እምነት ወይም ሃይማኖት ሰዎች በነጻ ምርጫቸው እንጅ አንድን እምነት እንዲተዉ ሌላውን እንዲከተሉ መገደድ እንደ ሌለባቸው ተደንግጓል::

**ማንኛውም ሰው ሃይማኖትን በፕሬስ ውጤቶችም በሌላም ሲያስተምር ሲያስፋፋ የሌሎችን እምነት ማንቋሸሽ ፣ አማኞችንና የእምነቱ አስተማሪዎችን ክብር መንካት በዐዋጅ ቁጥር 34/85 አንቀጽ 10 እና 20 ስር በተደነገገው መሠረት ቅጣትን ያስከትላል::**

በዓለም አቀፍ ሕጐች ማለትም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ /1948 እ.ኤ.አ/፣ በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት /ዲሴምበር 19 ቀን 1966 እ.ኤ.አ/ በአንቀጽ 18፣በአህጉር /ክፍለ ዓለም/ አቀፍ ደረጃ ደግሞ የአሜሪካ መንግሥት ሰብአዊ መብቶች ስምምነት ሰነድ አንቀጽ 12 /ጁላይ 18 ቀን 1978/፣ በአፍሪካ ሰብአዊ መብቶች ቻርተር አንቀጽ 6 እና በአወሮፓ መንግሥት ሰብአዊ መብቶች ስምምነት ሰነድ አንቀጽ 9 በግልም ሆነ በቡድን ሰው የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል፣ የማስተማርና የማስፋፋት ነጻነት እንዳለው ተደንግጓል::

የኛም አገር የሕግ ሥርዓት ከላይ ከተጠቀሱት ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሆዎች አንጻር የተቃኘ ሆኖ እናገኘዋለን::

ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ በሥርዓተ ሕጋችን ሃይማኖትን ከመንግሥት በመለየት የመንግሥት ሃይማኖት ወይም ብሔራዊ ሃይማኖት እንዳይኖር ተደርጓል::

በተለይ በ1987 ዓ.ም. የታወጀውና አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአንቀጸ 11 «መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡ መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም:: መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም:: ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም» በማለት እምነት በአገራችን ያለውን ተቋማዊ ነጻነት በግልጽ ደንግጓል::

የሰዎችን የእምነት ነጻነት በተመለከተ ደግሞ በዚሁ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 27 በዝርዝር ተመልክቷል:: እንደ ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጐች ሁሉ በዚህ ሕገ መንግሥትም ማንኛውም ሰው የእምነት ነጻነት ማለትም የመረጠውን ሃይማኖት የመያዝ የመቀበል ለብቻው ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራና በይፋ የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማርና የመግለጽ መብት እንዳለው ተረጋግጧል::

የእምነት ነጻነት በሕገ መንግሥቱ ልዩ ቦታ ከተሠጣቸው መሠረታዊ የሰው ልጆች መብቶችና ነጻነቶች አንዱ ነው:: መሠረታዊ መብቶችንና ነጻነቶችን በማመላከት የተደነገጉ የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች አገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጐም እንዳለበት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13/2/ ያስገድዳል:: በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ላይ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌደራል መንግሥትና የክልል መንግሥት ሕግ አውጭ፣ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች ላይ መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ጥሎባቸዋል::

በአጠቃላይ በአገራችን ማንም ሰው የመረጠውን እምነት የመከተል፣ የማስተማርና የማስፋፋት መብት አለው:: መንግሥትን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ጣልቃ በመግባት በሌላው ሰው የእምነት ነጻነት ላይ ተጽዕኖ እንዳይደረግበት የሕግ ጥበቃ አለ::

ስለዚህ በሕጉ መሠረት የሌሎችን ሰዎች ነጻነትና መብት ለመጠበቅ ከተቀመጠው ገደብ ውጭ ማንም ሰው በማንኛውም ቦታ እና ጊዜ ሥርዓተ አምልኮቱን እንዳይፈጽም ሊከለከል ወይም ማንኛውም ተጽዕኖ ሊደረግበት አይገባም:: በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናት ይህንን መብትና ነጻነት ራሳቸው የማክበር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም እንዳይጣስ ብርቱ ጥንቃቄና ጥበቃ የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸው ከላይ ተመልክተናል::

አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ገባሬ ሠናይ ድርጅቶች በሚሠጧቸው ማኅበራዊ አገልግሎቶች ዜጐችን በድርጅቶች የሚደገፈውን እምነት ካልተቀበሉ አድልዎ ይፈጽሙባቸዋል:: በተለይ ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከትና ከባሕላዊ ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ መካሄድ እንዳለበት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 90 /2/ በግልጽ ተደንግጐ እያለ በአሁኑ ሰዓት በአንዳንድ መንግሥታዊ ባልሆኑ በጐ አድራጊ ድርጅቶችና የእምነት ድርጅቶች በተ ቋቋሙ ት/ቤቶች የሚ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ማሩ ሕፃናትና ወጣቶች ከወላጆቻቸው የወረሱትን ሃይማኖት እንዲለውጡ ይገደዳሉ:: ፈቃደኛ ካልሆኑ ደግሞ ሌሎች ምክንያቶች እየተፈለጉ ከትምህርት ገበታቸው እንዲወገዱ የሚደረግበት አጋጣሚ እየታየ ነው:: በአንዳንድ ሥት የትምህርት ተቋማ ትም ኃላፊዎች በተማሪዎቻቸው የእምነት ነጻነት ላይ የአገሪቱ ሕግ ከሚፈቅደው ውጭ ገደብ የሚጥሉ በት ሁኔታ አለ::

እነዚህ ድርጊቶች የአገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ የሚጥሱ በመሆናቸው የድርጊቱ ፈጻሚዎችን ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው:: እዚህ ላይ መብቱን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ የተጣለባቸው በየደረጃው ያሉ የመንግሥት ባለሥልጣናት ተጠያቂነት ስላለባቸው ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል::

ማንም ሰው የመረጠውን እምነት የመከተልና የማስፋፋት ነጻነት ከዓለም አቀፍ እስከ ብሔራዊ ሕጋችን ድረስ ያለውን ጥበቃ ተመልክተናል:: ይሁን እንጂ ይህ ነጻነት ገደብ የለሽ ወይም ፍጹማዊ የሆነ ነጻነት አይደለም:: ስለሆነም ይህ ነጻነት /መብት/ የሚገደብበትን ሁኔታ እንመለከታለን::

## የእምነት ነጻነት የሚገደብበት ሁኔታ

መብቶች በባሕርያቸው እርስ በእርሳቸው ይገዳደባሉ:: በእያንዳንዱ መብት ላይ ተከትሎ የሚመጣ ግዴታ አለ:: የአንዱ ሰው መብት ለሌሎች ግዴታ ይሆናል:: ይህ ሁኔታ በተለይ በሰብአዊ መብቶች ላይ ጐልቶ ይታያል:: አንድ ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው ስንል ሌሎች ሰዎች ይህንን መብት የማክበር ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል:: እንዲሁም አንድ ሰው በሕይወት የመኖር መብት የሚኖረው የሌሎችን ተመሳሳይ መብት እስካልተጋፋ ድረስ ነው::

ስለዚህም የእምነት ነጻነት ከመሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች አንዱ ቢሆንም የሚገደብበት ሁኔታዎች አሉ::

እነዚህም:–

1. የአሳብን ደኅንነት፣ሰላምን ፣ጤናን፣ትምህርትን፣የሞራል ሁኔታን ለመጠበቅ፤
2. የሌሎች ዜጐችን መሠረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ለመጠበቅ እና
3. መንግሥት ከሃይማኖት ነጻ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጐች ነው::

ማንም ሰው እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በጋራ ለማስተማር እና ለመግለጽ እንዲሁም የአንድ እምነት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸውን የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማትን የማቋቋም መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል::

የማንኛውም እምነት ተከታይ ከላይ የተገለጸውን መብት በመጠቀም የሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ የሕዝቡን ደኅንነትና ሰላም የሚያናጋ፤ በሕዝብ ጤና፣ ትምህርት እንዲሁም ሞራል ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም የሌሎችን ዜጐች ተመሳሳይ መብቶች ወይም ሌሎች መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን የሚጋፋ ሊሆን አይገባም::

አንድ ሰው የራሱን እምነት ለማስፋፋት በሚያስተምርበት ወቅት ትምህርቱ የሌሎችን እምነት ተከታዮች ክብርና ሞራል የሚነካ ከሆነ የሌሎችን ሰብአዊ መብት ከመዳፈሩም በላይ በሕዝብ መካከል ግጭት በማነሣሣት የሕዝብን ደኅንነትና ሰላም አደጋ ላይ ስለሚጥል በወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል::

ማንኛውም ሰው ሃይማኖትን በፕሬስ ውጤቶችም በሌላም ሲያስተምር ሲያስፋፋ የሌሎችን እምነት ማንቋሸሽ፣አማኞችንና የእምነቱን አስተማሪዎች ክብር መንካት በዐዋጅ ቁጥር 34/85 አንቀጽ 10 እና 20 ስር በተደነገገው መሠረት ቅጣትን ያስከትላል::

ይህን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አንዳንድ የእምነት ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የእምነትንና የፕሬስ ነጻነትን ሽፋን በማድረግ የሌሎችን ዜጐች ሃይማኖት በማንቋሸሽና የእምነቱን አማኞችና መምህራን በመዝለፍ በተለያዩ የፕሬስ ውጤቶች ሲተገትጉ ይታያል::

ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነት፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትና ታሪክ በማጣጣል የተጻፈውን «ገድል ወይስ ገደል?» የሚለውን ጨምሮ ሌሎች መጻሕፍትን በዋቢነት መጥቀሱ በቂ ነው::

የእነዚህ መጻሕፍት ይዘታቸው የደ ራሲዎችን እምነት ማስተማር ሳይሆን ሌሎች አማኞች የሚከተሉትን ሃይማኖት መንቀፍ እና ለሃይማኖቱ ተከታዮች ያላቸውን ንቀት እንዲሁም የሃይማኖቱን መምህራን ለመዝለፍና ለማዋረድ አልመው እንደ ሆነ መጻሕፍቱን ለተመለከተ አንባቢ ሁሉ ግልጽ ነው::

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ ታላቅ ክብር የሚሰጣቸውን የቅዱሳን ጻድቃንንና የሊቃነ መላእክትን ቅዱሳት ሥዕላት በሽፋን ገጾቻቸው ላይ አሳትመዋል:: በሽፋን ገጽ ላይ ስለ ተሣሉት ቅዱሳን የጻፉት ነገር የቅዱሳኑን ክብር የሚያዋርዱ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ታላቅ ክብር ያላቸውን ቅዱሳት ሥዕላት የሚያቃልሉ ናቸው:: ይህ ደግሞ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን መሠረት የወንጀል ድርጊት መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል::

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ክብር የተሰጣቸውን የእምነቱ መገለጫ የሆኑትን ቅዱሳን ሥዕላት ፣ቅዱሳት መጻሕፍት ምንም ዋጋ እንደ ሌላቸው አማኞችም ሞኞች፣ ምንም የማያውቁ ፣ መምህሮቻቸውንም አታላዮች ፣ አሳሳቾች እያሉ ጽፈዋል:: ይህ ድርጊት የሌሎችን ዜጐች መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ማለትም የእምነት ነጻነት የሚጋፋ፣የዜጐችን ክብርና ዝና የሚያዋርድ በመሆኑ ወንጀል ነው::

የደራሲዎች ሥራ በሰዎች መካከል ግጭት በመቀስቀስ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያናጋ በመሆኑ ከተጠያቂነት የሚድኑበት ሕጋዊ መንገድ አይኖርም::

በሌላ በኩል በተጠቀሱት መጻሕፍት ላይ የተጣሰው ሕግ ስለ ፕሬስ ነጻነት የወጣው ዐዋጅ አንቀጽ 12/1/ሀ ማናቸውም በጽሑፍ የሚሠራጭ የፕሬስ ውጤት ያለ በቂ ስም፣ አድራሻ፣ የዋናና የምክትል ዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ እንዲሁም የአሳታሚው ስምና አድራሻ መገለጽ አለበት ሲል ይደነግጋል:: ከላይ የተጠቀሱት መጻሕፍት ግን የደራሲው «ስም» ብቻ /የአባቱ ስም የለም/ ተጠቅሶ የት እንደ ታተመ አልተገለጸም:: ይህ ከተጠያቂነት ለማምለጥ የተደረገ ሙከራ ነው::

አንድ የኅትመት ውጤት ይዘቱ በሕግ የሚያስጠይቅና በየጊዜው የሚታተም /periodicals/ ከሆነ ተጠያቂው ዋና አዘጋጁ ነው:: የኅትመት ውጤቱ ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን በኅትመት ይዘት ላይ ተጠያቂ የሚሆነው አሳታሚው ነው:: ከላይ ለአብነት የጠቀስናቸው ኅትመቶች ግን በየጊዜው የሚወጡ /periodicals/ ሳይሆኑ መጻሕፍት ናቸው:: በመጻሕፍት ላይ ለሚወጡ ኅትመቶች በሕግ የሚያስጠይቁ ከሆነ ተጠያቂው ደራሲው ሳይሆን አሳታሚው በመሆኑ በመጻሕፍቱ ላይ አሳታሚው ማንና የት እንደ ሆነ አልተገለጸም::

ስለዚህ በመጻሕፍት ደራሲዎችና አሳታሚዎች የተፈጸመው ሕገ ወጥ ድርጊት ተደራራቢ የወንጀል ድርጊት በመሆኑ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ አይችሉም:: በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ተከታዮች መብታቸውን ለማስከበር የሚያስችላቸው የሕግ ጥበቃ ያላቸው መሆኑን ተገንዝበው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን በማቅረብ ለተፈጸመባቸው የመብት መደፈር ሕጋዊ እርምት እንዲወሰድላቸው ወደፊትም ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸምባቸው መከላከል የሚችሉ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## አሳስቦኛል

ከትእዛዛተ እግዚአብሔር አንዱ «እናትህንና አባትህን አክብር» የሚለው ነው። ይህም ካህናት አባቶቻችንን ጨምሮ ታላላቆቻችንን ሁሉ ማክበር እንደሚገባን የሚያመለክት ይመስለኛል። በርግጥም በማናቸውም ወገን የሚፈጸሙ ስሕተቶችን በቸልተኝነት ማለፍ ተገቢ አይደለም። ለዚህም ቢሆን የራሱ ሥርዓትና አገባብ አለው። ዳሩ ግን በተለይም አዕይንተ እግዚአብሔር የኾኑትን፣በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ሆነው የሚማልዱትንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የሚፈጽሙትን ካህናት አባቶቻችንን ያለ አገባብ የመዳፈርና የመናገር ሁኔታ እንደ ዋዛ እያየነው የመጣን ይመስለኛል። በእኔ በኩል ምንም ቢሆን አባታዊ ምክራቸውንና ትምህርታቸውን መቀበሉ አስፈላጊ ስለሆነ የሚገባቸውን አክብሮት መስጠት ይገባናል እላለሁ።

*መ/ር የማታዬ በለጠ*
*እምድብር*

## ብናስተውል

ብዙዎቻችን ስለ ዐበይት በዓላትና ሌሎችም መንፈሳዊ ጉዳዮችን የሚያስተምሩ በራሪ ወረቀቶችን በተለያዩ አጋጣሚዎች እናገኛለን። እኒህንም አንብበንና ተረድተን እንደ ሚገባቸው ማስቀመጥ እንዳለብን ግልጽ ነው፤ በይዘታቸው ስመ ቅዱሳንን ጨምሮ መንፈሳዊ ቁም ነገሮችን ስለ ያዙና ለተከታዩ ትውልድም ስለሚጠቅሙ። ይሁንና ብዙዎቻችን ከመጸዳጃ ቤት ጀምሮ ለሌሎች ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ስንጠቀምባቸው፣በአልባሌ ቦታ ስናስ ቀምጣቸው ይታያል። በመሆኑም አባቶቻችን ለመንፈሳዊ ጽሑፎችና መጻሕፍት ይሰጡ የነበሩትን ክብር በማስታወስ ማስተዋል የተመላበት አያያዝ ቢኖረን መልካም ነው።

*ግርማዬ ማሞ*
*አዊ ዞን-ግምጃ ቤት ጤና ጣቢያ*

*መንገደኛው*

## *መግፋት መገፋፋት እስከ ጥፋት*

*ኃ/ገብርኤል ዘሐና*

እንዴት ከረማችሁ? ሰው ሲጠፋ አትፈልጉም እንዴ? ይኸውላችሁ ክረምቱ ደኅና አለፈ ብዬ ስደሰት ደግሞ ሌላ ችግር ይዞ መጣ። አንድ ሰሞን ዋዕየ ፀሐዩ ሲበዛ አዞን ተሸንቆሮ ነው ተባለ። አሁን ደግሞ ብርዱ የባሰው ምኑ ተሸንቁሮ ይሆን?

መቼም መንገደኛው ብርድ አይል ሙቀት አይል ይሄዳል። በመሆኑም አንድ ቀን መንገደኛው ልቤ ወደ አመለከተኝ ልጓዝ ያገኘኋትን መኪና ተሳፍሬ...። ታዲያ አንድ ሁለት ምዕራፍ እንደ ተጓዝን መኪናዋ ዛለች፣ ተንቀሳቀሰች፣ ተንኳረረች፣ ጎማዎቿ ለመሽከርከር ዐቅም አጡ። አሽከርካሪው ባለው ሞያ ሊረዳት ብዙ ጣረ። ግን አልሆነላትም። ብርዱ ደግሞ ችግር አያውቅም መሰለኝ የመንገደኛውን ሁሉ አፍንጫ ያቀልጠው፣ እጅ እግሩን በቆፈን ያስረው ጀመረ።

የጨነቀው አሽከርካሪ መላ ላይሆን መላ ዘየደ። « ተሳፋሪዎች እስቲ ውረዱና ግፉ»አለ። የት ድረስ? አለ መንገደኛው ልቤ። መኪናዋ የአካል ብልቷ ከተሟላና ሕይወት የሚሆናት ነዳጅ ከተሟላላት መገፋት ያስፈልጋታል ወይ? ወርደን ገፋናት። ትንሽ ተንተፋትፋ ጸጥ አለች። «ኃይል ጨምሩ» ተባለ። መንገደኛው በመንገድ በዛለ አንጀቱ እንኳን መኪና ሊገፋ ራሱን መግፋት እያቃተው ነው።

ተሳፋሪዎች ብርዱ ሳያንሳቸው ጉዞአቸው እክል ስላገኘው ቢያበሳጫቸውም ካሰቡበት ለመድረስ ሲሉ መኪናዋን ይገፏታል። ገሚሱ ይስቃል። ገሚሱ ይነጫነጫል። መንገደኛው ከዳር ቆሞ ያሰላስላል። አንድ ነገር ትዝ አለው። እንደ ተበላሸችው መኪና የሚገፉ ሰዎች። ወዴት?

መኪና የምትገዛው ልትገፋ ሳይሆን ሥራ ሊሠራባት ነው። ሰውም የተፈጠረው በሰው ሊገፋ ሳይሆን በተሰጠው አእምሮ እየተመራ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሠራ ነው። መቼም አልፎ አልፎ መድከም ሊከሰት ይችላል። እንደ መኪናዋ። ሁሌ መገፋት ግን ተገፍቶ ከመንገድ መውጣትን ያስከትላል። አሁንም መንገደኛው ያብሰለስላል ሌሎቹም «ሆ፣... አንድ ላይ፣ አንድ ሁለት » እያሉ መኪናዋን ይገፋሉ። ወይ ፍንክች፣ ወደ ፊት ወደ ኋላ ብትነካ ያው ናት።

ቀጠለ መንገደኛው የሚገፉትንም የሚገፉትንም /ፉን አላሉና/ አስተዋለ። እነማን ናቸው የሚገፉን? ለምንድን ነው የሚገፉን? ወዴትስ ነው የሚገፉን? እንዲያው መገፋት ሳይሆን እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቁ ጥሩ ነው። በሃገራችን መግፋት መገፋፋት እየበዛ ነው፤ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ከደብሩ አለቃ ጋር ይገፋፋሉ። ወዴት ይሆን ግፊያው? ሌላም አለ። ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባትና ኑፋቄያቸውን መዝራት ያቃታቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን በልጆቿ በኩል ይገፏታል። ጉድ ነው። ሰው እንደ ጋሪ ሲገፋ አለቃው ይነሡልን ለማለት መገፋት፣ ክፉ አድራጊዎች እንዳይነኩ መገፋት፣ ለበጎው መገፋት ለክፉው መገፋት። እንደ መኪናዋ ወደ ፊት ወደ ኋላ መገፋት፤ እንዲያው አውጣኝ ነው የሚበጀው።

አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ። ልጁ በደብሩ የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት በአንድ የሥራ መደብ ያገለግላል። ታድያ ጥፋት ፈጸመ። በደንቡ መሠረት ከቦታው እንዲነሣ ሲል ደብሩ ለሃገረ ስብከቱ ደብዳቤ ይጽፋል። ይህን የሰማው ጎበዝ ወደ ሰንበት ት/ቤት ጎራ አለ። «ያለ አበሳዬ ሊያነሡኝ ነው» አለ። ከዚያ በኋላማ የሰንበት ት/ቤቱ አባላት ሰላማዊ ሰልፍ ልበለው .... ወደ ደብሩ ጽ/ቤት፣ ወደ አገረ ስብከት ጽ/ቤት ተመመ፤ ተንጫጫ። እርሱ ከተነሣ እኛም አንማርም አሉ። አስቸገሩ። ለምን? በጥሩ የምላስ ጉልበት ተገፍተዋላ። እናንተ የሚገፋው እኮ ሕይወት የሌለው ቁስ ነገር ነው። ደግሞስ እስቲ አሁን ለመንጫጫት መገፋት። ለሰላማዊ ሰልፍ መገፋት፤ ግፊያው ተፈጠረ፤ ለተባለው ችግር መፍትሔ ይገኝ ዘንድ መገፋፋቱ ወደ ጾም ጸሎት ቢሆንስ? መኪናዋ ብትገፋም አልተንቀሳቀሰችም። ጎበዝ ናት። ለክፋት ላለመገፋት እኛም እንደ መኪናዋ እምቢ ብንልስ? *መንገደኛው!!!*

| የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
| | የ6 ወር | 12 ወር | የ6 ወር | 12 ወር |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
Balew Tadelle and/or Mesfin Tilahun
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አዲስ መጽሐፍ

# ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት

"...እምነት ተስፋ ፍቅር ..."

- ነገረ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን አጣምሮ በመያዝ፤ የሠለስቱ ምእትን ጸሎተ ሃይማኖት መሠረት አድርጎ በመተንተን የቀረበ መጽሐፍ ነው።
- ኑፋቄና መናፍቃን በበዙበት፣ ክርክርና ተጠየቅ በሠለጠነበት፣ ሰው ሃይማኖቱን በሚገባ ማወቅና መረዳት በሚሻበት በዚህ ዘመን፣ የአበውን ሃይማኖት ትውልዱ ሊገባው በሚችል መልኩ የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው።
- በብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና አበው ታርሞ፣ በ484 ገጽ የቀረበው እና ዝግጅቱ ከ10 ዓመታት በላይ የፈጀው ይህ መጽሐፍ፣ ለመምህራነ ወንጌል እንደ ማጣቀሻ፣ ለምእመናን ደግሞ እንደ መማርያ ያገለግላል።

አዘጋጅ:-ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ

አሳታሚ:- ማኅበረ ቅዱሳን ዋጋ ብር 30.00

ውዳሴ ማርያም በኦሮምኛ
እንደ ገና ከእርምት ጋር ታትሞ በቅርብ
ቀን በሥርጭት ላይ ይውላል !!!

FAARFANNAAN
WALDAA QULQULLOOTAA
LAKK. 2
የኦሮምኛ ቁጥር 2 መዝሙር
በሥርጭት ላይ ውሏል!!



# አዳዲስ የቪድዮ ትምህርቶች

1ኛ/ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ:- በቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው
2ኛ/ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን:- በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ
⇨ ከዚህ በፊት በቪዲዮ የቀረቡ ትምህርቶች በVCD ተዘጋጅተው ቀርበዋል!!

ሁሉንም ኅትመቶች በሐመር መጽሔት እና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል።
ስልክ 23 45 29/ 23 45 30 መ.ሣ.ቁ. 80078
website:- http://www. eotc-mkidusan.org E-mail:- lemat@eotc-mkidusan.org

# በማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ

- የካህናት አልባሳት
- የመዘምራን ልብስ
- ጧፍ፣ ዕጣንና ዘቢብ
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች አልባሳት
- ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት
- በተክሊል ለሚጋቡ ሙሽሮች ካባ በኪራይ/ በግዥ ያገኛሉ።

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀን፣ ቀጠሮ አክብረን እንድናዘጋጅልዎ ይጎብኙን!!
ስልክ 56 67 88 መ.ሣ.ቁ. 80078

ዋጋ ብር 3.50

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡